ቢሠራም፣ ቀጣይነት ያለው ክርስቲያናዊ እድገትና መንፈሳዊነት ካሳየ፣ እንደገና ልናምነው ይገባል።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ:- በማኅበረ ምእመንና ውስጥ ኃጢአትን ለማረም የተሰጡትን መርሖዎች ተመልለሀ ከልሳቸው፡ ሀ) ቤተ ክርስቲያን ከእነዚህ መርሖዎች መካከል በሚገባ ተግባራዊ የምታደርገው የትኞቹን ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ በሚገባ ተግባራዊ የማታደርገው የትኞቹን መርሖዎች ነው? |

## ሦስተኛ ቀን

## ከአስተምህሮዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙትን ግጭቶች መፍታት።

የሚያሳዝነው፣ በታሪክ ሁሉ በአማኞች መካከል ከታዩት መራራ እስመግባባቶች አብዛኞቹ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ እስተ ምህሮዎች ግንዛቤ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ይህ ለመረዳት የሚችግር ነገር አይደለም። በብሉይ ኪዳንና በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ላይቀር የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ነበሩ። እነዚህንም አስተማሪዎች መከላከል የግድ ነበር። ጳውሎስ ከጻፋቸው ጠንካራ ቃላት አብዛኞቹ በሐሰተኛ አስተማሪዎች ላይ የተሰነዘሩ ነበሩ። እንዲያውም፣ ለገላትያ አማኞች አንድ ሰው እውነተኛ የሆነውን ወንጌል ካላስተማረ፣ ወደ ሲኦል እንዲወርድ ተናግሯል (ገላ. 1:6-9)። ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች ከአማኞች እንዲያውም ከሽማግሌዎች መካከል ሐሰተኛ ትምህርቶችን የሚያስተምሩ ሰዎች እንደሚነሡ ነግሯቸዋል። እንደ ሽማግሌዎች የራሳቸውን እምነትና የእግዚአብሔርን መንጋ መጠበቅ ያስፈልጋቸው ነበር (የሐዋ. 20:28-31)። ሁልጊዜም ሐሰተ ኛ ትምህርት ወይም ሚዛናዊ ያልሆነ እውነት የሚያስተምሩ ሰዎች መኖራቸው ስለማይቀር፣ ሁልጊዜም አስተምህሮዊ እስመግባባቶች እንደሚኖሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መረዳት አለባቸው። ስለሆነም፣ እግዚአብሔር የእውነት ጠባቂዎች አድርጎ የሾማቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎችን እንዴት



በትክክል ማስተናገድ እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው። ሐሰተኛ ትምህርቶችን በትክክል ካላረምን፣ «ተኩላዎች» የእግዚአብሔርን በጎች እንዲነጥቁ እየፈቀድን ነው ማለት ነው። ሐሰትን መከላከል መሪዎች ሊያከናውኑት የሚገባው የአመራር አካል ነው።

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአነስተኛ አስተምህሮዊ ጉዳዮች ላይ ይጣላሉ። የተለያዩ አማኞችና ቤተ እምነቶች በአንዳንድ አስተምህሮዎች ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እሳብ ለመረዳት ይቸገራሉ። አማኞች በእነዚህ ትናንሽ አስተ ምህሯዊ ጉዳዮች ላይ በመለያየት ከቤተ ክርስቲያናቸው ተለይተው አዳዲስ ቤተ እምነቶችን ይመሠርታሉ። አብዛኞቹ ታሪካዊ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት (መካነ ኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ ሙሉ ወንጌል) የተጀመሩት በአነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተ ምህሮዎች ላይ በተፈጠሩ ልዩነቶች ሳቢያ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በክርስቶስ አካል ውስጥ አንድነት እንዲኖር ለማድረግ የዚህ ዓይነቱን ልዩነት እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው።

| |
|---|
| 27ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዛሬ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተስፋፉ አማኞችን የሚያታልሉ ሐሰተኛ አስተምህሮዎች ምን ምንድን ናቸው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራሳቸውንና ምእመናንን ከእነዚህ ሐሰተኛ አስተምህሮ ዎች ለመጠበቅ ምን እያደረጉ ናቸው? ሐ) አማኞች ወይም ቤተ እምነቶች የሚለያዩበትን አነስተኛ አስተምህሮ ግለጽ። |

1. አስተምህሯዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በታሪክ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ከሚከተሉት ሁለት የተሳሳቱ አቋሞች አንዱን ለትይዝ ኖራለች።

<u>አንደኛ</u>፣ አማኞች ለአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሚሰጡት አተረጓጎም እርግጠኛ የሚሆኑባቸው ጊዜያት አሉ። ከዚያ በኋላ የአነርሱን አቋም የሚቃረኑትን ሁሉ አጥብቀው ይከላከላሉ። ራሳቸውን «የእውነት ጠባቂዎች» አድርገው በመመልከት፣ እውነት የማይመስለውን ማንኛውንም ነገር በኃይል ይቃወማሉ። አንዳንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች የሚወለዱት በአነስተኛ ጉዳዮች ላይ ይሆናል። ለምሳሌ፣ ስለ እልከ

ል መጠጦች፣ የሕጻናት ጥምቀት፣ ክርስቶስ ለሺህ ዓመታት በኢየሩሳሌም ስለ መንገሡ፣ ወዘተ. . . ከፍተኛ ውዝግቦች ተከስተ ዋል፡፡ ሴቶች አጭር ቀሚስ መልበስ ወይም «ሊፕ ስቲክ» ወይም የከንፈር ቀለም መቀባት አለባቸው ወይስ የለባቸውም በሚሉ ጉዳዮች ላይ መራር አለመግባባቶች ታይተዋል፡፡ አማኞች ዓለምን እንዳይመስሉ በመፍራታቸው ከእነርሱ የተለየ ግንዛቤ ያላቸውን ሌ ሎች አማኞች አጥብቀው ይቃወማሉ፡፡

ሁለተኛ፣ ስለ አስተምህሯዊ ጉዳዮች ማሰብ አስፈላጊ እይደለም ብለው የሚያስቡ አማኞች አሉ፡፡ ከሁሉም ጋር በሰላም ለመኖር ይፈልጋሉ፡፡ በመሆኑም፣ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ከሚተላለፉ ሰዎች ጋር ሳይቀር ተስማምተው ለመኖር ይፈልጋሉ፡፡ «ትክክል ከመሆን በፍቅር እብሮ መኖር አይሻልም?» ይላሉ፡፡ ስለሆነም፣ እንዲህ ዓይነት ሰዎችና እብያተ ክርስቲያናት ከግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር የሚጋጩትን አሳቦች ጭምር ይቀበላሉ፡፡

28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ክርስቲያኖች በእውነት ላይ ከሚገባው በላይ በማተኮራቸው ለፍቅርና አንድነት ደንታ- ቢስ ሲሆኑ የተመለከትበትን ሁኔታ በምሳሌነት ጥቀስ፡፡ ለ) ክርስቲያኖች ለፍቅርና አንድነት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠታቸው ምክንያት ለእውነት ደንታ- ቢስ ሲሆኑ የተመለከትክበትን ሁኔታ በምሳሌነት ጥቀስ፡፡ ሐ) እነዚህ ሁለቱም አቋሞች ለምን ለቤተ ክርስቲያን አደገኛ እንደ ሆኑ አብራራ፡፡

እነዚህ ሁለቱም አመለካከቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም፡፡ በኤፌሶን 4:15 ጳውሎስ እንደ አማኞች ሁልጊዜም «እውነትን በፍቅር» መናገር እንዳለብን ያስረዳል፡፡ ፍቅርና እውነት ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ክርስቶስ እንደ ተናገረው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚፈጥሩና እርሱን በእውነት የሚያመልኩ ሰዎች ብቻ ተቀባይነት ያገኛሉ (ዮሐ. 4:23-24)፡፡

2. አማኞች አስተምህሯዊ ውዝግቦችን እንዲያስተናግዱ የሚያግዟቸው ሁለት እውነቶች፡፡

ሀ. አማኞች ለእግዚአብሔር ቃል እውነት ሊያስቡና **ግልጽ የእግዚአብሔር ቃል ትምህርቶች** በሚጣሉበት ጊዜ ጠንካራ እርምጃ



ሊወስዱ ይገባል፡፡ እነዚህ ትምህርቶች ሁለት ርእሰ-ጉዳዮችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ፣ ግልጽ አስተምህሯዊ ትምህርቶች አሉ፡፡ ጳውሎስ አማኞች ነን እያሉ ሰው ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን በእምነት ብቻ እንደሚድን የሚያስረዳውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ያልተቀበሉትን አማኞች በአጽንኦት ተቃውሟል (ገላ. 1-2)፡፡ ዛሬ የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከላዊ እውነት የሚጥሱ ብዙ ሐሰተኛ ትምህርቶች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ሥላሴ የሚባል ነገር እንደሌለ፣ አንድ ሰው ለመዳን የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ እንዳለበት፣ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ ብዙ መንገዶች እንዳሉና ክርስቶስ ከእነዚህ መንገዶች አንዱ ብቻ እንደ ሆነ ያስተ ምራሉ፡፡ ግልጽ የእግዚእብሔር ቃል እውነት በሚጣስበት ጊዜ፣ አማኞች ጠንካራና ዳሩ ግን ፍቅር ያልተለየው እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡ ከዚህ ያነሰ ነገር ማድረጉ ለእግዚእብሔር እውነት ግድ እንደሌለን ያሳያል፡፡ የሐሰተኛ ትምህርቶችን ሐሰተኛነት ካላሳየን፣ ተግባራችን ከእግዚአብሔር የበለጠ እውቀት እንዳለንና እውነት የሆነውንና ያልሆነውን ነገር ራሳችን ለመወሰን እንደምንፈልግ ያሳያል፡፡ እግዚእብሔር በቃሉ የፈለገውን ቢናገርም፣ እኛ ደስ ያለንን ልናምንና እንደ ፈለግን ልንኖር እንደምንችል ማሳየታችን ነው፡፡

ሁለተኛ፣ መጠበቅ ያለብን ግልጽ የእግዚአብሔር ትእዛዛት አሉ፡፡ አማኞች እነዚህን ትእዛዛት በማያከብሩበት ጊዜ፣ ንስሐ እንዲገቡ ለማድረግ የቤተ ክርስቲያን የቅጣት እርምጃ መውሰድ አለብን፡፡ ለምሳሌ፣ ጳውሎስ ዝሙት በሚሠራ አማኝ ላይ ጠንካራ እርምጃ ወስዷል (1ኛ ቆሮ. 5)፡፡ እንዲሁም ደግሞ የማይሠራና ቤተ ሰቡን የማይደግፍ ሰው ከማያምን የከፋ መሆኑን ተናግሯል (1ኛ ጢሞ. 5:8፤ 2ኛ ተሰ. 3:6-15)፡፡ ዛሬ አፍቃሪዎችና ታጋሾች ለመሆን በመፈለጋቸው፣ አንዳንድ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚቃወመውን ዓይነት እኗኗር ይቀበላሉ፡፡ በእንዳንድ አገሮች ሰዎች እርስ በርሳቸው እስከ ተዋደዱና በመሐል የሚጎዳ ሰው እስከሌለ ድረስ፣ ዝሙትን መፈጸም ምንም እይደለም የሚሉ

አማኞች አሉ፡፡ ግብረ-ሰዶማዊነትን እንደ ኃጢአት የማይመለከቱ ሰዎችም አሉ፡፡ እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎችን በዚህ መንገድ ፈጥሯቸዋል የሚል ምክንያት ይሰጣሉ፡፡ ፍች የፈጸሙ ክርስቲያኖች ሳያቀጡ እንዲኖሩ ያደርጋሉ፡ ክርስቲያኖች አመለካከታችንን በማያምኑ ሰዎች ላይ ሳለመጫን መጠንቀቅ ቢኖርብንም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን ጽኑ አቋም ሊኖረን ይገባል (1ኛ ቆሮ. 5:9-13)፡፡ እኛ ከእግዚአብሔር በላይ እናውቃለን? እግዚአብሔር አንዳንድ ነገሮች ስሕተት ናቸው እያለ ተሳስተሃል ለማለት የሚያስችል ትዕቢት ሊኖረን ይገባል? የክርስቶስ ተከታዮች ከሆንን፣ እርሱ የሚለንን ሰምተን ልንታዘዘው ይገባል!

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰዎች በማይቀበሏቸው ጊዜ አማኞች በአጽንኦት ሊቃወሙ ይገባል የምትላቸውን በጣም አስፈላጊ አስተምህሮዎች ዘርዝር፡፡ ለ) ሰዎች ተቀባይነት ያለው ሰማድረግ በሚሞክሩበት ጊዜ አማኞች ሊቃወሙ የሚገባቸው ልምምዶች ወይም ተግባራት ምን ምንድን ናቸው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቁልፍ አስተምህሮዎችን ወይም ቁልፍ ልምምዶችን በጣሱት ሰዎች ላይ ጠንካራ እርምጃ ሲወስዱ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ መ) የቤተ ክርሰቲያን መሪዎች ቁልፍ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን ወይም ልምምድን በጣሰ ሰው ላይ እርምጃ ሳይወስዱ የቀሩበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ |

ሰ. አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የማያስተምራቸውን እውነቶች በተመለከተ መቻቻል ይኖርባቸዋል፡፡ በታሪክ አብዛኞቹ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ባልቀረቡ አነስተኛ አስተምህሮዎች ወይም ልምምዶች ምክንያት ተለያይተዋል፡፡ ሕጻናት መጠመቅ እንዳለባቸው የሚያመለክቱ አንዳንድ ጥቅሶች አሉ (የሐዋ. 16:31-33)፡፡ ነገር ግን ሕጻናት መጠመቃቸውን የሚያሳዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሉም፡፡ ጉዳዩ ግልጽ ባለመሆኑ፣ የተለያዩ ቤተ እምነቶች የተለያዩ አቋሞችን ይይዛሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች መጠጣት አለባቸው ወይ? ለሚለው ጥያቄ ግልጽ ምላሽ አይሰጠንም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አማኞች መጠጣታቸውን የሚያሳዩ አንዳንድ ምሳሌዎች አሉ፡፡ መስከር እንደማይገባ የሚያስጠነቅቁ ክፍሎችም አሉ፡፡ በተወሰነ መንገድ ከተነበቡ፣ መንፈሳዊ የሆኑ አማኞች ሁሉ በልሳን



ሊናገሩ እንደሚችሉ የሚያሳዩ ምንባቦች አሉ፡፡ የተለየ አሳብ የሚሰጡ ምንባቦችም እንዲሁ አሉ፡፡ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በግልጽ ያልቀረቡትን የአስተምህሮና የልምምድ ጉዳዮችን በተመለከተ ክርስቲያኖች ምን ማድረግ አለባቸው?

በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 እስከ 13፣ ጳውሎስ በአነስተኛ የአስተምህሮና የልምምድ ጉዳዮች ረገድ ፍቅር የራስን መንገድ ከመፈለግ የተሻለ መሆኑን አስተምሯል፡፡ የቆሮንቶስ አማኞች ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ መብላት አለብን ወይስ የለብንም? በሚል አሳብ ዙሪያ ይወዛገቡ ነበር፡፡ አማኞች በማኅበራዊ አምልኮ ወቅት በልሳን መናገር አለባቸው ወይስ የለባቸውም? በሚለው ጥያቄ ላይ የተጋጋለ ክርክር ይደረግ ነበር፡፡ ጳውሎስ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያልከለከለውን ልምምድ የሚተገብሩ ሰዎች የተለየ አቋም የሚይዙ ሰዎች ልክ እንደ እነርሱው እንዲሆኑ ማስገደድ እንደሌለባቸው አስረድቷል፡፡ (ለምሳሌ፣ የአሳማ ሥጋ መብላት፡፡) የተወሰነ አስተምህሮ የሚከተሉ ወይም የተወሰነ ልምምድ የሚለማመዱ ሰዎች ከእነርሱ የተለየ አቋም የሚይዙትን ሰዎች መናቅ የለባቸውም፡፡ (ለምሳሌ፣ በልሳን መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ምልክት ነው ማለት፡፡) ልምምዱን የማያደርጉት ደግሞ ከሚያደርጉት በላይ መንፈሳዊ አድርገው ራሳቸውን መመልከት የለባቸውም፡፡ (ለምሳሌ፣ እኔ ወደ ሲኒማ ቤት አልሄድም፡፡)

ላለመስማማት መስማማትንና እንደዚያውም ሆኖ ግለሰቡን ለመቀበል የሚያስችለን ፍቅር፣ ያኔ እንደ ነበረው ዛሬም በጣም አስፈሳጊ ነገር ነው፡፡ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደተናገረው፣ «ወሳኝ በሆኑት ጉዳዮች ላይ አንድ ዓይነት አቋም መያዝ አለብን፣ ወሳኝ ባልሆኑት ጉዳዮች ላይ ግን መቻቻል አለብን፡፡» እግዚአብሔርን የሚወድና ቃሉን ለመታዘዝ የሚፈልግ አማኝ ከአንተ የተለየ አቋም በሚይዝበት ጊዜ፣ ይህ ምናልባትም ከዚያ ወንድም የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ጋር የማያስማማን አነስተኛ አስተምህሮ መሆኑን የሚያሳይ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ብዙ ርቀን በመሄድ የሐሰት አስተማሪ ነህ ብለን ልንወቅሰው አይገባም፡፡ ጳውሎስ እንዳስጠነቀቀው፣ ሌላውን ሰው ለመፍረድ እኛ ማን ነን?

ሌሎች መልስ የሚሰጡት ለክርስቶስ እንጂ ለእኛ አይደለም (ሮሜ 14:4፤ 1ኛ ቆሮ. 4:1-5)::

| |
|---|
| 30ኛ ጥያቄ:- ሀ) ቁልፍ አስተምህሮዎች ያልሆኑና አማኞች የተሰያየ አቋም የሚይዙባቸው አስተምህሮዎች ናቸው የምትላቸውን ዘርዝር:: ለ) አማኞች በመቻቻል ክርስቲያናዊ ፍቅር ማሳየት ሲገባን የምንለያይባቸው ተግባራት (ልምምዶች) የትኞቹ ናቸው? ሐ) አማኞች ወሳኝ ባልሆኑ አስተምህሮዎች ወይም ልምምዶች ላይ ጠንካራ አቋም ይዘው አለመግባባትን ሲፈጥሩ የተመለከትካቸውን ሁኔታዎች በምሳሌነት ጥቀስ:: መ) ሁኔታውን ለማስተናገድ ፍቅርና መቻቻል ይበልጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገዶች ሊሆኑ ይችሉ የነበረበትን ሁኔታ አብራራ:: |

3. በክርስቲያኖች መካከል የአስተምህሮና የልምምድ ልዩነቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ ልንከተላቸው የሚገቡን ሁለት መሠረታዊ መርሖዎች::

ሀ. አንድ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ካልተከለከለ ወይም በግልጽ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ውጭ ካልሆነ፣ እያንዳንዱ አማኝ እግዚአብሔር እንዳደርገው ይፈልጋል የሚለውን መንገድ የመከተል ነጻነት አለው:: ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመኖቻቸው እንዲከተሉ የሚፈልጓቸውን አድርጉ አታድርጉ ዝርዝሮች ለማውጣት ይፈተናሉ (ለምሳሌ፣ ጫት አትቃሙ፣ እሑድ ቀን ገበያ አትሂዱ፣ ወዘተ. . .):: ይህንን የሚያደርጉት ምእመናንን መጥፎ ነው ብለው ከሚያስቡት ነገር ለመጠበቅ ካላቸው ፍላጎት በመነሣት ነው:: ነገር ግን፣ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን ሰው በአግባቡ ሊመራ እንደሚችል እርግጠኛ ነበር:: ስለሆነም፣ አንድ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ካልተከለከለ፣ አማኞች እንደ ክርስቶስ እንዴት መመላለስ እንዳለባቸው እንዲወስኑ ጳውሎስ ፈቅዷል:: በመሆኑም፣ ቤተ ክርስቲያን የሰዎችን እምነትና ተግባራት ለመቆጣጠር ከመሞከር ይልቅ፣ ምእመናን በሁሉም አሳብና ድርጊት እግዚአብሔርን ለማስከበር እንዲጥሩ ልታስተምር ይገባል:: (ቈላ. 3:17ን አንብብ::) ከዚያም መንፈስ ቅዱስ አማኞች እንዴት ክርስቶስን እንደሚከተሉ ሊመራቸው እንደሚችል ማመን ይኖርባቸዋል::



ለ. አማኞች በግልጽ ያልተከለከለውን ነገር የማድረግ ነጻነት ቢኖራቸውም፣ ትኩረት ማድረግ ያለብን ደስ በምንሰኝበት ነጻነት ላይ ሊሆን አይገባም:: ይልቁንም፣ እምነታችንንና ተግባራችንን በፍቅርና ለሌሎች በማሰብ ልንቆጣጠር ይገባል:: (1ኛ ቆሮ. 8:9-13፤ 10:23-33 አንብብ::) የምንወደውን የአምልኮ ስልት ከመከተል፣ የምንፈልገውን ከማመን፣ ወይም በምንፈልገው መንገድ ከመኖር በላይ አስፈላጊው ነገር ፍቅር ነው:: ፍቅር ሌላውን ሰው የሚጎዳ ተግባር ስለማይፈጽም፣ ሌሎች የማይወዱትን ወይም የማያምኑትን ነገር ላለማድረግ እንጠነቀቃለን:: ለምሳሌ፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 14 ውስጥ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማይተረጎም ልሳን መናገር ትክክል እንዳልሆነ አስተምሯል:: ለዚህም ምክንያቱ ልምምዱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚያመልኩ ሌሎች ሰዎች የማይመች በመሆኑ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የማይኮንነውን ተግባር (ለምሳሌ፣ ማጤስ፣ የተወሰነ የጸጉር አቆራረጥ፣ ፋሽን ልብሶችን መልበስ፣ ፊልም ማየት፣ ዓለማዊ ሙዚቃ ማዳመጥ) በተመለከተ የራሳችንን አቋም ለመያዝ የምንከተላቸው አምስት ደረጃዎች አሉ:-

1) ይህንን ነገር የማደርገው ወይም የማላደርገው ለክርስቶስ ያለኝን ፍቅር ለመግለጽ ነው? ክርስቶስ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» ብሏል (ዮሐ. 14:21):: ነገር ግን «እንድወዳችሁ ከፈለጋችሁ ትእዛዜን ጠብቁ» አላለም:: ክርስቶስ እንዲወደን ለማድረግ የምንፈጽመው ተግባር የለም:: ነገር ግን እርሱን ደስ አያሰኘውም ብለን የምናስበውን ነገር ባለማድረግ ለእርሱ ያለንን ፍቅር ልንገልጽለት እንችላለን::

2) የማደርገው ነገር «አዲስ ፍጥረት» መሆኔን ያሳያል? ጳውሎስ በክርስቶስ ባመንን ጊዜ አዲስ ፍጥረት እንደምንሆን ተናግሯል (ገላ. 6:15፤ 2ኛ ቆሮ. 5:17):: እንደ ክርስቶስ ተከታዮች እግዚአብሔር ፍላጎታችንን ስለ ለወጠ የማናደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ:: በእግዚአብሔር ጸጋ ክርስቶስን ለመከተል ከወሰንን በኋላ ሕይወታችን ይቀየራል::

3) እኔ የማደርገው ነገር በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ሰዎች ይጎዳ ይሆን? አንድን ሰው በምንወድበት ጊዜ፣ ደስ የሚያሰኘውን እንጂ የሚጎዳውን ነገር አናደርግም። ስለዚህ፣ እኔ የማደርገው ነገር ሌሎችን የሚጎዳ ከሆነ፣ ወይም ትክክል አይደለም ብለው የሚያስቡትን ነገር እንዲያደርጉ የሚገፋፋቸው ከሆነ፣ ለእነርሱ ባለኝ ፍቅር ምክንያት ላለማድረግ እወስናለሁ። ይህ የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ስልታችንን፣ አመጋገባችንን፣ ፊልም ማየታችንን፣ ወይም የተወሰኑ ልብሶች መልበሳችንን የሚመለከት ሊሆን ይችላል። ከእነዚህ ነገሮች አንዱን ማድረጌ ሰዎች በንጹሕ ሕሊና ክርስቶስን እንዳይከተሉ የሚያደርግ ከሆነ፣ ራሴን ከእነዚህ ድርጊቶች እቆጥባለሁ።

4) የማደርገው ነገር ለሌሎች የማቀርበውን ምስክርነት ይገድበዋል? መጽሐፍ ቅዱስ ምንም የማይጠቅሳቸውና ልናደርጋቸው የምንችላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ። ብናደርጋቸው ግን፣ የሌላ እምነት ተከታዮች እንደ ክርስቲያን ስለማይመለከቱን ምስክርነታችንን አይሰሙም። ለምሳሌ፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጫማ አድርገን ብንገባ፣ እግዚአብሔርን እንዳላከበርን የሚያስቡ አንዳንድ ሰዎች አሉ። በሌላ የሃይማኖት ተከታይ የታረደ ሥጋ ብበላ፣ በጣም የሚከፉ ሰዎች አሉ። እኔ እግዚአብሔር ይህንን እንደ ጥፋት አይመለከተውም ልል ብችልም፣ ለእነርሱ ካለኝ ፍቅርና ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ካለኝ ፍላጎት የተነሣ፣ ይህንን እርምጃ ከመውሰድ እቆጠባለሁ።

5) ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝን መንፈሳዊ እርምጃ በተወሰነ መንገድ ይገድብብኝ ይሆን? የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነውን ሥጋዬንስ ይጎዳው ይሆን? ለመንፈሳዊ ሕይወቴና አስተሳሰቤ ጎጂ እስከ ሆነ ድረስ፣ ማንኛውንም የተፈቀደ የሚመስል ነገር ማድረግ የለብኝም። ለምሳሌ፣ የተወሰኑ ፊልሞችን ማየት እግዚአብሔር የማይፈልጋቸውን ነገሮች እንዳደርግ የሚገፋፉኝ ከሆነ፣ ማየት የለብኝም። ጫት መቃም ወይም ማጤስ ለጤናዬ ጥሩ ስለማይሆን፣ አላደርገውም። ይህም በሰውነቴ ውስጥ ለሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ያለኝን አክብሮት ያሳያል።



31ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚይዟቸውንና ሌሎች ደግሞ የሚቃወሟቸውን ነገሮች በምሳሌነት ጥቀስ። ለ) አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚያከናውኗቸውንና ሌሎች የማይቀበሏቸውን ነገሮች ዘርዝር። ሐ) ልዩነቶች በሚኖሩበት ጊዜ፣ «ፍቅር» የሌሎችን ሰዎች ውሳኔዎች እንድናከብር የሚያደርገን እንዴት ነው? መ) አንድን አከራካሪ ነገር ማድረግ እንዳለብህ ወይም እንደሌለብህ ለመወሰን ከላይ የቀረቡት አምስት መርሖዎች የሚረዱህ እንዴት ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ባልተብራሩ ትናንሽ ጉዳዮች ላይ አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ፣ እያንዳንዱ ሰው የሚያምነውንና የሚያደርገውን ነገር እንዲመርጥ በፍቅር ነጻነት ልንሰጠው ይገባል። መሪዎች ሌሎችን የሚጎዳ ነገር ባለማድረግና በፍቅር በመመላለስ እግዚአብሔርን የማክበርን እውነት ማስተማር ይኖርብናል። እንደ መሪዎች ነገሮች በምስክርነታችን ላይ ስለሚያስከትሏቸው አሉታዊ ነገሮች፣ እንዴት ሌሎችን እንደሚጎዱ፣ ወይም ሰውነታችንን የሚጎዱ መሆናቸውን ልንናገር እንችላለን። ነገር ግን እንደ ጳውሎስ አማኞች እምነታቸውን በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚረዳቸው መተማመን አለብን። በአብያተ ክርስቲያኖቻችን የተዘጋጁትን ሕግጋት ሰዎች እንዲጠብቁ ማድረጉ የሰዎችን እምነት የሚጎዳ ነገር ነው። ብዙም ሳይቆይ ለእነዚህ ሰው-ሠራሽ ሕግጋት መገዛት አለመገዛታቸውን በመመልከት የሰዎችን (እና የራሳችንን) መንፈሳዊነት መገምገም እንጀምራለን። ነገር ግን መንፈሳዊነት የሚገለጸው በመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንጂ የተወሰኑ ውጫዊ ተግባራትን በማድረግ ወይም ባለማድረግ አይደለም (ገላ. 5:22-23)።

## አራተኛ ቀን

4. መንፈሳዊ አማኞችን በመሰብሰብ የክርስቶስ አካል ወሳኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ወይም ልምምድ የሆኑት የትኞቹ እንደ ሆኑ እንዲወስኑ ማድረግ።

32ኛ ጥያቄ፡- የሐዋ. 15፡1-35ን አንብብ። ሀ) የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በዚህ ክፍል የሚከራከሩት ስለ ምን አስተምህሮ ነበር? ለ) የክርክሩ ውጤት ምንድን ነበር? ሐ) አስተምህሯዊ ልዩነቶችን ስለ ማስተናገድ ከዚህ ክፍል ምን እንማራለን?

ሁልጊዜም አዳዲስ አስተምህሮዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ተ ግዳሮት መፍጠራቸው የማይቀር ነው። ከእነዚህ ትምህርቶች አንዳንዶቹ ከእግዚአብሔር ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ግን ከእግዚአብሔር አይደሉም። አንዳንዶች ለቤተ ክርስቲያን ጥሩዎች ሲሆኑ፣ ሌሎች ግን አይደሉም። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ቤተ ክርስቲያናችን የምታምነውንና የምትለማመደውን ነገር እንድንወስን እግዚአብሔር ይጠብቅብናል። ቪዲዮዎችና ቴሌቪዥን አዳዲስ ነገሮችን በፍጥነት በሚያመጡበት ዘመን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች መንጋቸውን መጠበቅ አለባቸው። ወንፊት ቆሻሻ ነገሮችን ከጤፍ እንደሚለይ ሁሉ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉንም ነገር በመመርመር እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው የሚፈልገውን መለየት አለባቸው።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ውስጥ የተጠቀሰው ታሪክ ክርስቲያኖች የአስተምህሮና የልምምድ ልዩነቶችን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው የሚያስተምር ነው። ይህ ክፍል በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከተከናወኑት ዐበይት ስብሰባዎች አንዱን ያሳያል። የዚያ ስብሰባ ውሳኔዎች ክርስቲያኖች ደኅንነትን የሚ ረዱበትን መንገድ ለሁልጊዜውም ቀይረዋል። የአማኞቹ ጥያቄ «አንድ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ምን ማድረግ አለበት?» የሚል ነበር። ለሰው ልጅ ከዚህ የበለጠ እውነት የለም። አንድ ሰው ሃይማኖተኛ ቢሆንም እንኳን፣ እግዚአብሔር ስለ ደኅንነት የሚያስተምረውን እውነት ካላወቀና ካልታዘዘ፣ የዘላለም ሕይወቱ በአደጋ ላይ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያትና ቀደምት አማኞች ለዚህ አስተምህሮ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ከስምምነት ላይ የደረሱት።

ዛሬ አስተምህሯዊ ልዩነቶችን ለመፍታት እንድንችል የዚህን ታሪክ ሥረ-መሠረት መረዳቱ ጠቃሚ ነው። ከ2000 ዓመታት



ለሚልቁ ጊዜያት የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበሩት አይሁዶች፣ የቃል ኪዳን ሕዝብ መሆናቸውን ለማሳየት ልጆቻ ቸውን ይገርዙ ነበር። በክርስቶስ ዘመን ይህ ልማድ ከፍተኛ ትኩ ረት ተሰጥቶት ነበር። ይህም የሆነው ግርዘቱን እንዲያቆሙ ግፊት ከሚያደርጉ አሕዛብ ጋር ከመስማማት ይልቅ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የሚኖሩትን አይሁዶች ለመለየት የሚያስችል በመሆኑ ነበር። በግሪክ ባህል ግርዘት እንደ አለመሠልጠን ይቆጠር ነበር። አይሁዶች ደግሞ ማንኛውም አሕዛብ ሳይገረዝ እግዚአብሔርን ሊከተል ይችላል ብለው አያስቡም ነበር። የአሕዛብ መገረዝ እግዚአብሔርን መከተላቸውን የሚያሳይ ጠቃሚ ምልክት ነው የሚል አሳብ ነበራቸው። ከዚህም በላይ፣ አሕዛብ ለሙሴ የተ ሰጡትን የብሉይ ኪዳን ሕግጋት መጠበቅ አለባቸው ብለው ያስቡ ነበር።

እግዚአብሔር በግርዘትና የተወሰኑ ምግቦችን ስለ መመገብ ምንም ዓይነት የብሉይ ኪዳን አመለካከት ሳልነበራቸው አሕዛብ ጳውሎስ ወንጌሉን እንዲሰብክላቸው አዘዘው። (ማስታወሻ፡- በብሉይ ኪዳን ሦስት ዓይነት ሕጎች ነበሩ። በመጀመሪያ፣ «አትግደል» ወይም «አታመንዝር» የሚሉ ዓይነት ሕጎች አሉ። ሁለተኛ፣ በመሠዊያ ላይ በግ እንደ መሠዋት፣ በሳምንቱ ቀናት ውስጥ የተ ወሰኑ ቀናት እንደ ማምለክ ያሉ ሃይማኖታዊ ሕጎች አሉ፡ ሦስተኛ፣ ሰዎች እንዴት እንደሚኖሩ የሚመሩ ሕጎች አሉ። ለምሳሌ ያህል፣ አሳማ ስለ አለመብላት፣ ላም ተቀበዝብዛ እርሻ ውስጥ በምትገባበት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባ፣ ወይም የግርዘትን አስፈላጊነት የሚያመለክቱ ሕጎች አሉ። ጳውሎስ አሕዛብ እግዚአብሔር በባህል ሳይወሰን ለሰዎች ሁሉ የሰጠውን የመጀመሪያውን ዓይነት ሕግ ብቻ እንዲጠብቁ ነበር የፈለገው። ሁለተኛና ሦስተኛ ዓይነት ሕጎች ለሰዎች ሁሉ የሚያስፈልጉ አይደሉም ሲል ገለጸ።) ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ለአይሁዶች እግዚአብሔርን የሚያሳስበው የልባቸው ጉዳይ እንደ ሆነና ክርስቶስን እስካመኑና እስከ ተከተሉት ድረስ፣ ተጨማሪ ነገር አያስፈልጋቸውም የሚል ትምህርት ያስተ ምር ነበር። እንዲያውም፣ ጳውሎስ አንድ ሰው እግዚአብሔር ያላዘዘውን ነገር እንዲያደርግ መጠየቅ፣ ደኅንነትን ከእግዚአብሔር

ለጣታነት ለው በሥራው የሚያገኘው ነገር ወደ ማድረጉ የሐሰት ትምህርትነት መለወጥ ነው ሲል አስተምሯል::

በአይሁድና እሕዛብ ክርስቲያኖች መካከል ጠንካራ ክርክር ይካሄድ ነበር:: በመሆኑም፣ ችግሩ በኢየሩሳሌም ወዳለችው እናት ቤተ ክርስቲያን፣ በተለይም በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እንዲወስኑ ክርስቶስ ኃላፊነት ወደ ሰጣቸው ሐዋርያት መውሰዱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ:: አይሁዶችም ሆኑ እሕዛብ ክርስቲያኖች ያው አማኞች ነበሩ:: ሁለቱም እግዚአብሔርን ይወዱና ትክክል የሆነውን ነገር ለማድረግ ይፈልጉ ነበር:: ነገር ግን፣ ሰላምን ለመፍጠር ከአንድ ውሳኔ ላይ መድረስ ያስፈልግ ነበር:: ጉዳዩ ሰው እንዴት ሊድን እንደሚችል የሚያመለክት መሠረታዊ የደኅንነት ጉዳይ በመሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ ትኩረት ለመስጠት ቻለች:: (ማስታወሻ:- በታሪክ ሁሉ በተለይም በመጀመሪያዎቹ 300 የቤተ ክርስቲያን ዓመታት በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ በዋና ዋና አስተምህሮዎች ላይ ክርክር ሲደረግና ማብራሪያ ሲሰጥ ቆይቷል:: በእነዚህ ዓለም-አቀፍ ጉባኤዎች ላይ «በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መካተት ያለባቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው? እግዚአብሔር ማን ነው? አንድ ወይስ ሦስት? ኢየሱስ ፍጹም እምላክና ፍጹም ሰው ነበር?»፣ ወዘተ. . . ለሚሉ ጥያቄዎች መፍትሔዎች ተሰጥተዋል::)

ከሐዋርያት ሥራ 15 ውስጥ አስተምህሯዊ ልዩነቶችን ወይም ሌሎች ዐበይት ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚያግዙንን ትምህርቶች እናገኛለን:-

ሀ. በሳል መንፈሳዊ አማኞች ሳይቀር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ለመከተል ልንወስናቸው በሚገቡን ነገሮች ላይ የአሳብ ልዩነት ይኖራቸዋል:: የተለያዩ ግንዛቤዎችን መያዝ ስሕተት አይደለም:: እውነትን በተለያየ መንገድ መመልከት መንፈሳዊ አለመሆን አይደለም:: በሳል ክርስቲያኖች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አመለካከቶች እንደሚኖሩ ስለሚያውቁ፣ የራሳቸውን አሳብ በሰው ላይ ለመጫን አይሞክሩም:: እንዲሁም፣ በሳል ክርስቲያኖች ሰዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ ብዙ የማናውቃቸው ነገሮች



እንዳሉ ያውቃሉ:: ጳውሎስ ይህ በቆሻሻ መስታወት እንደ መመልከት ነው ብሏል:: ትንሽ ነገር ልንመለከት ብንችልም፣ አብዛኛው ግን ብዥ ብዥ ይልብናል (1ኛ ቆሮ. 13:12):: ይህ ደግሞ አማኞች ሁሉንም ነገር እንደማናውቅ በማወቅ አንድን ጉዳይ በትሕትና መቅረብ እንዳለብን ያሳየናል:: እንዲሁም ደግሞ፣ በሳል አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው ብሎ የሚያስተምረውን አሳብ ማወቅና በዚሁ እውነት መኖር አስፈላጊ መሆኑን ይገነዘባሉ:: ስለሆነም፣ እግዚአብሔር በግልጽ የሚያስተምረውን እውነት ለማመንና ለመታዘዝ ክልባችን ልንቆርጥና እግዚአብሔር በግልጽ የማያስተምራቸውን ነገሮች በተመለከተ ታጋሾችና አፍቃሪዎች ልንሆን ይገባል::

ለ. አማኞች እውነትን ለማወቅና ባወቁት እውነት ለመኖር መሻት አለባቸው:: የተለያዩ አስተምህሮዎች እንዳሉን መካዱ የመንፈሳዊ ብስለት ምልክት አይደለም:: ያሉንን ልዩነቶች እንደሌሉ ለማድረግ መሞክሩም ጤናማ አመለካከት አይደለም:: እንዲያውም፣ አንዳንድ ክርስቲያኖች፣ ክርስቲያኖች በተለያዩ መንገዶች የሚረዷቸውን አስተምህሮዎች ለመረዳት የሚደረገውን ጥረት እንደ ተሳሳተ ነገር ይመለከታሉ:: ዛሬ አንዳንድ ወጣቶች አምልኮውና ኅብረቱ ጥሩ ስሜት ከፈጠረላቸው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለ መሆን አለመሆኑ አይጨነቁም:: እነዚህ ክርስቲያኖች አንድነት በመፍጠሩ ላይ ከመጠን በላይ ትኩረት ስለሚያደርጉ፣ እንድ ነገር እውነት ስለ መሆኑ ወይም ስላለመሆኑ አያስቡም:: እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የገለጸውን ለማመንና ለማድረግ የምንፈልግ ከሆነ፣ ሁልጊዜም እውነትን ለማመንና እርሱ የሚፈልገውን ለመተግበር መጣር አለብን:: እግዚአብሔር ከሚጠብቅብን ለመቀነስም ሆነ ለመጨመር መሞከር የለብንም::

ሐ. የሌሎች አማኞችን እምነትና ታዛዥነት ከመጠራጠር ይልቅ፣ በተቻላቸው መጠን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እየሞከሩ ናቸው ብለን ብናስብ መልካም ነው:: ጳውሎስ እንዳለው፣ ሁልጊዜም ፍቅር ስለ ሌሎች መልካሙን እንጂ ክፉውን አያስብም (1ኛ ቆሮ. 13:5-7 እንብብ):: ክርስቲያኖች ወሳኝ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ

በአሳብ ቢለያዩም እንኳን፣ የተለያዩ አመለካከቶቻቸውን ይዘው በሰላም ለመኖር መሞከር አለባቸው:: «ምንም ነገር» አለማመን መንፈሳዊ ብስለት አይደለም:: እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን በመመርመር የምናምነው ነገር ከሁሉም የተሻለ መልስ መሆኑን እንድናረጋግጥ ይጠብቅብናል:: (የሐዋ. 17:11ን አንብብ::) ነገር ግን መንፈሳዊ የሆኑ አማኞች ከእኛ የተለየ አመለካከት በሚኖራቸው ጊዜ፣ ይህ ምናልባትም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እውነት በሚገባ እንዳልተረዳን ሊያሳየን ይችላል::

መ. በአንድ አስተምህሮ ወይም ልምምድ ላይ የአመለካከት ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ፣ አማኞች የእግዚአብሔርን እውነት አብረው መፈለግ አለባቸው:: ሁሉንም እውነት የሚያውቅ አንድ ሰው ወይም አንድ ቤተ እምነት የለም:: በእውነት ልንኖር ከፈለግን፣ ሌሎች እምነታችንን ቢገመግሙ ምንም አይደለም:: ጳውሎስ ራሱ ሰዎች የትምህርቱን ትክክለኛነት እንዲገመግሙ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዟል (ገላ. 2:1-5):: የሚያሳስበን የቤተ እምነታችንን አስተምህሮ መጠበቅ ሳይሆን፣ በተቻለን መጠን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሻት ሊሆን ይገባል:: በሌላ በኩል፣ ሽማግሌዎችና የቤተ እምነት መሪዎች የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን እውነት የማወቅና የመከተል ኃላፊነት አለባቸው:: እንዳችን ከሌላችን የተለየ ግንዛቤ ቢኖረንም፣ ሁላችንም በተቻለን መጠን እግዚአብሔርን መታዘዝ አለብን::

ሠ. እነዚህን ውሳኔዎች ለብቻችን ማድረግ የለብንም:: ጉዳዩን ለመመርመር ከሌሎች አማኞች ጋር መሰባሰብ አለብን:: (ይህ ማለት እያንዳንዱ ቤተ እምነት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እውነት ለማወቅ እንዲችል ሌሎች የሚያስተምሩትን በጥንቃቄ መመርመር አለበት ማለት ነው:: አብያተ ክርስቲያናት ሊገመግሙ ከሚገባቸው ነገሮች መካከል በልሳን ስለ መናገር፣ በመንፈስ ስለ መገንደስ፣ ሴቶች መስበክ እንዳለባቸው ወይም እንደሌለባቸው፣ «የኢየሱስ ብቻ» ወይም «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» አስተምህሮ ይገኙባቸዋል::) አንድን እውነት ለመረዳት ጥረት በምናደርግበት ጊዜ የሚከተሉት ዓይነት ሰዎች ቢሳተፉና የሚያሳስቧቸውን ነገሮች ቢገልጹ መልካም ነው:-



1) ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የቆረጡ ሰዎች:: አማኞች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማግኘት እንዳለባቸውና ሌሎች ወይም ዓለም ምንም ብትል ፈቃዱን መፈጸም እንዳለባቸው ያምናሉ:: አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እውነት ለመታዘዝ ቃል በመግባት ውይይታቸውን ካልጀመሩ፣ ውሳኔያቸውን የሚያሳርፉበት መሠረት አይኖራቸውም:: ይህ መሠረት በማይኖራቸው ጊዜ ደግሞ፣ ወደ ጥብቅ ውሳኔ የማያደርሱ የተለያዩ አሳቦችን አንሥተው ከመወያየት ያለፈ ተግባር ሊያከናውኑ አይችሉም:: መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት መለኪያ ተደርጎ ካልተወሰደ፣ ሁሉም ሰው የየራሱን አመለካከት እያነሣ ወደ ከፋ ክርክር ከመግባት ያለፈ ውጤት ሊኖር አይችልም::

2) ለውይይት በቀረበው አስተምህሮ ወይም ልምምድ ላይ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ሰዎች:: በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ ላይ፣ በአስተምህሮው ላይ ተመሳሳይ አቋም ያላቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ጳውሎስና ሌሎችም ሰዎች እንዲናገሩ ዕድል ተሰጥቶአቸዋል:: የአንተን ድምጽ መልሰው ከሚያስተጋቡ ሰዎች ጋር መወያየት ምን ለውጥ ያመጣል? ይህ ቀደም ሲል የያዝከውን አቋም ከማጠናከር ያለፈ ሚና አይኖረውም:: ከዚህ ይልቅ፣ ቃሉን በመጠበቅ እግዚአብሔርን ለማስከበር ከሚፈልጉና ከአንተ የተለየ አመለካከት ካላቸው ሰዎች ጋር መወያየቱ የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረዋል:: የፈራጅነትን መንፈስ ከመያዝ ይልቅ፣ አሳባቸውን በመስማት አመለካከታቸውን ለመረዳት መሞከር አለብን - በአመለካከታቸው ባንስማማም እንኳ::

3) በእግዚአብሔር ቃል ልዩ ሥልጠና የወሰዱ ሰዎች:: ኢየሱስ ሐዋርያትን በሚገባ አሠልጥኖአቸው ነበር:: ጳውሎስ በክርስቶስ ከማመኑ በፊት የብሉይ ኪዳን ሊቅ ነበር:: በክርስቶስ ካመነ በኋላ ደግሞ ወንጌሉን ከክርስቶስ ተቀብሏል (ገላ. 1:12):: ሕይወት ዘመናቸውን ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናትና

በማዛመድ ላይ ያዋሉ ሰዎች አሉ:: እንዲህ ዓይነት ልዩ ሥልጠና ያላገኙ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ሊቶችን ሳያማክሩ በአስተምህሮዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት መሞከራቸው መንፈሳዊ ትዕቢት ነው:: የእግዚአብሔር ቃል የእምነታችን መመዘኛ ከሆነ፣ ቃሉን በሚገባ የሚያውቁ ሰዎች የውይይቱ አካል መሆን አለባቸው:: እነዚህ ሰዎች በጥናታቸው የተለያዩ አመለካከቶችን ስላጠኑ፣ በቃሉ ውስጥ በግልጽ የቀረበው እውነትና ከአመለካከቶቹ አንዱ የሆነውን ለይተው ሊያሳዩን ይገባል:: (ማስታወሻ፡- ነገር ግን «የሥነ-መለኮት ሥልጠና» የወለዱና የእግዚአብሔር ቃል እንከን-የለሽ ነው የሚለውን አሳብ የማይቀበሉ ወይም ቃሉን ብቻ እምነታችንንና ልምምዳችንን ይወስናል የሚለውን አሳብ የማይቀበሉትን ምሑራን በዚህ ውስጥ ማሳተፍ የለብንም:: አሁን ብዙ የሥነ-መለኮት ትምህርት ቤቶች የእግዚአብሔርን ቃል ትክክለኛነት በመጠራጠር ላይ ናቸው:: እነዚህን መስማት የለብንም::)

4) የተለያዩ ልምዶች ያላቸውም ሰዎች የራሳቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው:: ጳውሎስ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ሲያደርግ ስለ ነበረው ነገር እንዲመሰክር ተጠርቶ ነበር:: ጴጥሮስም በቆርኔሌዎስ ቤት የገጠመውን ሁኔታ መስክሯል (የሐዋ. 10):: በተለያዩ ተዛማጅ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ሰዎች እግዚአብሔር ስላደረጋቸው ነገሮችና ውሳኔው በአገልግሎታቸው ላይ የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክተው አሳባቸውን እንዲናገሩ ማድረጉ ጠቃሚ ነው::

5) ሰፊው የክርስቶስ አካል:: በሐዋርያት ሥራ 15 በተገለጸው ስብሰባ ላይ ሐዋርያት፣ ሽማግሌዎች፣ የወንጌል መልእክተኞችና የቤተ ክርስቲያን አባላት ተሳትፈው ነበር:: ሁሉም እንዲሰሙና እንዲሳተፉ ተጋብዘው ነበር:: ብዙውን ጊዜ ጥቂት ሰዎችን ብቻ በማሳተፍ ውሳኔዎችን በምናሳልፍበት ጊዜ፣ ከባባድ ችግሮችን ለመፍታት አንችልም:: ሰዎች የተወሰኑ ውሳኔዎች የተሰጡበትን ምክንያት ስለማያወቁ፣ የተሰጠውን ውሳኔ ይጠራጠራሉ:: በተቻለ መጠን ብዙ ሰዎችን ማሳተፉ ጠቃሚ ነው:: ተሰብሳቢዎቹ በስብሰባው ላይ የሚነሡትን አሳቦች



የመስማትና የመረዳት ሚና ብቻ ቢኖራቸው እንኳን፣ መገኘታቸው አስፈላጊ ነው:: በዐበይት የአስተምህሮና የልምምድ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን ማሳለፍ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ የውሳኔ ሰጪዎችን ቁጥር በተቻለ መጠን ከፍ ማድረጉ አስፈላጊ ነው::

ረ. ጉዳዩ ከአቋማችን ንቀንቅ ማለት የማንችለው ዐቢይ አስተምህሮ ወይም የተለያዩ አመለካከቶችን ይዘን እንደ መንፈሳዊ አማኞች አብረን ልንኖር የምንችለው አነስተኛ አስተምህሮ መሆኑን መወሰን:: ጉዳዩ ግልጽ አስተምህሮ ወይም ትእዛዝ ከሆነ፣ ምንም ዓይነት ለውጥ ልናደርግበት አንችልም:: ነገር ግን አነስተኛ አስተምህሮ ወይም ትእዛዝ ከሆነ (ለምሳሌ፣ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን መሸፈን አለባቸው?)፣ የተለያዩ አመለካከቶች ያሏቸው ሰዎች በሰላም ለመኖር እንዲችሉ ልንስማማ እንችላለን:: በኢየሩሳሌሙ ስብሰባ ላይ ጳውሎስና ጴጥሮስ ሰላምን ለማምጣት ብሰው የወንጌሉን እውነት ለመቀየር አልሞከሩም:: እነርሱም ሆነ ጠቅላላይቱ ቤተ ክርስቲያን መዳን በእምነት መሆኑ ዐቢይ አስተምህሮ እንደ ሆነ ተረድተው ነበር:: አማኞች ሁሉ የዳንነው በእግዚአብሔር ጸጋ ወይም ነፃ ስጦታ መሆኑን ማመን ያስፈልጋቸው ነበር:: ለዚህም ነበር ወንጌሉን የሚጎዳው የአሕዛብ ግርዘት (አሕዛብን መግረዝ) አስፈላጊ ያልሆነው:: ነገር ግን፣ ከተነሡት ጉዳዮች መካከል አነስተኛ ትኩረት የሚሰጣቸውም ነበሩ:: እነዚህን በተመለከተ ግን ሐዋርያት ሰላምን ለመፍጥር ሲባል መስማማት አለብን የሚል አሳብ ነበራቸው:: ከእነዚህ አነስተኛ ጉዳዮች መካከል ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ የመብላት ጉዳይ አንዱ ነበር::

ጉዳዩ የቤተ ክርስቲያን ዐቢይ አስተምህሮ አለመሆኑን ቀደም ብለን ከወሰንን፣ ከሚከተሉት ሁለት ውሳኔዎች አንዱን እንደምንፈልግ እናውቃለን::

<u>በመጀመሪያ</u>፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች የተለያዩ አመለካከቶችን ሊይዙና በሰላምና በፍቅር ሊኖሩ የሚችሉባቸውን መንገዶች እንፈልጋለን:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ አማኞች የሚይዟቸውን አመለካከቶች በማብራራት፣ እነዚህ የተለያዩ

አመለካከቶች ያሏቸው አማኞች እንዴት በስምምነት ሊኖሩ እንደሚችሉ እንረዳቸዋለን:: ለምሳሌ፣ አማኞቹ በጸሎት ጊዜ በልሳን ስለ መናገር የተለያዩ አመለካከቶች ካሏቸው፣ ቤተ ክርስቲያን ምን ጊዜ በልሳን መናገር እንደሚቻልና ምን ጊዜ ደግሞ ስሌሎች በማሰብ በልሳን መናገር መገደብ እንዳለበት ልታስረዳ ትችላለች::

ወይም ሁለተኛ፣ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የተለየ አቋም ሊይዙ እንደሚችሉ እየተገነዘብን፣ እኛ ግን እንደ ክርስቶስ አካል በጉዳዩ ላይ የራሳችንን አቋም ስመያዝ ልንስማማ እንችላለን:: ለምሳሌ፣ በቤተ ክርስቲያናችን ልጆችን ላለማጥመቅ ወይም አልኮል ላለመጠጣት ልንስማማ እንችላለን:: ይህ የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት መብት ነው:: ነገር ግን፣ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የተለየ አቋም የመያዝ መብት እንዳላቸው መዘንጋት የለብንም:: ሰላምን ለመፍጠር ሲባል የእኛ አቋም የማይመቻቸው አማኞች ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እንዲሄዱ እናበረታታቸዋለን:: አማኞች ከእኛ ጋር ሆነው የማያምኑበትን ነገር ከሚያደርጉ፣ ወይም ሌሎች አማኞች እነርሱ የሚፈልጉትን እንዲያደርጉ በመገፋፋት ክፍፍል ከሚፈጥሩ፣ ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ቢሄዱ የተሻለ ነው:: ለምሳሌ፣ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሕዝብ ባለበት የጸሎት ስብስባ ላይ በልሳን መናገር አይቻልም የሚል ደንብ ካወጣች፣ በዚህ መንገድ በልሳን መናገር በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተፈቅዷል የሚል እምነት ያለው አማኝ አንድም በግሉ ብቻ በልሳን ለመናገር ወይም ይህንን ስጦታ እንዲጠቀም ወደምትፈቅድ ሌላ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አለበት:: አንድ አማኝ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍል የሚፈጥር ተግባር መፈጸሙ የፍቅር መንፈስ አይደለም::

| |
|---|
| 33ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሦስት ተጨማሪ አነስተኛ አስተምህሮዎችን ወይም ልምምዶችን ዘርዝር:: ለ) እነዚህ እያንዳንዳቸው አስተምህሮዎች ከላይ በተጠቀሱት ሁለት መንገዶች ሊስተናገዱ የሚችሉት እንዴት ነው? ሐ) ይህ ሁልጊዜ የራስን አቋም ለማጽደቅ ጥረት በማድረግ ክፍፍል ከመፍጠር የሚሻለው እንዴት ነው? መ) እነዚህን ጉዳዮች በመወሰኑ ሂደት ላይ ፍቅር ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ግለጽ:: |



ጉዳዩ የክርስትና እምነት ዐቢይ ክፍል ነው የሚል አቋም ካለን፣ አሳባችንን ልንለውጥ እንደማንችል እናውቃለን:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ የቀረበውን አስተምህሮ ወይም ልምምድ የማይቀበሉ አማኞች ከእግዚአብሔር ቃልና ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ውጭ መሆናቸው ይገለጻል::

ሰ. በዚህ ሂደት ውስጥ ከቁጣ ወይም ከጥላቻ ስሜት ነፃ መሆን አስፈላጊ ነው:: ይህ እርስ በርሳችን እንዳንደማመጥና የሌላውን ሰው አመለካከት በሚገባ እንዳንረዳ ይከላከላል:: በልባችን ውስጥ ስሜትና ቁጣ የሚፈጠረው ከግላዊ ወይም ከቤተ እምነታዊ ትዕቢት ነው:: ልባችንን በመመርመር ለምን እንደ ተናደድን መረዳት አለብን:: በልባችን ውስጥ መራር ነገር ካለ፣ መጀመሪያ ይህንን ችግር ማስወገድ አለብን:: መራራ ነገር ይዘን አንዳችን ሌላችንን ልንረዳና ልናዳምጥ አንችልም:: የተለየ አቋም በሚይዙ ሰዎች ላይ የተሰነዘሩ አላግባብ የሆኑ ቃላት ካሉ፣ ንስሐ መግባት ያስፈልጋል:: ሁሉም ሰው ወደ ስብሰባው መምጣት ያለበት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ በሚፈልግ ንጹሕ ልብ ነው:: መንፈስ ቅዱስ የሚመራንና አንድነትን ሊፈጥር የሚችለው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው::

ሸ. በጉዳዩ ላይ የእግዚአብሔር እጅ መኖሩን የሚያሳይ መረጃ መፈለግ አለብን:: ጳውሎስም ሆነ ጴጥሮስ እግዚአብሔር አሕዛብ እንዲገረዙ ሳያስገድድ ያደረጋቸውን ነገሮች ተናግረዋል:: እግዚአብሔር ያልተገረዘውን ቆርኔሌዎስን እንደ ተቀበለው አሳይቷል:: እንዲገረዙ ሳይጠይቅ መንፈስ ቅዱስን ለአሕዛብ አልሰጠምን? ጳውሎስ ምን ያህል አሕዛብ በክርስቶስ እንዳመኑና ሳይገረዙ ሕይወታቸው እንደ ተለወጠ ተናግሯል:: እግዚአብሔር በሠራው ሥራ ደስ በምንሰኝበት ጊዜ፣ የአሳብ ልዩነቶቻችን መራራ ስሜት እንዲፈጠር አያደርጉም::

ቀ. ሁለቱም ወገኖች አሳባቸውን ለመግለጽና ምክንያታቸውን ለማቅረብ ፍትሐዊ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል:: ባንስማማ እንኳን፣ የሌሎችን አመለካከት በፈራጅነት ሳይሆን፣ በስልታዊ መንገድ መስማት አለብን:: ለመረዳት መሞከር እንጂ ለክርክር ብለን

መስማት የለብንም። በአሳባቸው ላንስማማ ብንችልም፣ በፍቅርና በአክብሮት ልናስተናግዳቸው ይገባል። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመሥርተን ስለ አሳባቸው ፋይዳ ልንነጋገር ብንችልም፣ ስለ መንፈሳዊ ብስለታቸው ደረጃ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ስላላቸው የግል ተሞክሮ መነጋገር የለብንም። ፍትሐዊ ውይይት ለማካሄድ የጉዳዩን የተለያዩ ገጽታዎች መመርመር አለብን። ይህ ደግሞ ጊዜ የሚወስድ ነገር ነው። አለመግባባቱን የሚጨምርና በሰዎች መካከል የነበረውን ክፍፍል የሚያባብስ ውሳኔ ከመስጠት ይልቅ ተጨማሪ ጥናቶች እስኪደረጉ ድረስ መታገሡ መልካም ነው።

በ. «እውነትን በፍቅር በመናገር» አመለካከቶቻችንን መግለጽ አለብን። ዓላማችን ክርክሩን ማሸነፍ ሳይሆን፣ በጉዳዩ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ነው። ስለሆነም፣ እያንዳንዱ ሰው ወይም ቡድን የተረዳውን እውነት ሳይዋሽ፣ ሙሉ መረጃ ባለመስጠቱ ምክንያት እውነትን ሳያደበዝዝ፣ ወይም ሌሎች መጥፎ አመለካከት በመያዝ ከማመን እንዲመለሱ በሚያደርግ መልኩ የሰዎችን አባባል አዛብቶ ባለመጥቀስ አሳቡን ማካፈል አለበት። ስብሰባው አንዱ ሌላውን እንዲያሸንፍ ወደሚያደርግ ፉክክር ከተቀየረ፣ ወደ ተጋጋለ ክርክር ማምራቱና መንፈሳዊ ውሳኔ ከመሰጠት የሚያግድ መሆኑ ግልጽ ነው።

ተ. በሦስት ጥያቄዎች ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን፡-

1) እግዚአብሔር አንደኛውን ወይም ሌላኛውን አመለካከት እንደሚደግፍ የሚያሳዩ ምን ዓይነት ምልክቶች አሉ? እግዚአብሔር አንደኛውን አቋም እንደሚደግፍ የሚያሳይበት መንገድ አለ? ወይስ በሰብአዊ ድክመታቸው ውስጥ በመሥራት ለሁለቱም ወገኖች መቻቻልን እያሳየ ነው? እግዚአብሔር በአንድ ሁኔታ ውስጥ ሠራ ማለት ያንን አመለካከት እየደገፈ ነው ማለት ላይሆን ይችላል። ጳውሎስ በእርሱ ላይ ተጨማሪ ችግር ለማስከተል በማሰብ ወንጌል የሚሰብኩ ሰዎች እንደ ነበሩ ተናግሯል። ይሁን እንጂ፣ ሰዎች በዚህ ስብከት አማካኝነት ደኅንነትን በማግኘታቸው ጳውሎስ ደስ ተሰኝቷል (ፊልጵ. 1:15-18)። በርግጥ፣ እግዚአብሔር የእነዚህን ሰዎች ልባዊ አሳብ አይደግፍም ነበር። ነገር ግን በቸርነቱ



የቃሉ ኃይል እንዲሠራ እየፈቀደ ነበር። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ከመልእክተኞቹ ድክመት ባሻገር ኃይሉን በመግለጥ ፍጹም ባልሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ይሠራል። ስለሆነም፣ ስኬት መገኘቱ እግዚአብሔር አንድን አመለካከት መደገፉን አያሳይም።

2) መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል? ልምምድ ጥሩ ነገር ቢሆንም፣ ለአማኞች የመጨረሻው መመዘኛ ሊሆን አይችልም። ነገር ግን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በመመልከት የትኛውን አመለካከት እንደሚደግፍ መረዳት አለብን። ይህ አንድን ጥቅስ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ማገናዘብን የሚጠይቅ ነው። ተገቢ የአተረጓጎም ደንቦችን በመጠቀም አቋማችንን መመሥረት ይኖርብናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጽ ትምህርቶች ወይም መርሖዎች በሚኖሩበት ጊዜ፣ መታዘዝ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ትምህርት በልምምድ ውስጥ ከምንመለከተው ነገር ጋር በሚቀናጅበት ጊዜ፣ ትክክል ስለሆነው ነገር የበለጠ ልበ ሙሉነት ይኖረናል። ሰዎች ወደ ውሳኔ ለመምጣት የፈቀዱት ያዕቆብ የጳውሎስንና የጴጥሮስን ልምምድ ከቃሉ ጋር አስደግፎ ባቀረበላቸው ጊዜ ነበር። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉዳዩ ምንም የማይናገር ከሆነ፣ ወይም ግልጽ አቋም የማያሳይ ከሆነ፣ የተለያዩ መረዳቶች እንዲኖሩ መፍቀድ አለብን። የምንነጋገረው እንከን ስለሌለው የእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን፣ ስለ ሰዎች አመለካከቶች ነውና።

3) አንዱን ወይም ሌላኛውን አመለካከት ብንመርጥ፣ የውሳኔው አስከትሎቶች ምን ምንድን ናቸው? ማሰብ ያለብን ለሥነ-መለኮታዊ እውነት ብቻ ሳይሆን፣ ውሳኔያችን በሌሎች ሰዎች ላይ ስለሚያስከትላቸው ነገሮች ጭምር መሆን አለበት። ለዚህም ነው የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን፣ «አሕዛብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ አማኞች ተቀባይነት ለማግኘት መገረዝ አለባቸው ወይ?» በሚለው ጥያቄ ላይ ብቻ ያልተወሰኑት። አንድ እርምጃ በማከል ውሳኔው ስለሚያስከትላቸው ነገሮች ማሰብ ጀመሩ። አይሁዶችና አሕዛብ አብረው የሚያመልኩባቸው አብያተ ክርስቲያናት መኖራቸውን ያውቁ ነበር። አሕዛብ የሚያደርጓቸው አንዳንድ ነገሮች ለአይሁዶች የማይመቹ ነበሩ። የኅብረቱን መንፈስ

ለመጠበቅ ሲባል፣ አሕዛብ አንዳንድ ነገሮችን እንዳያደርጉ ተጠይቀዋል:: ከእነዚህም ነገሮች መካከል ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ መብላት አንዱ ነበር:: ፍቅርና አንድነት አሕዛብ የፈለጉትን ለማድረግ ነፃ ከመሆናቸው በላይ አስፈላጊዎች ነበሩ:: ዛሬም አብረን ለመሥራት በምንፈልግበት ጊዜ፣ ለአንደኛው ጎሳ ወይም ቤተ እምነት የማይመች እምነት ወይም ልምምድ ካለ (ስሕተት ነው የሚል እምነት ባይኖረንም እንኳ)፣ በፍቅር መተው አለብን::

ቸ. ውሳኔው እንዴት ለሰዎች እንደሚዳረስ በጥንቃቄ ማቀድ አለብን:: አንድን አስተምህሯዊ ጉዳይ ወይም ልምምድ በተመለከተ ከትክክለኛ ውሳኔ ላይ ከተደረሰ በኋላ፣ ውሳኔውን በማሳወቁ በኩል ጥንቃቄ የታከለበት ዕቅድ ባለመውጣቱ ምክንያት ሁኔታው አስከፊ ደረጃ ላይ የሚደርስባቸው አጋጣሚዎች አሉ:: አመለካከታቸው ድጋፍ ያላገኘላቸውን ሰዎች የስሜት መጎዳት የምንጠግንበትን መንገድ መፈለግ አለብን:: የእነርሱ ቁጣ ካልረገበ፣ ችግሩ አልተፈታም ማለት ነው:: ስለሆነም፣ ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ፣ መሪዎች ጉዳዩን ከሁለቱም አመለካከቶች አንጻር እንዴት እንደሚያረግቡ ማሰብ አለባቸው::

1) በዚህ ውሳኔ የተጎዱትን ወይም የሚጎዱትን ሰዎች ስሜት እንዴት እንፈውሳለን? ውሳኔውን ሳንሸረሽር፣ በክርክሩ «የተረቱት» ወገኖች ምንም ዓይነት ጎፍረት ወይም ያለመወደድ ስሜት ሳይሰማቸው በሰላም የሚኖሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለብን::

2) ውሳኔውን ብቻ ሳይሆን፣ ውሳኔው የተሰጠበትን ምክንያት ጭምር ለሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት ማሳወቅ:: የሰዎች ጥያቄዎች ሁሉ እስካልተመለሱ ድረስ፣ ችግሩ አይፈታም፤ ከፍፍሉም ይቀጥላል:: ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔውን የሰጠቡትን ምክንያት በጥንቃቄ ካብራሩና የምእመናን ጥያቄዎች ሁሉ ከተመለሱ፣ ባይወዱትም እንኳን ውሳኔውን ይቀበላሉ::

በአብዛኛው ፊት ለፊት ተገናኝቶ ማብራሪያ መስጠትና በጽሑፍ የሰፈሩትን አሳቦች መናገር የተሻለ መግባባት እንዲፈጠር ያደርጋል:: የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ ክሰጡ በኋ



ላ፣ ውሳኔውን ለአብያተ ክርስቲያናት የሚያደርሱ ሰዎችን መረጡ:: በተጨማሪም ደብዳቤ ጽፈው ሰጧቸው:: መሪዎቹ የውሳኔው አካል የነበሩትንና ማብራሪያ ሊሰጡ የሚችሉትን ሰዎች መላካቸው፣ በደብዳቤ ግልጽ ለማድረግ የሚከብዱትን ጉዳዮች ለማብራራት አስፈላጊ ነበር:: የደብዳቤው መኖር ደግሞ ሰዎች የውሳኔውን አሳብ እንዳይለውጡ ወይም እንዳያዛቡ ያደርጋል:: ደብዳቤውን ያደረሱ ሰዎች ከሄዱ በኋላ ጥያቄዎች ቢነሡ፣ ሰዎች ወደ ደብዳቤው በመሄድ ማብራሪያ ሊያገኙ ይችሉ ነበር::

ኀ. ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ነው ብላ የምታስበውን መሠረታዊ ውሳኔ ልንጠብቅና ግልጽ ስላልሆኑት አነስተኛ ጉዳዮች ታጋሾች ልንሆን ይገባል:: ከብዙ ዓመታት በኋላ ለጣዖት የተሠዋን ሥጋ የመብላቱ ጉዳይ በቆሮንቶስና ሮም አብያተ ክርስቲያናት ትልቅ ችግር ሆኖ በተነሣበት ወቅት ጳውሎስ ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት ተገድዷል (1ኛ ቆሮ. 8፣ ሮሜ 14):: ስለ ጉዳዩ በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ ላይ ለማንሣት ግን ጊዜው ገና ነበር:: ጳውሎስ ዋናው ችግር እንዲፈታና ቤተ ክርስቲያን ለአነስተኛ ጉዳዮች ወደ ፊት ደንብ እንድታወጣ ይፈልግ ነበር:: ምእመናን ሁሉንም ችግሮች እንዲፈቱ ብንገፋፋቸው፣ ሁሉንም ውሳኔ ሊቃወሙ ይችላሉ:: ሰዎች ከዋና ዋና ጉዳዮች ይልቅ በአነስተኞቹ ችግሮች ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይችላሉ:: ዋንኛው አስተምህሯዊ ጉዳይ ምን እንደ ሆነ ካወቅንና በእርሱ ላይ ከስምምነት ላይ ከደረስን፣ ሌሎች ጉዳዮችን መተው ጠቃሚ ነው:: የእግዚአብሔር መንፈስ አሁን ማስተካከል አለብን ወደምንለው ደረጃ እስኪያመጣቸው ድረስ፣ እነዚህ ነገሮች ላይ ትኩረት አለማድረጉ መልካም ነው::

34ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ምእመናን በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አማኞች በልሳን መናገር አለባቸው ወይ? በሚለው ጥያቄ ላይ አልተስማሙም እንበል:: ከላይ የቀረበውን ትምህርት በመጠቀም፣ እንዴት ይህንን አስተምህሯዊ ክርክር እንደምትፈታ ግለጽ:: ለ) ክርክሩ ሳይፈታ እንዲቀጥል ከማድረግ ይልቅ ይህንን ማድረጉ እንዴት የበለጠ አንድነት እንደሚያመጣ ግለጽ::

**የተለያዩ ቤተ እምነቶች ልዩ እምነቶቻቸውን ይዘው እንዴት አብረው ሊሠሩ እንደሚችሉ።**

የተለያዩ ቤተ እምነቶች አብረው ለመሥራት መፈለጋቸው ጥሩ ነገር ነው። ይህ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ሥር ያሉት ቤተ እምነቶች እንደሚያደርጉት ማለት ነው። ይህ ማለት የተለያዩ አስተምህሯዊ እምነቶችን የሚይዙ ሰዎች በቅርብ ይገናኛሉ ማለት ነው። ካልጠነቀቅን፣ ሰይጣን ልዩነቶቻችንን ተጠቅሞ ተጨማሪ ውዝግቦች ውስጥ ሊከትተን ይችላል። ችግሩ፣ አብሮ መሥራቱ አብያተ ክርስቲያናት የማያምኑባቸውን ነገሮች እንዲያደርጉ ሊያስገድዳቸው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ አስተምህሯዊ አቋሞቻችን ሊከበሩልን ይገባል በማለት ዛቻዎችን የሚሰነዝሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። (ለምሳሌ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚመጣው ከደኅንነት በኋላ ነው የሚሉ አብያተ ክርስቲያናት በጋራ በተዘጋጀው ጀማ ስብከተ ወንጌል ላይ የእነርሱን አቋም ከሚደግፉ አብያተ ክርስቲያናት ሰባኪ እንዲጋበዝ ይፈልጋሉ።) እንዲህ ዓይነት አመለካከቶች ፍቅርን የማያሳዩና ሌሎች ቤተ እምነቶችን የማያከብሩ በመሆናቸው ጤናማ አይደሉም።

እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንድነት እንዲኖረን ከተፈለገ፣ የተለያዩ ቤተ እምነቶች በሚከተሉት አሳቦች መስማማት አለባቸው የሚል እምነት አለኝ፡-

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዋና አስተምህሮዎች የትኞቹ እንደ ሆኑ ከስምምነት ላይ መድረስ አለባቸው። እነዚህን አስተምህሮዎች የሚቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ናቸው አብረው መሥራት ያለባቸው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንድነት ማድረግ የሚቻለው በእምነቱ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ሲኖር ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የአስተምህሮን ንጽሕና እንዲጠብቅ እንዳበረታታው ሁሉ፣ እያንዳንዷ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነቱን ዋና ዋና አስተምህሮዎች መጠበቅ አለባት (1ኛ ጢሞ. 1:18-20፤ 4:15-16፤ 2ኛ ጢሞ. 4:1-5)። ታሪክ እንዳመለከተው አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ለመፍጠር ብለው ዋና ዋና አስተምህሮዎችን በሚጥሉበት ጊዜ፣ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ከዓለም ጋር ተስማምተው እምነታቸውን ይተዋሉ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ዓለም አቀፍ የአብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ያሉትን ኢኩሜኒካል ቡድኖች የማይቀላቀሉት ከብዙ ቤተ እምነቶች ጋር አብረው ለመሥራት በሚያደርጉት ጥረት፣ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ስለሚጣሉ ነው። የእነዚህ ቡድኖች አባላት የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ለእግዚአብሔርና ለመጽሐፍ ቅዱስ ታማኞች ለመሆን ይቸገራሉ። ለአንድነት ብለን የመጽሐፍ ቅዱስን ዋና ዋና አስተምህሮዎች መካድ የለብንም። ይህ ቤተ ክርስቲያን ወደ መንፈሳዊ ሞት የምታዘግምበት የመጀመሪያው እርምጃ ነው። እግዚአብሔር በእውነት የማይኖሩትን አብያተ ክርስቲያናት አያከብርም (1ኛ ዮሐ. 4:6፤ 2ኛ ዮሐ. 1-4)።

2. እያንዳንዱ ቤተ እምነት የሌሎችን ቤተ እምነቶች ልዩ አስተምህሮዎችና ልምምዶች ማወቅ አለበት። መስማማት ባያስፈልግም፣ ማወቁ ጠቃሚ ነው። ከዚያም ግንኙነታችን በክርስቲያናዊ ፍቅር ላይ እንደሚመሠረት ማረጋገጥ አለብን። በክርስቲያናዊ ፍቅር ላይ የተመሠረተ ኅብረት እንዲኖር፣ እያንዳንዱ ቤተ እምነት የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለበት፡-

ሀ. ክርስቲያናዊ ፍቅር ማለት እኛ የራሳችንን መንገድ እንዲከተሉ ሳናስገድድ እያንዳንዱ ቤተ እምነት በእግዚአብሔር ፊት የራሱን አስተምህሯዊና ልምምዳዊ አቋሞች የመያዝ ነጻነት ይኖረዋል ማለት ነው። ስለዚህ፣ እያንዳንዱ ቤተ እምነት ስለ ጥምቀት፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት፣ አልኮል ስለ መጠጣት፣ ወዘተ. . . የራሱን አቋም የመያዝ ነጻነት ይኖረዋል ማለት ነው። አንደኛው ቤተ እምነት ስለ ሌላኛው ቤተ እምነት አስተምህሮዎችና ልምምዶች ጥያቄዎች ካሉት፣ ስለ ጉዳዩ መነጋገር ያለባቸው የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እንጂ ምእመናን መሆን የለባቸውም። አንድ ቤተ እምነት ሌላው ቤተ እምነት በአነስተኛ አስተምህሯዊ ጉዳዮች ላይ የራሱን አቋም እንዲይዝ የማንፈቅድ ወይም የራሳችንን አቋም እንዲከተል የምናስገድድ ከሆነ፣ አንድነቱ የውሸት ይሆናል ማለት ነው። አንዳችን የሌላችንን እምነት በፍቅር የማናከብር ከሆነ፣ በፍጹም አንድነት ሊኖር አይችልም።

ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቅር ማለት የሌላ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በራሳቸው ተነሣሽነት በአንድ ጉዳይ ላይ ስላለን አመለካከት እንድናብራራላቸው ካልጠየቁን በቀር፣ የእኛን ሥነ-መለኮታዊ አቋም እንዲከተሉ አለማድረግንም ይጨምራል። አንደኛው ቤተ እምነት «እኛ የበለጠ መንፈሳውያን ነን» በማለት የሌላውን ቤተ እምነት አባላት ወደ ራሱ የሚያፈልስ ከሆነ፣ ፍቅር የለም ማለት ነው። ምእመናን በራሳቸው ተነሣሽነት ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው የመሄድ መብት አላቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን ሆን ብለው «በጎችን» ለመስረቅ መሞከር የለባቸውም። ወደ ክርስቶስ በማፍለስ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ልናደርግ የምንችላቸው እጅግ ብዙ ዓለማውያን የሉምን? የሌላውን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሆን ብለው እየሰረቁ፣ በአንድነት እየሠራን ነው ማለት አይቻልም። የትኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም ሰባኪ ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ከቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት የተለየ ትምህርት ቢያቀርብ፣ ክርስቲያናዊ ፍቅር አለው ማለት አይቻልም።

ሐ. ክርስቲያናዊ ፍቅር ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ወይም በኮንፍረንስ አብረን በምንሠራበት ጊዜ፣ የሌላውን ቤተ እምነታዊ እምነቶች የሚጎዳ ምንም ዓይነት ነገር መደረግ የለበትም ማለት ነው። ስለሆነም፣ በጋራ የሚያዘጋጁት አንድ ኮንፍረንስ ካለ፣ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ማተኮር ያለባቸው በዋና ዓላማው ላይ መሆን አለበት። እንበልና፣ የተለያዩ አብያተ ክርስያናት አንድ ኮንፍረንስ በጋራ ለማዘጋጀት ተስማምተው ሳለ፣ የካሪዝማቲክ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሰባኪው የፈውስ አገልጋይ ወይም ሰዎችን በመንፈስ የሚገነድስ መሆን አለበት የሚል አቋም ያዙ። ይህ እንግዲህ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የማይስማሙበት ጉዳይ ነው። ይህ የካሪዝማቲክ መሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቅር አለማሳየታቸውንና ከዚህም የተነሣ በመካከላቸው እውነተኛ አንድነት አለመኖሩን የሚያሳይ ነው። የራሳችንን ልዩ እምነት በሌሎች ላይ ከመጫን ይልቅ፣ ሁሉም የሚያምኑባቸው ሌሎች ብዙ ትምህርቶች የሉምን? የሌሎችን እምነት የሚጻረር ችግር ከሚፈጠር፣ ተመሳሳይ አቋም ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ኮንፈ



ረንሶችን በጋራ ቢያዘጋጁ የተሻለ ነው። የክርስቲያናዊ አንድነት መሠረቱ ክርስቲያናዊ ፍቅር መሆን አለበት። ክርስቲያናዊ ፍቅር ደግሞ ከራሳችን በላይ ስለ ሌላው ማሰብ ነው። ጳውሎስ እንዳለው፣ ያለ ፍቅር የምናደርገው ነገር ሁሉ ከንቱ ነው (1ኛ ቆሮ. 13:1-3)።

35ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት አባል መሆናቸው ምን ምን ጥቅሞችን ያስገኝላቸዋል? ለ) በዐበይት አስተምህሮዎች ላይ ስምምነት ከሌለ፣ ወይም አንዱ ለሌላው እምነቶች ወይም አነስተኛ አስተምህሮዎች አክብሮት ከሌለው፣ ምን ዓይነት ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ? ሐ) አንድ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ልዩ እምነቶች በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ላይ ለመጫን ስትሞክር የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። መ) አንድ ቤተ ክርስቲያን የሌላ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በአባልነት እንዲቀላቀሏቸው ለማድረግ ሲሞክሩ የተመለከትክበት ሁኔታ ነበር? ሠ) ይህ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ስላለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንድነትና ክርስቲያናዊ ፍቅር ምን ያሳያል?

**የሚጣሉትን ሁለት የአማኞች ቡድኖች እንዴት ማስታረቅ እንደሚቻል።**

ሁሉም አማኞችና ቤተ እምነቶች በሰላም አብረው መኖራቸው ወሳኝ ነገር ቢሆንም፣ አማኞችና ቤተ እምነቶች የማይስሙባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። የሚጣሉ አማኞችና አብያተ ክርስቲያናት ብዙውን ጊዜ በሰላም ለመኖር ይቸገራሉ። እግዚአብሔር ግን ከሁኔታው ውጭ ያለውን ሰው በመጠቀም ሰላምን ያመጣል። ከቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና አገልግሎቶች አንዱ ክርስቲያኖች በሰላም እንዲኖሩ መርዳት ነው። ጳውሎስ በሳል አማኞች በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚጣሉትን አማኞች እንዲያስታርቁ ጠይቋቸዋል (ፊልጵ. 4:2-3)። ክርስቶስም የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው ብሏል (ማቴ. 5:9)። ስለሆነም፣ እግዚአብሔርን የሚያከብሩና ወንድሞቻቸውንና እኅቶቻቸውን የሚወዱ አማኞች፣ ሰዎች በአንድነት እንዲኖሩ መርዳት አለባቸው (ፊልጵ. 2:1-11)። እርቅ ለመፍጠር በሚደረግ ጥረት ውስጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስታወሱ ጠቃሚ ነው፦

1. ለሁለቱም ቡድኖች መጣላታቸው እግዚአብሔርን ሊያስደስት እንደማይችል ግለጽላቸው:: ከሌላው ጋር ተጣልተው የሚኖሩ እማኞች፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ነው የሚኖሩት:: ስለሆነም፣ ሰዎች የራሳቸውን ሰብአዊ ግንኙነቶች ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለመኖር ሲሉ እርቅን መፈጸም አለባቸው:: ይህ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸውና እድገታቸው አስፈላጊ ነገር ነው::

2. እርቅን ለመፍጠርም ሆነ የደረሰባቸውን ስሜታዊ ጉዳት ለማሸነፍ ሁለቱም ቡድኖች በእግዚአብሔር ላይ እንዲደገፉ አስታውሳቸው:: እንዳይታረቁ የሚያደርጓቸውን ነገሮች ለማስወገድ ጸሎት ወሳኝ ነው:: ሁለቱም ወገኖች ወደ እርቅ እንዳይመጡ የሚያደርጓቸውን ነገሮች እግዚአብሔር እንዲያስወግድላቸው ቢጸልዩ መልካም ነው::

እግዚአብሔር እርቅ እንዳይፈጸም የሚከላከሉትን መሰናክሎች እንዲያነሣ መጸለዩ፣ እያንዳንዱ ወገን ከሌሎች ጋር በሰላም ለመኖር እንደሚፈልግ እንዲገነዘብ ያስችለዋል:: አንድ ሰው ከልቡ እርቅን እስኪፈልግ ድረስ፣ ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉት ጥረት ምንም ዓይነት ፋይዳ ሊኖረው አይችልም:: ሰዎችን በግድ ማስታረቅ አይቻልም:: ሁለት ቡድኖች በግድ እንዲታረቁ በምናደርግበት ጊዜ፣ ሁለቱም ወገኖች መሬት ላይ ወድቀው ይቅርታ ሊጠያየቁ ይችላሉ:: ነገር ግን እውነተኛ እርቅ ለማድረግ የሚያስችል የልብ ለውጥ ልናመጣላቸው አንችልም:: ሁለቱ ቡድኖች መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳቸው በሚጸልዩበት ጊዜ፣ እርቅን እንደሚፈልጉ እየገለጹ ናቸው:: ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ከፍላጎታቸው ጋር በመዳመር እርቅን ያመጣላቸዋል::

3. በአመዛኙ ሁለቱም ወገኖች የሚያከብሩትን ሦስተኛ ሰው ማምጣቱ ቡድኖቹ እርስ በርሳቸው እንዲደማመጡና አንደኛው ስለ ሌላው ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ሦስተኛ አካል ሆኖ የሚመጣው ሽማግሌ ማን ትክክል እንደ ሆነና እንዳልሆነ የሚፈርድ ዳኛ ሳይሆን፣ ሰዎቹ ይቅር ተባብለው በሰላም እንዲኖሩ የሚያግዝ ነው:: ሽማግሌው ሁሉንም ነገር ስለማያውቅ፣ ራሱን



እንደ ዳኛ ቆጥሮ አንዱን ትክክል አንዱን ስሕተት ማለት የለበትም:: በሁሉም አለመግባባት ማለት ይቻላል፣ ሁለቱም ወገኖች ጥፋተኞች ሆነው ይገኛሉ::

እግዚአብሔር ሰዎችን እንድታስታርቅ እየጠየቀህ ከሆነ፣ ሁለቱም ወገኖች መጣላታቸው የሚያስከትለውን ውጤት እንዲገነዘቡ አድርግ:: በራሳቸውና በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ስለሚያመጡት አደጋ እንዲያስቡ አግዛቸው:: በአመዛኙ እያንዳንዳቸው የሚያቀርቡት ወቀሳ ማለቂያ አይኖረውም:: ይህ ደግሞ የበለጠ ጸብ እንዲፈጠር ያደርጋል:: ነገር ግን አለመግባባታቸው ምን ያህል ጎጂ እንደ ሆነ ስናሳያቸውና እርቅን በመፍጠር እግዚአብሔርን እንዲያስከብሩ በምንጠይቃቸው ሰዓት፣ እርስ በርሳቸው ለመደማመጥና የሚያስማሟቸውን ነጥቦች ሊያገኙ ይችላሉ::

4. እያንዳንዱ ቡድን ተራ በተራ አለመግባባቱን ምን እንዳመጣው እንዲናገሩ አድርግ:: የስሜት መጎዳትን በማስከተል እንዲራራቁ ያደረጓቸውን ነገሮች አስታውሰው ያስረዱ:: ነገር ግን እርስ በርሳቸው መወቃቀስ የለባቸውም:: ነገር ግን «. . . ሲከሰት . . . ስሜት አደረብኝ» ዓይነት አሳብ እንዲናገር አድርግ:: በዚህ መንገድ አሳባችንን በምንገልጽበት ጊዜ፣ ሌላውን ግለሰብ መውቀስ የለብንም:: ስሜቱ እንዲፈጠርብን ያደረገንን ነገር ነው የምናስበው:: ይህ እርስ በርሳችን እንዳንወቃቀስ ያደርገናል:: መወቃቀሱ ብዙውን ጊዜ መፍትሔ ሊያመጣ አይችልም::

5. አንዱ ቡድን የሌላውን ቡድን አሳብ በሚገባ እንዲረዳ ለማገዝ፣ ሽማግሌው የተነገሩትን አሳቦች በግልጽ ዓረፍተ ነገሮች ጠቅለል አድርጎ ቢደግም መልካም ነው:: ብዙውን ጊዜ ሰዎች ስሜታዊ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ምን እንደ ተከሰተና ለምን እንደ ተጎዱ በግልጽ ለመናገር ይቸገራሉ:: አንዱ የሌላውን አሳብ በተሳሳተ መንገድ በመረዳት መካረር ውስጥ መግባት የለባቸውም:: በመሆኑም፣ ሽማግሌው እያንዳንዱ ሰው ዐበይት ነጥቦችን በሚናገሩበት ጊዜ፣ የተረዱትን ነገር ጠቅለል አድርገው መግለጽ አለባቸው:: የዚህ ድርጊት ዓላማ ሰዎችን ለመውቀስ ሳይሆን፣ የተ

ከለተውን ነገርና የስሜት መጎዳቱን ማሳየት ነው። ሽማግሌው፣ «ስሜቴ የተጎዳው በ . . . ምክንያት ነው ነበር ያልከው? በትክክል ለምቼሃለሁ?» ማለት ይችላል። ይህ አንደኛው ቡድን ግልጽ ያልሆነውን ነገር ግልጽ የሚያደርግበትን ዕድል ይሰጣል። ይህም የሚያዳምጠው ወገን ሌላኛው ወገን ለምን እንደ ተጎዳ እንዲያስብ ያስችለዋል።

6. ሽማግሌው ወገንተኛነትን ማሳየት የለበትም። ከዚህ ይልቅ፣ እንዱ ቡድን የሌላውን አመለካከት እንዲረዳና ችግሩ ለምን እንደ ተከሰተ እንዲገነዘብ ያግዛል። ለምሳሌ፣ « . . . ስትል ለምን እንደ ተጎዳች አየህ?» ሊል ይችላል። የሽማግሌው ዓላማ እያንዳንዱ ቡድን ከሌላው እይታ አንጻር ሁኔታውን እንዲመለከት ማገዝ ነው።

7. ሽማግሌው እያንዳንዱ ቡድን ሌላኛውን ይቅርታ እንዲጠይቅ ማድረግ አለበት። ይህ ከልባቸው የማያደርጉት እንጂ፣ በግድ ወይም የሚጠበቅባቸው ስለሆነ ብቻ የሚፈጽሙት መሆን የለበትም። ነገር ግን አንድ ሰው አንድ ነገር አጥፍቻለሁ የሚል አሳብ ከሌለው፣ ይቅርታ እንዲጠይቅ (እንዲናዘዝ) ማስገደዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ይቅርታ ወይም ኑዛዜ ደግሞ አጠቃላይ ሳይሆን፣ ግለሰቡ የፈጸማቸውን ነገሮች የሚገልጽበት መሆን አለበት።

ይቅርታ በሁለት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል። _በመጀመሪያ_፣ በሌላኛው ቡድን ላይ ለፈጸሙት በደል ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች ሊወቃቀሱ፣ ከሁለቱም ወገኖች ጥፋቶች ይመዘዛሉ። ሐሜት፣ የሰውን ስም በማጥፋት ላይ ያተኮረ ውሸትና ሌሎችም ኃጢአቶች ይኖራሉ። ሁለቱም ወገኖች እነዚህን ኃጢአቶች መናዘዝ አለባቸው። ይቅርታ የሚጠይቀው ግለሰብ የፈጸመውን ኃጢአት ቢገልጽ መልካም ነው። ይህ ኃጢአቱን እንዲቀበልና ከኃጢአቱ እንዲማር ያስችለዋል። ለምሳሌ፣ አንደ ሰው፣ «ይቅር በለኝ፣ አምቼሃለሁ» ሊል ይችላል። ነገር ግን አንድን ሰው አልፈጸምኩትም እያለ በግድ ይቅርታ ልናስጠይቀው አንችልም። ይህ መዋሸት ይሆናል። ነገር ግን አንድ ሰው



የፈጸምኩት ነገር በእግዚአብሔር ፊት ስሕተት ነው የሚል እምነት ካለው፣ ይቅርታ መጠየቅ አለበት።

_ሁለተኛ_፣ ስሜታቸው የተጎዳባቸውን ሰዎች ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው። በየትኛውም አለመግባባት ውስጥ የስሜት መጎዳት የሚደርስባቸው ሰዎች አሉ። ምንም እንኳ የትኛውም ቡድን ፈጽሜአለሁ ብሎ የሚያስበው ግልጽ ኃጢአት ሳይኖር ቢችልም፣ ሁለቱም ወገኖች ይህንን ማድረግ አለባቸው።

አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ይቅርታ የሚጠይቅበት መንገድ እንደ ሰዎቹ ማንነትና ባህል የሚወሰን ይሆናል። ማልቀስ፣ መሬት ላይ ወድቆ ይቅር በሉኝ ማለት፣ መተቃቀፍ፣ ወዘተ. . . የይቅርታ መጠየቂያ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ። ዋናው ነገር ሰዎች ይቅርታ መጠየቃቸውን ለማሳየት አንዳንድ ውጫዊ ነገሮችን እንዲያከናውኑ አለማስገደዳችን ነው። ይህ ሁለቱ ቡድኖች ልባዊ ይቅርታ መደራረጋቸውን የሚያመለክት ጉዳይ ነው።

8. ቀጣይነት ያለው እርቅ ይኖር ዘንድ መቀየር ያለበት መሠረታዊ ችግር ካለ፣ ችግሩ ዳግም እንዳይከሰት በዚሁ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ መወያየቱ አስፈላጊ ነው። በመሠረታዊው ችግር ላይ ሳይወያዩ «ይቅር መባባል» ችግር ዳግም እንዳይከሰት ሳይከላከልልን ይችላል። ችግሩ ዳግም በሚከሰትበት ጊዜ ደግሞ በሰዎቹ መካከል ሥር የሰደደ ጸብና ክፍፍል ሊፈጠርና እርቁን የበለጠ አዳጋች ሊያደርግ ይችላል። እንዲሁም ደግሞ፣ በሁለቱ መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር ምን መደረግ እንዳለበት ሁለቱም ቡድኖች በግልጽ መነጋገር አለባቸው።

9. በችግሩ ውስጥ የተሳተፉት ሰዎች ሁሉ የተካሄደውን ውይይት ለማንም ላለመናገር ቃል መግባት አለባቸው። ስለዚህ ጉዳይ ምንም ዓይነት ሐሜት መነሣት የለበትም። ልክ ነጭ ጋዝ እሳትን እንደሚያቀጣጥል ሁሉ፣ ሐሜትም አለመግባባቱ በፍጥነት እንዲቀጣጠል የማድረግ ብቃት አለው።

10. ችግሩ የሚደጋገም ከሆነ፣ እማላጁ የተጠያቂነትን መዋቅር በማዘጋጀት ራሱ እማላጁ ወይም ሌላ መንፈሳዊ ሰው ከእያንዳንዱ

ቡድን ጋር በቅርብ የሚሠራበትን መንገድ ማመቻቸት ያሻል፡፡ እነዚህ የተጠያቂነት አጋሮች የቡድኖቹን ባሕርያትና ተግባራት በመቆጣጠር መጀመሪያ ለክፍፍል ያበቋቸውን እርምጃዎች እንዳይደግሙ ያደርጋሉ፡፡

36ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሁለት አማኞችን ለማስታረቅ የተደረገው ጥረት አለመሳካቱን የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ለምን ሳይሳካ የቀረ ይመስልሃል? ለ) ሁለት አማኞችን ለማስታረቅ የተደረገው ጥረት ሲሳካ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ በ ሀ) ውስጥ ያልተሳካው ነገር እዚህ ጋ የተሳካው ለምን ይመስልሃል? ሐ) ከላይ የተጠቀሱትን ደረጃዎች መከተሉ የተሻለ እርቅ ለመፍጠር የሚያስችለው እንዴት ነው? መ) የምታውቃቸውና የግንኙነት ችግር ያለባቸው ሰዎች አሉን? እግዚአብሔር እነዚህ ሰዎች እንዲታረቁ እንድትረዳ የሚፈልግ ይመስልሃል? እንዴት ልታስታርቃቸው እንደምትችል ወደ እግዚአብሔር መጸለዩ ጥሩ አማራጭ ይመስልሃል?

37ኛ ጥያቄ፡- አሁን ጊዜ ወስደህ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ አንድነት እንዲኖር ጸልይ፡፡ የጎዳኸው ሰው ካለና ይቅርታ መጠየቅ ካለብህ፣ እግዚአብሔር እንዲያሳይህ ጠይቀው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አንድን ሰው ወደ አእምሮህ ካመጣ፣ በፍጥነት ሂድና ይቅርታ ጠይቀው፡፡ ይቅርታ መጠየቅ ያለብህ ሰው ከሌለ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ስላለው ለሰላምና አንድነት እግዚአብሔርን አመስግን፡፡

ጥላቻና ክፍፍል በበዛበት ዓለም ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ በፍቅርና በአንድነት መኖርን መማር አለብን፡፡ ኃጢአተኞች በመሆናችን ምክንያት አንዳችን ሌላችንን ልንጎዳ እንደምንችል እናውቃለን፡፡ ግጭቶች ሲፈጠሩ እንደሚችሉም አይጠፋንም፡፡ ነገር ግን እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አንዳችን ስሌላው የይቅርታ መንፈስ ሊኖረን ይገባል፡፡ ይህንንም ስናደርግ፣ በክርስቶስ ላይ የተፈጸመው በደል በማናችንም ላይ ከደረሰው በላይ ከባድ መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል፡፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መጠበቅ አለብን፡፡ ይህም ማለት ክፍፍል በሚፈጥሩ ጉዳዮች ውስጥ በፍጥነት በመሳተፍ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ክርስቶስን የሚያስከብርና ለስሙ ታላቅ ምስክር ሊሆን የሚችል አንድነት መፍጠር ይኖርብናል፡፡ በቤተ ክርስቲያኖቻችን



ውስጥ ያሉትን ጸቦች ለማቆም ጊዜው አሁን አይመስላችሁም? እግዚአብሔር ሁላችንም የሰላም መሣሪያዎች እንድንሆን ይርዳን፡፡ አሜን፡፡

**አምስተኛ ቀን፡- ለሳምንታዊ ስብሰባ በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ፡፡**

## ሳምንታዊ ስብሰባ

*የመወያያ ጥያቄዎች፡-*

1\. ሀ) ሁለት ሰዎች የተለያዩ ባሕርያት ያሏቸው በመሆናቸው ምክንያት አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ለ) እኛን የሚያናድድ ባሕርይ ካላቸው ሰዎች ጋር በሰላም ለመኖር የሚያስችለን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ምንድን ነው?

2\. ሀ) ከተለያዩ ባህሎች ሳቢያ ሰዎች ሳይስማሙ ሲቀሩ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ለ) የተለያዩ ባህሎች ሲኖሩና አንደኛው ቡድን እናላ ጎላ ሲሆን፣ ማድረግ ስለሚገቡን ነገሮች ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ምን ተማርክ?

3\. ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኃጢአት ላይ ጠንካራ አቋም ሲወስዱ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ለ) ሽማግሌዎች ይህንን ሁኔታ እንዴት እንዳስተናገዱ ግለጽ፡፡ ጉዳዩ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ የተስተናገደው እንዴት ነበር? መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ ሁኔታ የተስተናገደውስ? ሐ) ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ቅጣት ያላቸው መረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው የሚለየው እንዴት ነው? መ) በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ኃጢአት የሚፈጽሙትን ሰዎች እንዴት ልናስተናግድ እንደምንችል ብናውቅ፣ የቤተ ክርስቲያን ቅጣት እንዴት ሊሰወጥ ይችላል?

4\. ሀ) በትንሽ የአስተምህሮ ጉዳይ ላይ አለመስማማት የተፈጠረበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያንን ሁኔታ የፈቱት እንዴት ነበር? ሐ) የሐዋርያት ሥራ 15ን ትምህርቶች መሠረት በማድረግ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አነስተኛ የአስተምህሮ ችግሮችን እንዴት በተሻለ ሁኔታ ሊፈቱ ይችላሉ?

5. ሀ) የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በአካባቢያችሁ ምን ያህል ጠንካራ ነው? ለ) ከኅብረቱ ጥቅሞች ያያችኋቸው የትኞቹ ናቸው? ሐ) ያያችኋቸው የኅብረቱ ድክመቶች ምን ምንድን ናቸው? መ) ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አንድነት አብረው ቢሠሩ ኖሮ፣ ኅብረቱ ምን ሊመስል ይችል እንደ ነበረ ተወያዩ።

6. ሀ) በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ አለመግባባት በመፍጠር ላይ ያሉትን አንዳንድ ቡድኖች ዘርዝሩ። ለ) ከዚህ ትምህርት በመነሣት፣ እናንተ (ወይም ሽማግሌዎች) እነዚህን ወገኖች ለማስታረቅ ምን ማድረግ ይጠበቅባችኋል? ሐ) በእውነተኛ ና እውነተኛ ባልሆኑ እርቆች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

# ትምህርት አሥራ ስድስት

## *የመጀመሪያ ቀን*

የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የሆኑት ዮሐንስና ጌታሁን በሚቀጥለው ዓመት ሊከናወን ስለሚገባው የቤተ ክርስቲያን ሥራ በመወያየት ላይ ናቸው። «ብዙ ገንዘብ ቢኖረን እኮ ሌላ ወንጌላዊ ወይም መጋቢ ቀጥረን በወንጌል ስብከትና አባሎቻችንን በማስተ ማር የተሻለ እንቅስቃሴ እናደርግ ነበር» እያሉ ይወያያሉ።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለምንድን ነው በርካታ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ገንዘብ በዋነኝነት አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚያስቡት? ይህ አመለካከት ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ። ለ) ማቴ. 9:35-38ን አንብብ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሥራ ሊሳካ እንዳልቻለ የሰጠው ምክንያት ምንድን ነበር? ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እንዴት እውን እንደ ሆነ አብራራ። |

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያን ስለሚያስፈልጋት ዋነኛ ነገር ሲናገሩ በዋነኝነት የሚያተኩሩት በገንዘብ አቅም ላይ



ነው። «በእኛ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ችግር በቂ ገንዘብ አለመኖሩ ነው» ይላሉ። የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ከተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ስለ አገልግሎት ሲነጋገር፣ «ለአገልግሎታችን ምን ያክል ገንዘብ ልትሰጠን አስበህ ነው?» የሚል ጥያቄ አንዳንድ ጊዜ ይጠየቃል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብን የችግራቸው ሁሉ መፍቻ ቁልፍ አድርገው ይመለከታሉ።

ነገር ግን እግዚአብሔር ነገሮችን የሚመለከተው በዚህ መንገድ አይደለም። እግዚአብሔር ዋነኛ የቤተ ክርስቲያን ሐብት አድርጎ የሚቆጥራቸው ሰዎችን ነው። ኢየሱስ መከሩ መድረሱን ባየ ጊዜ፣ የመከሩ ጌታ ለአጨዳው ሠራተኞችን እንዲልክ ጸልዩ እለ እንጂ፣ ሠራተኞችን ለመቅጠር ገንዘብ እንዲሰጣችሁ ጸልዩ አላለም። ይልቁንም፣ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሥራ የሚያዘጋጁ ሰዎች እንዲሰጣቸው እንዲጸልዩ ነገራቸው እንጂ (ማቴ. 9:35-38)። እግዚአብሔር ሰዎች ወደ አገልግሎት እንዲመጡ ይፈልጋል። እርሱ ሰዎችን ሲያገኝ፣ ገንዘባቸውንም አብሮ እንደሚያገኝ ያውቃል። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ራእይ እንዲያሳካ ከፈለግን፣ እርሱ የሰጠንን ሰዎች በጥሩ ሁኔታ ልንጠቀምባቸው ይገባል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ዓላማ ለማሳካት እርሱ የሰጣቸው ዋነኛ ሃብት ሰዎች መሆናቸውን ካልተረዱ በስተቀር፣ ለሥራው የሚሆን ገንዘብ አይለቅላቸውም።

እግዚአብሔር የሚሠራበት መንገድ አስቀድሞ ሰዎች ሕይወታቸውን ለአገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ነው። ከዚያ በኋላ ገንዘባቸውን ያገኛል። ሐዋርያው ጳውሎስ በመቄዶንያ ስላሉ አማኞች እንደ መሰከረው፣ መጀመሪያ ሰዎች ራሳቸውን ይሰጣሉ፣ ከዚያ ደግሞ ገንዘባቸውን ይሰጣሉ (2ኛ ቆሮ. 8:1-5)። እግዚአብሔ ር በቤተ ክርስቲያን የሚሠራበት መንገድ ቅደም ተከተል ይህ ነው። በመጀመሪያ ሰዎች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሥራ ይሰጣሉ። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ስለሚሠራው ነገር መደነቅ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው ስጦታዎች ጊዜአቸውን ሰጥተው ማገልገል ይጀምራሉ፣

ከዚያ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ገንዘብ ለእግዚአብሔር ሥራ እንዲያውሉት እናበረታታቸዋለን። ሰዎች በሰጡት ገንዘብ ሌላ አገልጋይ ቀጥሮ ማሠራት ግን የሚያስገኘው ውጤት አናሳ ነው። በመቶዎች የሚቆጠሩ የቤተ ክርስቲያን አባላት ራሳቸውን ለጌታ ሥራ ሲሰጡ ግን ብዙ ውጤት ይገኛል። ዛሬ አንድ መሪ መማር የሚገባውን ዋነኛ ነገር እናጠናለን- ይኸውም ሰዎች በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ እንዴት ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊገቡ እንደሚችሉ ነው።

## ክህሎት ዘጠኝ፡- የእግዚአብሔር ሰዎች በቡድን ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሠሩ ማድረግ።

*2ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮ. 12:7-11ን አንብብ። ሀ) ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም አማኞች ስጦታ ስለ መስጠቱ ምንድን ነበር ያለው? የእነዚህ ስጦታዎች ዓላማ ምንድን ነው?*

## የቤተ ክርስቲያን አባላት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መሳተፍ አለባቸው።

ለእግዚአብሔር ክብር ምን ማድረግ እንደሚገባ ማቀድ እንችላለን። ገንዘብን በሚገባ በሥራ ላይ ልናውል እንችላለን። ነገር ግን በአመራር ውስጥ አስቸጋሪ ነገር ከሰዎች ጋር መሥራት ነው። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያስቀመጠውን ዓላማ ለማሳካት ሰዎች ትልቅ ሃብት ናቸው። ያለ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሥራ ልንሠራ አንችልም። እግዚአብሔር ዕቅዱን እንድናሳካ የሰጠን ዋነኛ መሣሪያዎች የሰዎች ጊዜ፣ የጸጋ ስጦታዎችና ችሎታዎች ናቸው። ስለዚህ፣ መሪዎች ጥበብን በተላበሰ ሁኔታ ሰዎች ለእግዚአብሔር ክብር የእርሱን ሥራ እንዲሠሩ እንዴት ማነሣሣት እንደሚችሉ ማወቃቸው አስፈላጊ ነው።

**1. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት የእግዚአብሔር ሰዎች ዋነኛ መሣሪያ መሆናቸውን መረዳት አለባቸው።**



ዓለም ውሳኔዎችን የሚወስኑት መሪዎች እንደ ሆኑ ታስተምራለች። ውሳኔውን የሚፈጽሙት ደግሞ ሰዎች ናቸው። በብሉይ ኪዳን የነበረው አሠራር ይህ አይደለምን? ንጉሡ የፖለቲካ ውሳኔ ይወስናል፣ ሕዝቡ ደግሞ ለንጉሡ በመታዘዝ ይሠራል። (ለምሳሌ፣ ሕዝብ ታክስ ከመክፈል በተጨማሪ የሰሎሞንን ቤተ መንግሥት ሠርቷል።) ወይም ደግሞ ካህኑ መንፈሳዊ ውሳኔ ሲወስን፣ ሕዝቡ ይታዘዙታል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ አማኞች ሲመጣ የሆነ ነገር ከሥር መሠረቱ ተቀይሯል። በአዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአዲስ ኪዳንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መንገድ ሊመሩ የሚችሉባቸውን በርካታ እውነቶች እናገኛለን። እነዚህም እውነቶች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአባላትን ሚና የሚገነዘቡበትን መንገድ የሚያስተካክሉ ናቸው።

*ሀ. ሁሉም አማኞች በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን ማግኘት ይችላሉ (ዕብ. 4:14-16)።* ስለሆነም፣ በብሉይ ኪዳን አማኞች እግዚአብሔርን ለማምለክና ምን ማድረግ እንደሚገባቸው መመሪያ ለመቀበል ያደርጉ እንደ ነበረው በመሪዎቻቸው በኩል ማለፍ የለባቸውም። ወደ እግዚአብሔር አባታችን በቀጥታ መግባት እንችላለን። ጌታችንና ንጉሣችን ወደ ሆነው ኢየሱስ ክርስቶስም መግባት እንችላለን። ያ ማለት መሪዎች ራሳቸውን የእግዚአብሔር መንገድ ጠባቂዎች እንደ ሆኑና እግዚአብሔርም በእነርሱ ብቻ እንደሚናገር ሊያስቡ አይገባም ማለት ነው። እያንዳንዱ አማኝ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች እኩል ወደ እግዚአብሔር የመቅረብና ለሕዝቡ የሚሆን መመሪያ የመቀበል መብት አለው። የእግዚአብሔር ሕዝብ «ራስ» ኢየሱስ እንጂ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አይደሉም። በዕብራውያን 12:2-3 ላይ አማኞች የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ ወደ ሆነው ኢየሱስ እንድንመለከት ተነግሮናል።

ብዙ ጊዜ ትኩረታችንን ወደ መሪዎች አድርገን፣ «ያ መሪ ተከታዮች አሉት ወይ?» ብለን እንጠይቃለን። ለመሪ ቦታ የምንለጠው ሰዎች ተከትለውታል አልተከተሉትም ብለን ነው። ነገር ግን፣ በአዲስ ኪዳን ትክክለኛው ጥያቄ «ሰዎች መሪዎቻቸው

ካሳደሩባቸው መልካም ተጽዕኖዎች የተነሣ ኢየሱስን በተሻለ ሁኔታ መከተል ጀምረዋል ወይ?» የሚለው ነው:: የአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዓላማ ሰዎች እንዲከተሉት ማድረግ ሳይሆን፣ ሰዎች ኢየሱስን እንዲከተሉ ማድረግ ነው:: መሪዎች የሰዎች ትኩረት እነርሱን መከተሉ ላይ እንዲሆን ካደረጉ፣ እነዚያ መሪዎች በኢየሱስ ሊያዝ የሚገባውን የቤተ ክርስቲያን ራስነት ሥልጣን ወሰዱ ማለት ነው:: ያ ደግሞ ኢየሱስ ከአንድ ቤተ ክርስቲያን መሪ የሚጠብቀው ዓይነት አመራር አይደለም::

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ:- ሀ) መሪዎች ተከታዮቻቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚሉትን ከመስማትና ከማድረግ ኢየሱስ የሚላቸውን እንዲያደርጉ ቢያስተምሯቸውና ቢያበረታቷቸው የቤተ ክርስቲያን አመራር ምን ያክል ሊቀየር የሚችል ይመስልሃል? ለ) ሰዎች በቀጥታ ከእግዚአብሔር ከመስማት ይልቅ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትእዛዝ መቀበል ለምን የሚቀልላቸው ይመስልሃል? |

ለ. በእግዚአብሔር ፊት አማኞች ሁሉ አገልጋዮች ናቸው:: (1ኛ ጴጥ. 2:5-9ን ይመልከቱ::) ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንቀጥራቸው ሰዎች «አገልጋዮች» ናቸው ብለን እናስባለን:: አገልግሎት ውስጥ ምእመናን የሚኖራቸው አገልግሎት በታም አነስተኛ እንደ ሆነ እናስባለን:: እንዲያውም እነርሱ የሚከፍሉትን አሥራት ከመቀበልና እሑድ በአምልኮ ሰዓት ላይ ከመገኘት የዘለለ አንጠብቅባቸውም:: ነገር ግን ጴጥሮስ አማኞች ሁሉ «የንጉሥ ካህናት» እንደ ሆኑ ነው ያስተማረው:: እኛ የእግዚአብሔር ንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት ነን፣ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ደግሞ ማንም ከማንም አይበልጥም፣ ማንም ደግሞ ከማንም አያንስም:: እኛም ሌሎችን በማገልገል እግዚአብሔርን የምናገለግል ካህናትና አገልጋዮች ነን:: አማኞች ሁሉ በእግዚአብሔር እና በሌሎች አማኞች እንዲሁም በዓለም መካከል በመቆም የማገልገል መብትና ኃላፊነት አላቸው:: ካህን ዝም ብሎ ምንም ሳይሠራ በቤቱ እንዲቀመጥ አይደለም የሚጠበቅበት:: የካህን ኃላፊነት ለሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን መንገድ ማስተማር፣ እንዲሁም በጸሎት፣ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ ማስታረቅ ነው:: ስለዚህ ሰዎች መሪዎችና ተቀጣሪ አገልጋዮች ብቻ የቤተ ክርስቲያንን ሥራ



የሚሠሩበትና የቤተ ክርስቲያን አባላት ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን ትንሽ ብቻ እንደሚሠሩ አድርጎ ማሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪው ሁሉንም ነገር የሚያውቅበትና ውሳኔዎችን ሁሉ ብቻውን የሚወስንበት አሠራር ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው:: እግዚአብሔር ለልጆች ሁሉ እንዴት ሊያገለግሉ እንደሚገባ ትእዛዝ ሊሰጣቸው ይችላል፣ ይሰጣቸውማል:: በመሪዎች በኩል መናገር የለበትም:: መሪዎች ራሳቸውን እግዚአብሔር አማኞችን የሚናገርበትና የሚመራበት በር አድርገው ሊያስቡ አይገባም:: የቤተ ክርስቲያን አባላት ለእነርሱ እንዲሠሩላቸው ሌሎችን (ለምሳሌ፣ ወንጌላውያንንና መጋቢያንን) ሊቀጥሩ እንደሚችሉ እና በግላቸው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ አጃቸውን ሊያጠልቁ እንደማይገባቸው በፍጹም ማሰብ የለባቸውም::

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ያሉ አባላትን ገምግም:: በአገልግሎት ላይ ሁሉም ንቁ ተሳታፊዎች ናቸውን? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ሁሉም አባላት የእግዚአብሔር ካህናት መሆናቸውን ቢረዱና ለእርሱ ቢሠሩ ነገሮች ምን ያክል ሊቀየሩ ይችሉ እንደ ነበር አብራራ:: |

ሐ. አማኞች ሁሉ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማገልገል የሚችሉበት መንፈሳዊ የጸጋ ስጦታዎች አሏቸው (1ኛ ቆሮ. 12:7-11):: መጽሐፍ ቅዱስ አማኞችን እንደ አካል ነው የሚያያቸው:: «ራሱ» ወይም አሳብ የሚያመነጨው፣ አቅጣጫ የሚመራውና የሚያስችለው ኢየሱስ ነው:: አማኞች ደግሞ ራስ ሊቀር ሌላው የአካል ክፍል ናቸው:: አፍ፣ እጅ፣ እግር፣ ወዘተ. . . ናቸው:: አንድ አማኝ ሲድን፣ መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገው የመጀመሪያ ነገር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት መስጠት የሚችልበት ልዩ የጸጋ ስጦታና አገልግሎት መስጠት ነው:: ስለ ጸጋ ስጦታዎች አዲስ ኪዳን ውስጥ የሚከተሉትን እናነብባለን:-

1) የጸጋ ስጦታዎች ለአማኞች ሁሉ ተሰጥተዋል:: እግዚአብሔርን የሚያገለግልበት የጸጋ ስጦታ የሌለው አማኝ የለም:: ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎቶች ውስጥ እያንዳንዱ

አማኝ የጸጋ ስጦታ እንዳለው እንዲያውቅና እንዲያገለግልበት ማድረግ ነው። አማኞች ሁሉ እግዚአብሔር በታማኝነት በሰጠን የጸጋ ስጦታ እንዴት እንዳገለገልን እንጠይቃለን (ማቴ. 25:14-30)።

(ማስታወሻ:- ሐዋርያው ጳውሎስ በርካታ የጸጋ ስጦታዎች እንዳሉና ከእነዛ ውስጥም በልሳን መናገር አንዱ እንደ ሆነ ተናግሯል። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በአንዱ ላይ ብቻ ትኩረት ከሚያደርግ ይልቅ፣ ለጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ክብር ሲኖረው ይገባል። በልሳን መናገር፣ ወይም በፈውስ፣ አልያም በትንቢት ላይ ብቻ የምታተኩር ቤተ ክርስቲያን በፊቱ ላይ ትልቅ አፍ ብቻ ያለውን ሰው ትመስላለች (1ኛ ቆሮ. 12:14-20)። ቤተ ክርስቲያን ጤናማ የምትሆነው ሁሉም የጸጋ ስጦታዎች ሲከበሩና በጥቅም ላይ ሲውሉ ነው።)

2) የጸጋ ስጦታዎች ዓላማ ማገልገል ነው። የጸጋ ስጦታዎች ለሰዎች የሚሰጡት በቤተ ክርስቲያን እንዲያገለግሉባቸው ነው። የጸጋ ስጦታዎች የአንድ የቤተ ክርስቲያን አባል የግል ንብረቶችና ጥቅም ማግኛዎች አይደሉም። የሰውየውን «መንፈሳዊነት» ወይም «ታላቅነት» ለማሳየትም አይደለም የሚሰጡት። ይልቁን፣ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን አባላት የጸጋ ስጦታዎችን የሚሰጠው በዓለም ላለን እግዚአብሔርን እንድናገለግልበት ነው።

3) ጤነኛ በሆነች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጸጋ ስጦታዎች በሙሉ በአንድነትና በስምምነት በንቃት በጥቅም ላይ ይውላሉ። ጤናማ በሆነ ሰውነት ላይ እጅ ከዓይን፣ ከእግርና ከሌሎች የሰውነት ክፍሎች ጋር በስምምነት ይሠራል። ስለዚህ ጤናማ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉም አባላት እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን መሥራት የፈለገውን ለመሥራት በአንድነትና በትጋት ይሠራሉ። እግር የሌለውን ሰው አካል ጉዳተኛ እንለዋለን፣ ይህንን ስንል ሙሉ የሰውነት ክፍል የሌለው ማለታችን ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አንዲት ቤተ ክርስቲያን «ሙሉ» እና ጤነኛ የምትሆነው ሁሉም አባላት እግዚአብሔር የሰጣቸውን የጸጋ ስጦታ ሲጠቀሙ ብቻ ነው።



5ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር የሰጠህ የጸጋ ስጦታ ምንድን ነው? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን ለማገልገል እንዴት ነው የምትጠቀሙባቸው? ለ) አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የጸጋ ስጦታቸው ምን እንደ ሆነ የሚያውቁ ይመስልሃል? ካልሆነ፣ ለምን? ሐ) አማኞች ሁሉ እርስ በርስ ለማገልገል የጸጋ ስጦታቸውን ቢጠቀሙ ቤተ ክርስቲያናችሁ ምን ያክል ልትለወጥ ትችላለች?

ለ. የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚያስችለንን ኃይል የምናገኘው ከአንድ ምንጭ ነው። ያ የኃይል ምንጭ የትምህርት ደረጃ፣ የመጣንበት ብሔር ወይም ያለን ገንዘብ አይደለም። ይልቁንም፣ ያ የኃይል ምንጭ መንፈስ ቅዱስ ነው። በብሉይ ኪዳን ጊዜ እግዚአብሔር መንፈሱን ይሰጥ የነበረው ለተመረጡ መሪዎች ነበር፣ ስለዚህ የቀረው ሕዝብ አገልግሎት ለማግኘት በእነርሱ ነበር የሚደገፈው። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን በሁላችንም ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አለ። መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል፣ ይመራናል፣ ኃይልንም ያስታጥቀናል። ስለዚህ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት በቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪ ላይ ሊደገፉ አይገባም። እኛ የተማርን፣ ሴቶች፣ ወይም ድሆች ብንሆንም እንኳን፣ እግዚአብሔር እርሱን የምናገለግልበት ኃይል ሰጥቶናል።

ሠ. አዲስ ኪዳን እኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላት የተለየን ምርጥ እንደ ሆንን እንድናስብ አይፈቅድልንም። ይልቁንም፣ አዲስ ኪዳን የአንድ ቤተሰብ አባላት አድርጎ ነው የሚያስበን። ሁላችንም ወንድምና እኅት ነን። መሪዎችን የተለየ አክብሮት የሚያስፈልጋቸው ታላቅ ወንድም መሆናቸውን የሚሳይ ነገር የለም። ታላቅ ወንድማችን ኢየሱስ ነው። የተቀረነው ሁላችንም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆንም አልሆንም፣ ሁላችንም ወንድምና እኅት ነን። (ማቴ. 23:8ን ይመልከቱ።)

ረ. እግዚአብሔር ሰዎች እርሱን እንዲያገለግሉት ብዙ ዓይነት የፈጠራ ችሎታ ሰጥቷቸዋል። እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ዛፎችንና አትክልቶችን እንደ ሠራ ሁሉ፣ በእርሱ አምሳል

የፈጠራቸው ሰዎችም በፈጠራ ሥራቸው እግዚአብሔርን ሊያገለግሉ ይገባል:: እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ ልዩነት የምናመጣበትን ችሎታ ሰጥቶናል:: ይህ የፈጠራ ችሎታ አዳዲስ አገልግሎቶችን ለመጀመር ሊውል ይችላል:: ወይም ደግሞ መደረግ ያለበትን ሁሉ አድርገን ልናሻሽለው እንችላለን:: ሆኖም፣ ሰዎች ነገሮችን በሚገባ ተመልክተው እንዴት አዲስ አሳብ ይዘው እንደሚመጡ አልተማሩም:: ያንን የፈጠራ ችሎታ አናፍነዋለን:: ነገሮችን ባሉበት ሁኔታ እንድንቀበላቸው እንማራለን:: ወይም መሪዎች የመፍትሔ አሳብ እስከሚያመጡልን ድረስ እንድንጠብቅ እንማራለን::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ያለውን አገልግሎት ለማሻሻል ለሰዎች ይህንን ስጦታ እንደ ሰጠ ማወቅና አማኞች ለእግዚአብሔር ክብር የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙ ሊያበረታቱ ይገባል:: ጥበበኛ የሆነ መሪ አባላት የቤተ ክርስቲያን ራእይ የሚያሟሉ አዳዲስ አገልግሎቶችን እንዲሞክሩ ያበረታታል:: አባላት «ይህ አገልግሎት እንዴት ነው ሊሻሻል የሚችለው?» ብለው እንዲጠይቁ መሪው ሊያበረታታቸው ይገባል:: ሰዎች ያላቸውን ጸጋ በአዲስ መልክ እንዲጠቀሙ ከተበረታቱ፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አዳዲስና አስገራሚ ነገሮችን ያደርጋል:: ነገር ግን ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይቆጡናል ወይም ከአገልግሎት ያግዱናል ብለው የሚፈሩ ከሆነ፣ የፈጠራ ችሎታቸውን አይጠቀሙም:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሮች ባሉበት ስለሚቆዩ፣ አነስተኛ ለውጥ ብቻ ነው የሚመጣው:: ሰዎች ደግሞ ሁልጊዜ አዲስ ነገር በሚከሰትበት ቤተ ክርስቲያን ነው አባል ለመሆን የሚፈልጉት:: የፈጠራ ጠላት ልማዳዊ አሠራር ነው:: ነገሮችን በልምድ ስንሠራ፣ ስለ ዓላማውም ሆነ ስለ አሠራራችን ብዙ አናስብም:: ነገሮች ሁልጊዜ ተመሳሳይ ከሆኑ፣ ሰዎች ስሚሰለቻቸው ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳሉ:: እግዚአብሔርም ቤተ ክርስቲያኒቱ አዲስ እንደ ነበረችበት ጊዜ በኃይል አይሠራም::

6ኛ ጥያቄ:- ሀ) ባለፈው ዓመት እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናችሁ ምን ዓይነት አዳዲስ ነገሮችን አድርጓል? ለ) የቆየ አገልግሎት በአዲስ መልክ



የሚያገለግል አዲስ ሰው ሲመጣ ምን ያክል እንደ ተቀየረ እንዳየህ አብራራ:: ሐ) ለምንድን ነው በጣም ጥቂት የቤተ ክርስቲያን አባላት ብቻ በነጻነት እግዚአብሔርን አዲስ በሆነ መንገድ የሚያገለግሉት? መ) ለምንድን ነው እግዚአብሔርን ለማገልገል በራሳችን መንገድ ከመሄድ ይልቅ የሌሎችን አሠራር የምንኮርጀው? ሠ) የቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ሳያስፈቅዱ በሚኖሩበት አካባቢ እግዚአብሔርን በነጻነት ማገልገል የሚችሉበት አገልግሎት ማቋቋም ይችላሉ? ካልቻሉ፣ ለምን? ረ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልግ ሰዎች ማገልገል የሚችሉባቸውን አገልግሎቶች ዓይነት ዘርዝር:: ሰ) ሰዎች ከመጀመራቸው በፊት ለቤተ ክርስቲያን ማሳወቅ አለባቸው የሚሏቸው የአገልግሎት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ልዩነቱ ለምን ተከሰተ?

7ኛ ጥያቄ:- ኤፌ. 4:11-13ን አንብብ:: ሐዋርያው ጳውሎስ መሪዎች የእግዚአብሔርን ሥራ በማስፈጸም በኩል ያላቸው ሚና ምንድን ነው ብሎ ነው የሚያስተምረው?

2. መሪዎች ካሏቸው አስፈላጊ አገልግሎቶች መካከል የቤተ ክርስቲያን አባላት ያላቸውን የጸጋ ስጦታ እንዲረዱና እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ መርዳት ነው::

እግዚአብሔር አማኞች ሁሉ በጥንቃቄ እንዲያገለግሉት ይፈልጋል:: ነገር ግን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔር ሥራ ከባድ በመሆኑ፣ ምእመናን ሊሠሩት እንደማይችሉ ይታሰባል:: ስለዚህ ሽማግሌዎች፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢዎችና አስተማሪዎች ናቸው ሊሠሩት የሚገባው ተብሎ ይታሰባል:: የቤተ ክርስቲያን አባላት ሊያደርጉ የሚገባቸው ነገር መጸለይ፣ መዘመርና ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ደመወዝ ይሆናቸው ዘንድ ገንዘብ መስጠት ብቻ ነው ብለው ያስባሉ:: ዛሬ ዛሬ በርካታ በሥነ መለኮት ትምህርት የተመረቁና በቤተ ክርስቲያን ያለው ችግር የሚፈታው ሁሉንም አገልግሎቶች የሚያከናውን የሙሉ ጊዜ «መጋቢ» ሲኖር ነው ብለው የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ:: ካልተጠነቀቅን በስተቀር፣ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ በመቀጠሩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ትንሽ ብቻ እንዲያገለግሉ ለማድረግ ሰይጣን በምክንያትነት ሊጠቀምበት ይችላል:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት አገልግሎቶች ሙሉ ጊዜ

ያቸውን የሰጡ አገልጋዮች ኃላፊነት ነው ከሚለው መረዳት የተነሣ፣ በአብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጡ የጸጋ ስጦታዎች ያለ አገልግሎት ተቀምጠዋል፡፡ ጥቂት ሰ ዎች ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ሥራ ሁሉ ለመሥራት በጣም ይደክማሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ አገልጋዮች ምንም ያህል ተግተው ቢሠሩም፣ ሥራው እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ አይሠራም፡፡ ለምን?

ሀ. ምክንያቱም በእነዚህ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ውስጥ ያለው የጸጋ ስጦታ አንድ ጤነኛ ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት ከሚችለው ያነሰ በመሆኑ ነው፡፡ ሌሎች በርካታ የጸጋ ስጦታዎች በማያገለግሉ በርካታ የቤተ ክርስቲያን አባላት ውስጥ ያለ ሥራ ተቀምጠዋል፡፡

ለ. እነዚህ ጥቂት ሰዎች መደረግ ያለበትን ሁሉ ለመሥራት በቂ ጊዜ ሊኖራቸው ስለማይችል ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እኛ ብቻችንን ልናሟላ የማንችላቸው በርካታ አገልግሎቶች አሉ፡፡ ምክንያቱም ጥቂት ሠራተኞች ለብዙ ሥራ ጊዜ አያገኙም፡፡

ቤት መገንባት የሚቻልባቸው ሁለት መንገዶች አሉ፡፡ በከተማ ውስጥ ያሉ ቤቶች «በባለሙያ» ይሠራሉ፡፡ ግንበኞችና አናጢዎች ከጥቂት ረዳቶቻቸው ጋር በመሆን ቤቱን ለመሥራት ይተጋሉ፣ ነገር ግን ለማጠናቀቅ ወራት ይወስድባቸዋል፡፡ ነገር ግን በገጠር ያሉ ቤቶች የሚሠሩት «በተራው ሕዝብ» ሲሆን፣ ሁሉም ሰው ግን በሥራው ላይ ይሳተፋል፡፡ አንድ ሰው ጎጆ ቤት መሥራት ሲፈልግ፣ የአካባቢውን ሰው ሁሉ «ደቦ» ይጠራል፡፡ እያንዳንዱ ሰው አጠና፣ ገመድና ለጣራ ክዳን የሚሆን ሣር ያመጣል፡፡ ሁሉም ሰው በትጋት ይሠራል፡፡ ከእነርሱም መካከል ጣራውን እንዴት በጥሩ ሁኔታ ማስቀመጥ እንደሚቻል የሚያውቅ «ባለሙያ» ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሰው ስለሚሳተፍበት፣ በአንድና በሁለት ቀን፣ ጎጆዋ ተሠርታ ታልቃለች፡፡ መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ልክ እንደ ጎጆ ቤቱ እንደ ሆነ ልንረዳ ይገባል፡፡ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚሳተፉበት



ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን ሥራ በቀላል እና በተሻለ ሁኔታ መጨረስ ይችላል፡፡ መጋቢዎችንና ወንጌላውያንን የመሳሰሉ ባለሙያዎች መኖር ሂደቱን ለማምራትና ለመቆጣጠር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ሥው ሊሠራ የሚገባው በመላው የቤተ ክርስቲያን አባላት እንቅስቃሴና ተሳትፎ ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ ጥረታችንን በሁለት ዋነኛ ነገሮች ላይ ልናተኩር ይገባል፡-

ሀ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች ያላቸውን የጸጋ ስጦታ እንዲለዩ በማድረግና ለኢየሱስ አገልግሎትም ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሊያደርጓቸው ይገባል፡፡ ይህም በርካታ አስፈላጊ እርምጃ ዎችን ይጨምራል፡-

1) አማኞች ሁሉ የኢየሱስ ተከታዮች እንደ መሆናችን መጠን፣ በአገልግሎት ላይ ንቁ እንድንሆን እንደሚፈልግ ልንረዳ ይገባል፡፡ በሮሜ 12:1 ላይ እምነታችን የሚለካው ሕይወታችንን በሙላት ለእግዚአብሔር በመስጠታችን እንደ ሆነ ይነግረናል፡፡ ሰ ዎች እግዚአብሔርን የሚያሳስበው በኢየሱስ ማመን ወይም አለማመናችን ብቻ ያለመሆኑን ሊረዱ ይገባል፡፡ እግዚአብሔር የሚደሰተው በጸሎታችንና በዝማሬያችን ብቻም አይደለም፡፡ ወይም የሚፈልገው አስራት መስጠታችንን ብቻም አይደለም፡፡ እርሱ ሁለንተናችንን ነው የሚፈልገው፤ ጊዜአችንን፣ ገንዘባችንን፣ የተ ፈጥሮ ችሎታችንን እና የጸጋ ስጦታችንን ይፈልጋል፡፡ ይገለገልባቸው ዘንድ እነዚህን ሁሉ ልናስረክበው ይገባል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባላት ለእግዚአብሔር እና ለሕዝቡ አገልግሎት ራሳቸውን የሚሰጡት በመጀመሪያ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ከሰጡ ነው፡፡ ኢሳይያስ፣ «እነሆ፣ እኔን ላከኝ፣» ያለው እግዚአብሔ ር በጠራው ጊዜ ነበር (ኢሳ. 6:8)፡፡ ዛሬም በተመሳሳይ ሁኔታ፣ «እነሆ፣ እኔን ላከኝ፣» የሚለው ምላሽ የእያንዳንዱ አማኝ ልብ ፍላጎት ሊሆን ይገባል፡፡

2) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እያንዳንዱ አማኝ ከመንፈስ ቅዱስ የተሰጠውን የጸጋ ስጦታ እንዲያውቁ ሊረዱት ይገባል፡፡

መሪዎች የጸጋ ስጦታን ለአማኞች የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ ሊያስተውሉ ይገባል:: መሪዎች ምን መደረግ እንዳለበት መወሰን እና ሥራውን የሚፈጽም ሰው ሊሾሙ አይገባቸውም:: ወይም መሪዎች አባላቶቻቸው ለቤተ ክርስቲያናቸው «ጥቅል በሆኑ አገልግሎቶች» (ለምሳሌ፣ ሴቶች ቡና እንዲያፈሉና ምግብ እንዲያበስሉ በማድረግ፣ ምእመናን በቤተ ክርስቲያንና የቤተ ክርስቲያንን ንብረት እንዲያጸዱ በማድረግ) እንዲያገለግሉ እና ያም መንፈሳዊ ጸጋቸውን በጥሩ ሁኔታ መጠቀም እንደ ሆነ እንዲያስቡ ማድረግ አይገባቸውም:: የጸጋ ስጦታዎች እስቀድመው የታሰቡት የእግዚአብሔር እውነት ለዳኑትም ሆነ ላልዳኑት ለመግለጽ፣ እርስ በርስ በእምነት ለማደግ፣ የተቸገሩትን ለመርዳትና አምልኮን ለመሳሰሉት መንፈሳዊ ነገሮች ነው:: መሪዎች እያንዳንዱ አማኝ የጸጋ ስጦታውን ለይቶ እንዲያውቅና በሥራ ላይ እንዲያውል መርዳት ይገባቸዋል:: ያን ጊዜ ብቻ ነው የእግዚአብሔር አገልግሎት በኃይልና በበረከት የምትፈጽመው::

መሪዎች ስለዚህ ሂደት መረዳት እንዲኖራቸው የሚከተሉትን ሊያስታውሱ ይገባል:-

ሀ) መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎችን ይሰጣል (1ኛ ቆሮ. 12:7-11):: መሪዎች ለማንም መንፈሳዊ ስጦታ ሊሰጡ አይችሉም:: መሪዎች የፈለጉትን ሰው ለፈለጉት አገልግሎት የመሾም» መብት እንዳላቸው ሊያስቡ አይገባም:: ይልቁንም፣ በሰዎች ውስጥ ላለው የጸጋ ስጦታ «እውቅና ልንሰጥና» እና ያ ሰው የጸጋ ስጦታውን ለእግዚአብሔር ክብር እንዲጠቀምበት ልንረዳው ይገባል::

ለ) እግዚአብሔር ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን ያከብራል:: አንደኛ፣ በጸጋ ስጦታዎች መካከል ልዩነት አለ:: እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ላሉ ሰዎች በርካታ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ይሰጣል:: እግዚአብሔር ለክብሩ ልክ እንደ አገልግሎቶች ብዛት የሚሆን በርካታ የጸጋ ስጦታዎችን ሰጥቷል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች አንዱ የአንዱን የጸጋ ስጦታ ለመኮረጅ ከመሞከር ይልቅ፣ አንዱ የአንዱን የጸጋ ስጦታ እንዲያከብር ሊያበረታቱ



ይገባል:: ሁለተኛ፣ የጸጋ ስጦታ እጠቃቀም ችሎታም ይለያያል:: ለምሳሌ፣ መንፈስ ቅዱስ ለሁለት ሰዎች የማስተማር ስጦታ ሰጠ እንበል:: ነገር ግን የስጦታው ደረጃ ይለያያል:: አንዱ አነስተኛ ሰዎችን የማስተማር ስጦታ ያለው ሊሆን ይችላል፣ ሌላው ደግሞ በርካታ ሰዎችን የማስተማር ስጦታ ሊኖረው ይችላል::

ያ ማለት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እያንዳንዱን አባል ሊያውቁ ይገባል ማለት ነው:: መሪዎች እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ያለውን የጸጋ ስጦታ ካወቁ፣ የጸጋ ስጦታውን በስፋት መጠቀም በሚችልበት የአገልግሎት ዘርፍ ላይ ሊያስቀምጡት ይችላሉ:: በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አባላትን የጸጋ ስጦታ መጠንም ማወቅ አለባቸው:: መሪዎች አነስተኛ የማስተማር ስጦታ ያለውን ሰው ከችሎታው በላይ የሆነ ትምህርት እንዲሰጥ ሊያደርጉ አይገባም::

እማኞች በጣም አስደናቂ የጸጋ ስጦታ ባላቸው ሰዎች ላለመቅናት ሊጠነቀቁ ይገባል:: ያንን ማድረግ ለሰዎች የጸጋ ስጦታ ከሰጠው መንፈስ ቅዱስ ጋር መዋጋት ነው:: ማንም ሰው ባለው ገንዘብም ሆነ የትምህርት ደረጃ የጸጋ ስጦታ ሊያገኝ አይችልም:: ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚመጣ ስጦታ ነው::

ሐ) እግዚአብሔር በተራ ሰዎች አስደናቂ ነገር ማድረግ ያስደስተዋል:: የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ታሪክ በጣም አስገራሚ ነው:: እግዚአብሔር ተራ ወንዶችና ሴቶችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አስታጥቆ ነው ዓለምን እንዲለውጡ የተጠቀመባቸው:: (1ኛ ቆሮ. 1:18-31ን ይመልከቱ::) ያ አሠራር ዛሬ እኛ የአመራር ደረጃን ከምናይበት መንገድ በጣም የተለየ ነው:: ዛሬ ሰዎች እግዚአብሔርን በመሪነት ማገልገል ካለባቸው የተማሩ ባለሙያዎች መሆን እንዳለባቸው እናስባለን:: በዚህ መስፈርት መሠረት፣ ከጳውሎስ ውጪ ያሉት ሐዋርያት እዚህ ተመልሰው ቢመጡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊሆኑ አይችሉም! እግዚአብሔር ከተማሩ ሰዎች ይልቅ ባልተማሩ ሰዎች፣ ከሐብታሞች ይልቅ በድሆች፣ ከተከበሩ ጉሳዎች ይልቅ በተናቁ ሰዎች ትልቅ ነገር ማድረግ ይወዳል:: (ለምሳሌ፣ ሐዋርያት ሁሉ ከፈሪሳውያን ያነሰ ትምህርት

ነበራቸው)፣ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚያን ውጫዊ መስፈርቶች ልክ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አመልካቾች መውሰዳቸው የተሳሳተ ነው።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለምንድን ነው ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በቀድሚያ የሚሠራው በተማረ ሰው ነው ብለው የሚያምኑት? ለ) ከቤተ ክርስቲያናችሁ ታሪክ ተነሥተህ እግዚአብሔር መንግሥቱን ለማስፋፋት ከተማሩ ሰዎች ይልቅ እንዴት ተራና ያልተማሩ ሰዎችን ሲጠቀም እንዳየህ አብራራ። ሐ) ይህ እውነት ከሆነ፣ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መግባት ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስልሃል?

9ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንተ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነህ እንበል። በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉ አማኞች ያላቸውን የጸጋ ስጦታ እንዲያውቁና ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም እንዲያውሉት ምን ዓይነት ዕቅድ ትዘረጋለህ? ለ) እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል የጸጋ ስጦታውን ቢያውቅና በንቃት ቢጠቀምባቸው የቤተ ክርስቲያናችሁ አገልግሎት ምን ያህል እንደሚለወጥ ግለጽ?

ለ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ሁሉም ሰው ልዩ የሆነውን የጸጋ ስጦታውን እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል በሚችልበት መንገድ ሊያቅዱት ይገባል።

ጥቂት መሪዎች ብቻ ሁሉንም ሥራ የሚሠሩ ከሆነ፣ አብዛኛው የእግዚአብሔር አገልግሎት አይሠራም። መሪዎች እነርሱ ብቻ የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት እንዳለባቸው እና የቤተ ክርስቲ.ን አባላት እንደማይታመኑ የሚያስቡ ከሆነ፣ ያ የኩራት ምልክት ነው። እንዲህ ባለ መልኩ አገልግሎትን መረዳት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔር ሥራ ይጎዳል፣ ምክንያቱም ጥቂቶቹ መሪዎች ያላቸው ጥቂት ጊዜና ጥቂት የጸጋ ስጦታ ብቻ ስለሆነ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ካላቸው ዋነኛ ኃላፊነቶች መካከል የቤተ ክርስቲያን አባላትን ለአገልግሎት ማስታጠቅ ነው። በኤፌሶን 4:11-12 ላይ፣ ጳውሎስ ዋነኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች (ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌላውያን፣



ለባኪያን/አስተማሪዎች) በቀጥታ እግዚአብሔርን ከማገልገል ይልቅ ትኩረታቸውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አገልግሎት በማስታጠቁ ላይ እንዲያደርጉ ይመክራል። እርሱ ሁሉም የእግዚአብሔር ሰዎች በአገልግሎት ላይ በንቃት ሲሳተፉ፣ በቤተ ክርስቲያን ብስለት እንደሚመጣ ያብራራል። ሐዋርያው በመቀጠል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትኩረት በሁለት ነገሮች ላይ መሆን እንደሚገባቸው ይገልጻል፡-

1) የቤተ ክርስቲያን አባላት የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት እንዲችሉ ማሠልጠን። ምንም እንኳን መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ ዎችን ቢሰጥም፣ የጸጋ ስጦታዎችን በብቃት ለመጠቀም ሥልጠናና ቅንነት ያስፈልጋል። መንፈስ ቅዱስ ለአንድ ሰው ልዩ የምስክርነት ጸጋ ሊሰጠው ይችላል። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ሌላ እምነት ላላቸው ሰ ዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመመስከር ሥልጠናና ዕውቀት ያስፈልጋል። ያ ደግሞ ትክክለኛ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ማወቅን ይጠይቃል። የጸጋ ስጦታዎች ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲሠሩ ካስፈለገ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥልጠና የመስጠት ሚና መጫወት አለባቸው።

2) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አባላት ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ሊለቅቋቸው ይገባል። ያ ማለት የቤተ ክርስቲያን አባላት ልዩ ወደ ሆነ አገልግሎት እንዲገቡ መሪዎችና የቤተ ክርስቲያን አባላት በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ወይም ደግሞ መሪዎች አንድን አባል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩ የሆነና በቀጥታ ከመሪ ዎች ቁጥጥር ሥር ባልሆነ አገልግሎት ውስጥ መግባት እንዲችል መጸለይ እንዳለበት ሊያበረታቱት ይገባል። የቤተ ክርስቲያን አባላት ሊያገለግሉት ሲፈልጉ፣ እግዚአብሔር ጠቃሚ ወደ ሆኑ አገልግሎቶች እንዲሰማሩ በአስደናቂ ሁኔታ በመምራት ሥራውን ይፈጽማል።

አንድ ሰው ከዳነ በኋላ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ከመሰማራቱ በፊት ለዓመታት ከመጠበቅ ይልቅ፣ አዳዲስ አማኞችን የጸጋ ስጦታቸውን ቶሎ እንዲለዩ ማድረግና እንዲያገለግሉ ማስቻል ያስፈልጋል። አንድ ጊዜ ቸልተኝነትን ከተ

ማሩ በኋላ፣ ልማዳቸውን መቀየርና ወደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መምጣት ይከብዳል። አዳዲስ አማኞች መንፈሳዊ ቅናታቸው በጣም ጠንካራ በሆነበት ወቅት ማገልገል ከጀመሩ፣ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ውጤታማ አገልጋዮች ይሆናሉ።

እንድ ቤተ አምነት፣ እዳዲስ እማኞች ኢየሱስን መከተል ምን ማስት እንደ ሆነ የሚገልጸውን የመጽሐፍ ቅዱስና የቅድመ-ጥምቀት ትምህርት ከወሰዱ፣ አማኞች ወደ እገልግሎት ዘርፎች ይላካሉ። ለምሳሌ፣ እንድ የምስክርነት ጸጋ ያለው ሰው የወንጌል ምስክርነት ስጦታ ካላቸው ሰዎች ጋር እንዲመደብ ይደረጋል። ስተ ወስነ ጊዜ ከቡድኑ ጋር በወንጌል ስርጭት ላይ ይሠራል። የወንጌል ስብከት ጸጋ እንዳለው ካሳየ፣ ከዚያ ቡድን ጋር ማገልገሉን ይቀጥላል። ለቡድኑ አባላት እርሱ የወንጌል ስብከት ጸጋ እንደሌለው ግልጽ ከሆነላቸው፣ የማስተማር ጸጋ ካለው ቡድን ጋር እንዲቀላቀል ይደረጋል። በዚህ መንገድ፣ አንድ አማኝ ከአዲስነቱ ጀምሮ ልዩ ልዩ እገልግሎቶችን እንዲሞክር በማድረግ የጸጋ ስጦታውን እንዲለይ ያደርጋሉ። እንድ ጊዜ የጸጋ ስጦታው ከታወቀ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጸጋ ስጦታውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጠቀም እንዲችል ሥልጠና ይሰጡታል።

እያንዳንዱ አባል በአገልግሎት ውስጥ በንቃት ሲሳተፍ እጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ኃይል ሊኖራቸው እንደሚችል አስቡ። ያን ጊዜ ወንጌል ለመስበክና ለጠፉት ለመመስከር የሚችለው ቤተ ክርስቲያን የቀጠረችው አንድ ወንጌላዊ ብቻ አይሆንም። ይልቁንም፣ እምነታቸውን በንቃት የሚያካፍሉ በመቶ የሚቆጠሩ ጸጋን የተሞሉ ሰዎች አሉ። በተቀበሉት የጸጋ ስጦታ ወጣቶችን ብቻ ሳይሆን፣ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን እባላት ያስተምራሉ። ጥቂት መሪዎች አገልግሎቶችን ሁሉ ለማስተባበር ከመሞከር ይልቅ፣ ሠላሳና አርባ የሚሆኑ ሰዎች የእረኝነት ሥራን ሊሠሩ ይችላሉ። የቤተ ክርስቲያን ጥንካሬ በውስጣቸው ያለውን መንፈሳዊ ጸጋ በብቃት በሚጠቀሙ በመቶዎች የሚቆጠሩ የቤተ ክርስቲያን እባላት ይወሰናል። የአግዚአብሔር እሠራር በርካታ ሰዎች



በፈቃደኝነት እንዲያገለግሉት ማድረግ ነው። በእኛ ቤተ ክርስቲያን ያ ሆኗልን?

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ ወንጌላውያን፣ እና መጋቢዎች አገልግሎት ትኩረት በቀጥታ ከማገልገል ይልቅ በይበልጥ የቤተ ክርስቲያን አባላትን ለአገልግሎት ማስታጠቅ ላይ ቢያተኩር ምን ያህል አገልግሎታቸው ይቀየር እንደ ነበረ አብራራ። ለ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ ወንጌላውያን፣ እና መጋቢዎች የቤተ ክርስቲያን አባላት ሊሠማሩባቸው የሚገባቸው የአገልግሎት በሮች ክፍት እንዲሆኑ ምን ማድረግ ይገባቸዋል? ሐ) በትምህርት መስፈርት መሠረት የአንዲት ጤነኛ ቤት ክርስቲያንን ዋና አካላት ቃኝ። በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉ እገልግሎቶች በበቂ ሁኔታ እንዲሟሉና ቤተ ክርስቲያናችሁ እንድታድግ ሊያደርጉ የሚችሉ ዝርዝሮችን አብራራ። |

3. ቤተ ክርስቲያን እባላቶቿ መንፈስ ቅዱስን ስምተው ያለ ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረድ እግዚአብሔርን ሊያገለግሉ የሚችሉበትን የአመራር መዋቅር ማዘጋጀት አለባት።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን ራሳችንን፣ «የትኛው ዓይነት የመሪነት መረዳት ነው ሁሉንም የቤተ ክርስቲያናችንን አባላት እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ የሚያደርገው?» ብለን ልንጠይቅ ይገባል። ምን ዓይነት አስተ ዳደራዊ መዋቅር በቤተ ክርስቲያናችን ብንዘረጋ ነው የቤተ ክርስቲያናችን አባላት በሙሉ እግዚአብሔርን ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊያገለግሉ የሚችሉት?» ብለን ልንጠይቅ ይገባል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን እባላትን ከመቆጣጠርና አገልግሎታቸውን ከመገደብ ይልቅ፣ ይህ ጥያቄ የቤተ ክርስቲያንን የአመራር መዋቅር ለማዘጋጀት አባላትን በየእገልግሎቱ ለማሰማራት እንዲችሉ ሊመራ ያስፈልጋል። የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች በሚከተሉት ሦስት መስፈርቶች የቤተ ክርስቲያናቸውን መዋቅር ሊፈትሹ ይገባል፡-

ሀ. ሰዎች እርስ በርሳቸው ያላቸው ግንኙነት እንዲጠናከር ይ ረዳል ወይ? እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን «እካል» ነው የሚለው። አካል እንዲሠራ ደግሞ፣ ሁሉም የሰውነት ክፍል

በአንድነት ሊሠራ ይገባል። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ የሚተዋወቁበትና ግንኙነታቸው እየተጠናከረ የሚሄድበት ነው። ብዙ የማይታወቁ ሰዎች ካሉ ወይም አንዱ ለአንዱ እንግዳ የሆነበት ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ልትሆን አትችልም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ እንድትሆን ነው የሚፈልገው፣ በማኅበረሰቡም ውስጥ አንዱ አንዱን የሚያገለግልበት የጸጋ ስጦታ አለ።

ለ. የአስተዳደር መዋቅራችን ሰዎች መንፈስ ቅዱስን እንዲሰሙና በሰጣቸው የጸጋ ስጦታ በልዩ መንገድ እንዲያገለግሉ የሚረዳ ነውን? መዋቅሩ የቤተ ክርስቲያን አባላት መሪዎችን በጣም እንዲሰሙ የሚያደርግ ወይም ጥቂት የቤተ ክርስቲያን አባላት የአገልግሎትን ሥራ እንዲሠሩ የሚያደርግ ከሆነ፣ የአባላትን መንፈሳዊ ዕድገት ይገድባል። እያንዳንዱ አባል መንፈስ ቅዱስ አለው። እያንዳንዱ አባል በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ «ካህን» ነው። እያንዳንዱ አባል የራሱ የሆነ የጸጋ ስጦታ ተሰጥቶታል። መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት ያውቃል። ስለዚህ የአስተዳደር መዋቅራችን ሰዎች መንፈስ ቅዱስን እንዲሰሙ የሚያስችል መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን ምንም ዓይነት የአመራር መዋቅር ቢኖራትም፣ አማኞችን በመሪው ፍላጎት «ከመቆጣጠር» ይልቅ ይህንን እውነት ልታከብር ይገባል።

ሐ. የአመራሩ መዋቅር ብዙ ሰዎች መንፈሳዊ ባሕርይ እንዲኖራቸውና በልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች ሌሎች ሰዎች እግዚአብሔርን በመምሰል እንዲያድጉና እርሱን እንዲሰሙ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ ያስችላል ወይ? እግዚአብሔር በማንኛውም የአሠራር መዋቅር ይሠራል፣ ነገር ግን መሪዎች አገልግሎታችን ፍሬያማ እንዲሆን የሌሎች ድጋፍ እንዲያስፈልገን ልናውቅ ይገባል። መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያስፈልገውን አገልግሎት ሁሉ ሊሰጡ አይችሉም። እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች፣ አመለካከቶችና ልምዶች ያላቸው በሳል አማኞች በአንድነት እንዲሠሩለት ይፈልጋል። እነዚህ በሳል



አማኞች ባላቸው የጸጋ ስጦታ እርስ በርስ ያገለግላሉ፣ አንዱ የአንዱን ጸጋ ያከብራል።

> 11ኛ ጥያቄ፡- ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት መስፈርቶች በመጠቀም፣ በቤተ ክርስቲያናችሁ ያለውን የአመራር መዋቅር ፈትሽ። ሀ) ውጤታማ በሆነ መንገድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን እንዲሰሙና ራስ የሆነውን ኢየሱስን እንዲያገለግሉ ያስችላል ወይ? ለ) እነዚህ ሦስት መስፈርቶች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እንዲሠሩ ምን ዓይነት የአስተዳደር መዋቅር ወይም የመሪነት መረዳት ሊቀየር ይገባል?

ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች በአንድነትና በስምምነት የሚሠሩባት አካል እንደ ሆነች አስተምሯል። (1ኛ ቆሮ. 12:12-30ን ይመልከቱ።) አካላችን በአስገራሚ ሁኔታ የሚሠራው ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍሎቻችን በጋራ ውጤታማ በሆነ መንገድ ስለሚሠሩ ነው። በቤተ ክርስቲያንም እንደዚሁ ነው። ቤተ ክርስቲያን ወደ ሙሉ አቅሟ የምትደርሰው የተለያዩ ሰዎች በጋራ ሆነው እንደ አንድ ቡድን በመሥራት እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ዓላማ ሲፈጽሙ ነው።

## በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሦስት ዓይነት ቡድኖች

1. በሆነ ጉዳይ ወይም አገልግሎት ላይ የሚነጋገርና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሳብ የሚያቀርብ ጊዜያዊ ቡድን ይቋቋማል። ብዙ ጊዜ የተወሰኑ ሰዎች ውስብስብ በሆኑ ጉዳዮችና አገልግሎቶች ላይ በጥንቃቄ ተወያይተው እንዲህ ቢሆን ጥሩ ነው ብለው ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሳብ የሚያመጡበት አሠራር ጥሩ ነው። ሥራ የሚበዛባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስፈላጊ በሆኑ እንደ አካባቢያዊ የወንጌል ስብከትና የቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ወደ ብስለት ሊያመጡ በሚችሉ ትምህርቶች አሰጣጥ ባሉ ጉዳዮች ላይ ወይም በአካባቢያቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መክፈትን በተመለከተ ለመወያየት በቂ ውይይት የሚያደርጉበት ጊዜ የላቸውም። ስለዚህ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የመፍትሔ አሳብ የሚያቀርብ በጥንቃቄ የተመረጡ ሰዎች ያሉበት ኮሚቴ ማቋቋም ተመራጭ ነው።

2. የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ወይም የቦርድ አባላት ልክ እንደ አንድ ቡድን መሥራት አለባቸው:: የሽማግሌዎች ቦርድ ውጤታማ የሚሆነው እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያናቸው የሚጠብቀውን ነገር ለመፈጸም በቡድን በአንድነት ሲሠሩ ነው:: በቡድን ውስጥ ሆነው «የግል» አሳባቸውን ብቻ የሚያራምዱ ከሆነ ግን፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት በርካታ ነገሮችን ለመፈጸም ያላቸው ችሎታ ይገደባል::

3. የአገልግሎት ቡድን:- እነዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ የአገልጋዮች ቡድን (ለምሳሌ፣ የወንጌላውያን ቡድን፣ የደቀ መዛሙርት ቡድን፣ የሰንበት ት/ቤት አስተማሪዎች ቡድን) ወይም ደግሞ የተወሰኑ አገልግሎቶችን የሚቆጣጠሩ መሪዎች ቡድን (ለምሳሌ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሚቴ፣ የወንጌላውያን ኮሚቴ፣) ሊሆኑ ይችላሉ::

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ስላሉ አገልግሎቶች አስብ:: ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች በእውቀት የዳበረና የተሻለ ውሳኔ እንዲወስኑ ለመርዳት ምን ዓይነት ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ናቸው የሚቋቋሙት? ለ) በተቋቋመው ቦርድ ውስጥ ሽማግሌዎቹ የሚንቀሳቀሱት እንደ ቡድን ነው ወይስ እንደ ግለሰብ? መልስህን አብራራ:: ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ያሉትን ዋና ዋና አገልግሎቶች ዘርዝር:: እነዚህ አገልግሎቶች የሚመሩት በአገልግሎት ቡድን ነው ወይስ በአንድ ግለሰብ? በአንድ ግለሰብ የሚመሩ ከሆነ፣ በቡድን ቢመሩ ምን የተሻለ ውጤት ይኖራል ብለህ ታስባለህ? |

## ሁለተኛ ቀን

## ውጤታማ የሆነ ቡድን መሠረታዊ እውነቶች

ቡድኑ የሽማግሌዎች ቡድን፣ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ቡድን፣ ወይም በበጎ ፈቃደኞች የተውጣጡ አባላት ቡድን ሊሆን ይችላል:: በቡድን መሥራት ከቻሉ አንድ ግለሰብ በግሉ ሊሠራ ከሚችለው በላይ ውጤታማ ይሆናሉ:: የሚከተሉት ነጥቦች በቡድን የመሥራትን ጠቀሜታ የሚያሳዩ ናቸው::



1. ትልቅ የፈጠራ ውጤት የሚመጣው ሰዎች በቡድን ሲሠሩ ነው:: *የቡድን ሥራ ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አእምሮአቸውን፣ ጉልበታቸውንና ተሰጥኦአቸውን በአንድ ግብ ላይ የሚያውሉበት ነው::* ለብቻችን ስንሠራ፣ ሥራው በእኛው እውቀት ላይ ብቻ ይገደባል:: በትምህርታችን፣ በልምዳችን፣ በእውቀታችን፣ በጸጋ ስጦታችን፣ ወዘተ. . . ሊገደብ ይችላል:: ነገር ግን ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ በምንሠራበት ወቅት፣ ለብቻችን ከምንሠራው በላይ ውጤታማ እንሆናለን:: ምክንያቱም ከሌሎች ሰዎች እውቀት፣ ልምድና ከጸጋ ስጦታቸውም ብዙ ስለምንጠቀም ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ከበርናባስ ወይም ከሲላስና ከጢሞቴዎስ ጋር በቡድን ለወንጌል ሥራ ይወጣ የነበረው ለዚህ ነው:: መሪዎች፣ ከተቻለ፣ አባሎቻቸው ውጤታማ ሥራ እንዲያከናውኑ በቡድን ቢያጣምሯቸው መልካም ነው::

ሰዎች በአንድ ቢሮ ውስጥ ስለ ሠሩ ብቻ ቡድን ላይሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን፣ አንድ ቡድን ማለት ለአንድ የጋራ ዓላማና ተልዕኮ አብረው የሚሠሩ ሰዎች ስብስብ ነው:: ለምሳሌ፣ «የወንጌላውያን» ቡድን ሊኖረን ይችላል:: ስለዚህ በዚህ ቡድን ውስጥ ያሉ አባላት ሁሉ ዓላማና ግባቸው ለአካባቢያቸውና ለሌሎችም ወንጌልን መስበክ ነው:: ወይም ደግሞ የአስተማሪዎች ቡድን ቢኖር፣ የሁሉም ዓላማ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በእግዚአብሔር ቃል እውቀት የሚያድጉባቸውን መንገድ መፈለግ ሊሆን ይችላል::

አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ባልደረቦቹ በጋራ ሊሠሩ የሚችሉትና አንድ ሊያደርጋቸው የሚችል ግብ አለ ብሎ ካመነ በቡድን ሊያደራጃቸው ይችላል:: ለምሳሌ፣ መሪው፣ ጸሐፊው፣ የወንጌል ሰባኪትና የሥልጠና መሪዎች ተሰብስበው «የአካባቢያችንን ሕዝብ በወንጌል ለመድረስና አማኞችን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ ምን ማድረግ አለብን?» ብለው በማለብ በአንድነት በቡድን ሊሠሩ ይችላሉ:: ወንጌላዊው እንዴት ወንጌልን ላልዳኑት ማዳረስ እንደሚቻል ያለውን እውቀት ሊያካፍል፣ አሠልጣኙ ደግሞ ሰዎች እምነታቸውን እንዴት በተሻለ ሁኔታ

መመስከር እንደሚችሉ መንገዱን ያሳያል። ጸሐፊዋ ደግሞ ነገሮች ስኬታማ በሆነ መንገድ እንዲጠናቀቁ የማስተባበር ችሎታዋን ልትጠቀምበት ትችላለች።

**2. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁለት ዓይነት ቡድን ሊመሠርቱ ይችላሉ።**

ሀ. አንድን ጉዳይ በጥልቀት ተመልክቶ ለውሳኔ ሰጭዎች የውሳኔ አሳብ የሚያመነጭ ቡድን ሊኖር ይችላል። እንዲህ ዓይነት ቡድኖች በይበልጥ የሚያስፈልጉት አዲስ አገልግሎት ስንጀምር ነው። ያ ቡድን አገልግሎት ሊጀመር የሚችልባቸውን መንገዶች አጥንቶ ለሽማግሌዎች ሊያቀርብ ይችላል። ቡድኑ የሚደርስበት የመፍትሔ አሳብ ሽማግሌዎች ለሚሰጡት ውሳኔ መሠረት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፣ አንድ ጊዜያዊ ቡድን ቤተ ክርስቲያን አጸደ ሕጻናት ብትከፍት ጥሩ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን አሳብ ያጠናል። ጊዜያዊው ቡድን የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግሎት ሊገመግም ይችላል። ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የትምህርት አገልግሎቱን ገምግሞ ሊሻሻሉ ይገባቸዋል በሚላቸው ላይ አሳቡን ሊሰነዝር ይችላል።

ለ. በጥናቱ ውጤት መሠረት አገልግሎት የሚያስጀምሩና የሚያስኬዱ <u>አስፈጻሚ ቡድኖች</u> አሉ፡ ስለዚህ፣ አንድ ጊዜያዊ ቡድን የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ሊያዘጋጅ ይችላል። ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የትምህርት አገልግሎት በቋሚነት የሚከታተል ቡድን ማቋቋም ይቻላል።

3. ቡድኑ የሚገነባው የተለያየ ሥልጠናና የጸጋ ስጦታ ባላቸው ሰዎች ነው። ለብቻችን ስንሠራበት ጊዜ፣ ጥንካሬአችን በድካማችን ይገደባል። ነገር ግን የተለያየ ጸጋ ያላቸው ሰዎች በቡድኑ ውስጥ ሲሠሩ፣ የእነርሱ ጥንካሬ የሌሎችን ድክመት ይሸፍናል። ለምሳሌ፣ በወንጌል ስርጭት ላይ ጥሩ ብንሆንና የዳኑትን በማስተማሩ ላይ ደካማ ብንሆን፣ ወንጌል ሰምተው የዳኑት ሰዎች ወደ ዓለም ስለሚመለሱ ሥራችን ዋጋ አይኖረውም። የምንደክምባቸውን ነገሮች ለመሸፈን በዚህ ረገድ ጥንካሬ



ያላቸው ሰዎች ያስፈልጉናል። ስለዚህ፣ አንድ ወንጌላዊ ውጤታማ ለመሆን የግድ የዳኑትን የሚያስተምር ሰው ያስፈልገዋል።

4. ሰዎች መሾም ያለባቸው በሚፈልጉትና የጸጋ ስጦታ ባላቸው አገልግሎቶች ላይ መሆን አለበት። ምንም እንኳን ሁሉም ሰው በሚደክምበት ቦታ ላይ ሊሻሻል ቢገባውም፣ የምናገለግለው በማንደሰትበት አቅጣጫ ከሆነ፣ ደካሞችና ፍላጎት-አልባ ነው የምንሆነው። አንድን ወንጌላዊ አስተዳዳሪ ብናደርገው፣ ምናልባት በአጋጣሚ ጥሩ አስተዳዳሪ ሊወጣው ይችል ይሆናል። ነገር ግን ተ ሰጥኦ ከሌለው፣ በሥራው ላይደሰትና በአስተዳደሩም ሰዎች ላይረኩ ይችላሉ። ሰዎች ትኩረት መስጠት ያለባቸው እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ ላይ መሆን አለበት። ያን ጊዜ እያንዳንዱ ሰው የተ ሻለ ሥራ ሲሠራና እግዚአብሔርም ሥራውንና ጥረቱን ሲባርክ ይመለከታል።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰዎች ያለ ጸጋ ስጦታቸው አገልግሎት ተሰጥቷቸው ሊደክሙ አይተህ ታውቃለህ? ውጤቱ ምን የሚሆን ይመስልሃል? በአገልግሎታቸው ላይ የሚመጣው ውጤት ምንድን ነው? ለ) ይህ ሰ ዎችን ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ጸጋ መሠረት እንዲያገለግሉ ስለ ማድረግ ምን ያስተምራል? |

5. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አባላቶቻቸውን ለቡድን ሥራ ሲመርጡ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል።

የአንድ ቡድን ውጤታማነት የሚለካው ትክክለኛውን ሰው በትክክለኛ ቦታ ላይ በማስቀመጥ ነው። ወጥ በምንሠራበት ጊዜ፣ እያንዳንዱን ነገር በትክክለኛ መጠን ስናደርግ ነው ወጡ ሊጣፍጥ የሚችለው። ነገር ግን ሴትዮዋ ወጥ በምትሠራበት ጊዜ ትክክለኛ ያልሆኑትን ቅመማ ቅመሞች ወጡ ውስጥ ብትጨምር፣ ወጡ ላይጣፍጥ ይችላል። በተመሳሳይ መንገድ፣ አንድ ቡድን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲሠራ ካስፈለገ፣ አባላቱ ሁለት መመዘኛዎችን መሠረት በማድረግ በጥንቃቄ መመረጥ አለባቸው:-

ሀ. የቡድኑ አባላት በጥንቃቄ መመረጥ ያለባቸው ባላቸው <u>ብቃትና</u> ለአገልግሎቱ ባላቸው <u>መስጠት</u> ነው። አባላቱ በጥንቃቄ ካልተመረጡ፣ ጥረታቸው ጥሩ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም። ይህ

ሊሆን መሪው የጠበቀውን ውጤት አያገኝም። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የማያውቅና በአመራር ያልሠለጠነ ሆ ሳለ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ኮሚቴ አባል አድርገን ብንሾመው፣ ቡድኑን እንዴት ሊጠቅም ይችላል? ብዙውን ጊዜ ይህንን ሥራ ሊሠሩ የሚችሉትን ሰዎች ተስፋ ያስቆርጣል፣ ወይም ሰውዬው ስለ አመራር ሥልጠና ምንም ፍላጎት ከሌለው፣ ኮሚቴው ጠንክሮ ሳይሠራ ይችላል።

ለ. የቡድኑ አባላት አንዱ የሌላውን አመለካከት የሚያከብርና ተመጣጣኝ አባላት ያሉት ሊሆን ይገባል። ስለዚህ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን አገልግሎቶች የሚቆጣጠረው ቡድን በመጽሐፍ ቅዱስ የሠለጠኑ አባላትና በተለያዩ አቅጣጫዎች ነገሮችን የሚመለከቱ ወንዶችና ሴቶች ያስፈልጉታል።

ሐ. ሰዎች ያለ ሰፊ ልዩነት መሥራት እንዲችሉ የቡድኑ አባላት ግብና አስተሳሰብ ሊቀራረብ ይገባል። ሰዎች መሆን አለበት ብለው የሚያምኑት ነገር ከሰፋ፣ ከሌሎች ጋር አብረው ለመሥራት ሊቸገሩ ይችላሉ። ነገር ግን በቡድኑ ውስጥ ያላቸው ራእይ ተመሳሳይ ከሆነ፣ ከስኬት ላይ ለመድረስ አብረው ሊሠሩ ይችላሉ። ስለዚህ ለወንጌል ስርጭት ጉጉት ያለው ሰው ለመዘምራን ቡድን አባላት ልብስ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት የሚጥር ኮሚቴ ውስጥ መግባት የለበትም።

መ. ምንም እንኳን አንድ ቡድን በጋራ ለመሥራት በቂ የሆነ የጋራ አመለካከቶች ቢያስፈልጉትም፣ ቡድኑ ውጤታማ ለመሆን ከተለያየ ልምድና አመለካከት የተውጣጡ አባላት ያስፈልጉታል። በአንድ ቡድን ውስጥ ሁለት ሰዎች አንድ ዓይነት አመለካከት ካላቸው አንዳቸው አያስፈልጉም። ምክንያቱም አንዳቸው አዲስ አሳብ ካላመጡ ወይም የተሻለ ዕቅድ ካላመጡ አይጠቅሙም።

ሠ. እያንዳንዱ የቡድኑ አባላት በቡድኑ ውስጥ ለማገልገልና ጊዜውና ጉልበቱን ለማፍሰስ ፈቃደኛ መሆን አለበት። የቡድኑ አባል ለቡድኑ ዓላማ ካልተሰጠ፣ ብዙ ጊዜ አይመጣም፣ ለቡድኑ ምንም ዓይነት ጥረት አያደርግም። አንድ ሰው የድርሻውን



የማይወጣና በስብሰባዎች ላይ ለመገኘት ጊዜ ከሌለው፣ በቡድኑ ውስጥ ሊካተት አይገባም። አንዳንድ አባላት የማይገኙና የድርሻቸውን የማይወጡ ከሆነ፣ ሌሎች የቡድኑን አባላት ተስፋ ያስቆርጣሉ። የቡድኑ አባላት የሚገኙት መሪው እንዲካፈሉ ስላስገደዳቸው ከሆነ፣ ጥራት ያለው ዕቅድ ላያወጡ ይችላሉ።

> 14ኛ ጥያቄ፦ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ «የወንጌል ስርጭት» ቡድን ልታቋቁሙ ነው እንበል። ሀ) በዚያ ቡድን ውስጥ ማን ማን ይካተታል? ለ) ለምንድን ነው እነዚህን ሰዎች የምትመርጣቸው? ሐ) ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች እንዴት ነው የሚያሟሉት?

6. ቡድኑ ጠቃሚ ይሆን ዘንድ እያንዳንዱ ቡድን በጋራ መሥራት አለበት።

የተወሰኑ ሰዎችን በአንድ «ቡድን» ውስጥ አደረግን ማለት እንደ አንድ ቡድን ይሠራሉ ማለት አይደለም። አብዛኞቹ ኮሚቴዎች ወይም ቦርዶች አንድ ላይ የሚሠሩ ብዙ «ግለሰቦች» ሆነው ነው ሥራ የሚጀምሩት። ልክ እርስ በርስ የማይተዋወቁ አዳዲስ የእግር ኳስ ተጫዋቾች እንዳሉበት ቡድን ነው የሚመስሉት። ለማሸነፍ ተስፋ ስለሚያደርጉ፣ ሁሉም ለማሸነፍ የግል ችሎታቸውን ይጠቀማሉ። አንድ የእግር ኳስ ቡድን ጥሩ ቡድን ለመሆን እንዲቀናጅ ካስፈለገ፣ የእያንዳንዱ የቡድን አባላት ችሎታን ማቀናጀት ያስፈልጋል። የግል ችሎታቸው አነስተኛ ቢሆንም በጥሩ ሁኔታ ተቀናጅተው የሚሠሩ ሰዎች፣ ሁልጊዜም ቢሆን በግላቸው በጣም የተሻለ ችሎታ ያላቸውና ነገር ግን ያልተቀናጁ ሰዎችን ቡድን ያሸንፋሉ።

የሚከተሉት እውነታዎች ሰዎች በቡድን ውጤታማ ሥራ እንዲሠሩ ያስችላሉ።

ሀ. እያንዳንዱ ቡድን ወዳሰበበት ዓላማ ለመድረስ የግድ አንድ የቡድን መሪ ያስፈልገዋል። የቡድኑ መሪ የመሪነት ድርሻውን በሚገባ መረዳት አለበት።

1) መሪው ራሱን በተመለከተ ውሳኔዎችን ሁሉ መወሰን ያለበት እርሱ እንደ ሆነ ሊያስብ አይገባም። ራሱን ማየት ያለበት

ቡድኑ ጥሩ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ እንደሚያደርግ አስተባባሪ ነው:: ጥሩ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ መንገዶችን ለማሳየት ለዎች ጉዳዩን በተለያየ አቅጣጫ እንዲያዩት ሊያደርጉ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማንሣት የተሻለ ውሳኔ እንዲወሰን ያደርጋል።

2) የቡድን መሪው ሁሉም የቡድኑ አባላት የጸጋ ስጦታቸውንና ችሎታቸውን በመጠቀም በግል የሚደክሙበትን አቅጣጫ በሌሎች ጥንካሬ መሸፈን በሚችልበት ሁኔታ ሊመራቸው ይገባል:: የቡድኑ መሪ ቡድኑን ለግል ክብራቸው ሊሉ ስብሰባው ላይ በክፋት በመናገር የሌሎች ለምች አሳብ እንዳይሰማና ቦታ እንዳያገኝ በማድረግ ቡድኑን ከሚያዳክሙ ሰዎች ሊጠብቅ ይገባል። የተለያዩ አመለካከቶች ሊፈጠሩ ጎጂ የሆኑ ግጭቶች እንዳይከሰቱ ሊገድብ ይገባል።

3) የቡድኑ መሪ እንዲህ ዓይነት ውሳኔ ላይ መድረስ አለባችሁ ከሚሉ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና የቡድኑ አባላት ካልሆኑ ለዎች መጠበቅ አለበት:: ለቡድኑ አሳብ መስጠት የሚፈልጉና የቡድኑ አባላት የሚወያዩባቸውን ነገሮች ማወቅ የሚፈልጉ ለዎች ካሉ ከመሪው ጋር ሊነጋገሩ ይችላሉ:: የቡድኑ አባል ያልሆኑ ሰዎች በራሳቸው አመለካከት በውሳኔው ላይ ተጽዕኖ ለማድረስ የሚሞክሩ ክሆነ፣ ውጤቱ አፍራሽ ነው የሚሆነው።

4) የቡድን መሪው በቡድኑ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ኃላፊነቱን እንዲረዳና ድርሻውን እንዲወጣ ኃላፊነት መስጠት አለበት:: ቡድኑ ውጤታማ እንዲሆን እያንዳንዱ አባል የሚከተሉትን ማከናወን አለበት።

ሀ) ነገሮች ያለ ችግር እንዲከናወኑ ማስተባበር:- አንድ ቡድን የሚያካሂዳቸው ስብሰባዎች እንዲሳኩ አንደኛው የቡድኑ አባል ወንበሮችን ማስተካከል፣ ጠመኔ፣ ወረቀትና እስክሪብቶ ማዘጋጀት፣ አስፈላጊ የሆኑትን ለዎች መጋበዝ፣ ቀደም ሲል የተካሄዱ ስብሰባዎች የተመዘገቡበትን ማስታወሻ ማቅረብ፣ ወዘተ. . . ይጠበቅበታል:: ነገሮችን በጥሩ ሁኔታ የሚያቀናጅ ሰው ከሌለ፣ ጥሩ ውይይትም ሆነ ጥሩ ውሳኔ ሊኖር አይችልም።



ለ) ለውይይት የሚያነሣሣና አስተያየት የሚሰጥ ሰው:- የዳበረ ልምድ ያለውና ለስብሰባው መነሻ የሚሆኑ መረጃዎችን ሊያቀርብና ቡድኑ በየት በኩል ቢሄድ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ሊያሳይ የሚችል ሰው ቢኖር ይመረጣል፤ ወይም የጉዳዩን ታሪክ በሚገባ ሊተነትንና የተሻለ የመፍትሔ አሳብ ሊሰጥ የሚችል ልዩ እንግዳም መጋበዝ ይቻላል:: ከባዶ ከመነሣት፣ አንድ ሰው ከሚያነሣው አሳብ መጀመር ይሻላል:: ነገር ግን ያ ሰው አሳብ እንዳቀረበ ብቻ ነው ሊያስብ የሚገባው:: ቡድኑ ያንን እንደ መነሻ አድርጎ በመውሰድ መቀየር ያለባቸውን ነገሮች ሊቀይር ይችላል።

ሐ) ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ:- ብዙውን ጊዜ አንድ ቡድን ሲገናኝ ትክክለኛ መረጃ አይያዝም:: ለውይይቱ እንዲረዳ አባላት ትክክለኛ መረጃ ይዘው መቅረብ አለባቸው።

መ) በአባላት መካከል የተሻለ መቀራረብ እንዲፈጠር ማድ ረግ:- የቡድኑ አባላት በሙሉ በዕቅዱ ላይ ድረሻ እንዲኖራቸውና ሁሉም አስፈላጊ መረጃ እንዲደርሳቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህ የስብሰባውን ቃለ ጉባኤ የሚይዘውን ሰው ይጨምራል።

ሠ) የስብሰባውን ውጤት የሚያጠቃልል ሰው:- ብዙውን ጊዜ አንድ የቡድኑ አባል የቡድኑን ውሳኔ በውሳኔው ማስታወሻ ውስጥ ግልጽ መሆኑንና የቡድኑን ውሳኔ ማንጸባረቁን ቢያረጋግጥ መልካም ነው:: ያንን ይዞ የመጨረሻውን የውሳኔ ሰነድ ማዘጋጀት አለበት:: ቡድኑ ሰነዶቹን በሙሉ አይቶ በጉባኤ የውሳኔ አሳብ ማዘጋጀት ይከብደዋል:: ስለዚህ ለእያንዳንዱ የቡድኑ አባል አስቀድሞ ሰነዶቹን አይቶ አሳብ ቢሰነዝር፣ ወይም ነገሮችን በጥልቀት የመመርመር ተሰጥኦ ያለው አንድ ሰው ሰነዶቹን በሚገባ ቢገመግማቸው የተሻለ ነው።

ለ. እያንዳንዱ የቡድኑ አባል የቡድኑን ግብ በግልጽ መረዳት አለበት:: የቡድኑ ዓላማ ኮንፍረንስ ማዘጋጀት ነው ወይስ ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት መጀመር? የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ለመጀመር ነው? ሰዎች ቡድን የሚያቋቁሙበትን

ዓላማ በግልጽ ካልተረዱ፣ ውጤታማ በሆነ መንገድ በጋራ ሊሠሩ አይችሉም። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለአባላት ቡድኑ የተቋቋመበትን ዓላማና የሚያመራበትን ግብ ሊያብራሩላቸው ይገባል። የቡድኑ ዓላማ በሚገለጽባቸው ስብሰባዎች ላይ ሁሉም የቡድኑ አባላት ሊገኙ ያገባል። በውይይትና አባላት በሚያነሷቸው ጥያቄዎች የቡድኑ ዓላማ ይበልጥ እየተገለጸ ይሄዳል።

ሐ. ሰዎች በሙሉ አቅማቸውና በፈጠራ ችሎታቸው ተጠቅመው ችግሮቹን ሊፈቱና አዳዲስ ነገሮችን ሊሠሩ የሚችሉት በመሪዎችና በቡድኑ አባላት፣ እንዲሁም በአባላት መካከል መተማመን ሲኖር ነው። አለመተማመን ካለ፣ ሰዎች እንደ ቡድን መሥራት ይሳናቸዋል።

1) የቡድኑ አባላት በቡድኑ መሪ ክህሎት ሳይ ሊተማመኑና ለቦታው የሚመጥን ሰው እንደ ሆነ ሊያምኑ ይገባል። አባላት ለመሪው ችሎታ ክብር ከሌላቸው፣ በትጋት ሊሠሩ አይችሉም።

2) የቡድኑ አባላት በሌሎች የቡድኑ አባላት ችሎታ ላይ ሊተማመኑ ይገባል። የቡድኑ ዓላማ በቡድኑ ውስጥ ያሉ ሌሎች አባላት ያላቸውን አቅም ሊያከብሩና በቡድኑ ውስጥ የተካተቱበት ምክንያት እንዳለ ሊያስቡ ይገባል። አንድ ሰው የቡድኑ አባል የሆነበት በቂ ምክንያት እንዳለ ካላመኑ፣ ሌሎች የቡድኑ አባላት የዚያን ሰው አሳብ ለመስማት አይፈልጉም።

3) የቡድኑ አባላት በግልጽነትና በቅንነት ያላቸውን የአሳብ ልዩነቶች ለመወያየት መቻል አለባቸው። አባላት እርስ በርሳቸው ሊደማመጡና ሊከባበሩ ይገባል። ከሌላው አባል የተለየ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል። ያሁን እንጂ፣ አንድ የቡድን አባል ሌሎች አባሳት ለእርሱና ለአሳቦቹ ክብር እንዳላቸው መረዳት አለበት። አለበለዚያ ዝም ስለሚል ለቡድኑ ጥቅም ሳይሰጥ ይቀራል። እርስ በርስ አለመተማመን ካለ፣ አባላት ምርጥ ነው የሚሉትን ነገር ከመናገር ይልቅ የተሳሳተ ነገር እናገራለሁ በሚል ስጋት ዝም ሊሉ ይችላሉ። ወይም ሌሎች አባላት ብናገር ይስቁብኛል በሚል ፍርሃት ብቻ አስተያየታቸውን ከመስጠት ይቆጠባሉ። ስለዚህ መሪው



በሚናገረው ነገር ላይ ይስማማሉ። ይህ ደግሞ ሰዎች ከሌሎች ጋር ውጤታማ ሥራ እንዳያከናውኑ ያደርጋል።

4) በቡድኑ ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች እርስ በርስ ያላቸውን አለመተማመን እንዲያዳብሩ ማድረግ የመሪው ኃላፊነት ነው። ሰዎች (ሌሎች መሪዎች፣ አገልጋዮች ወይም በጎ ፈቃደኛ አገልጋዮች) በእነርሱ ላይ እምነት እንደ ጣሉ ከተረዱ፣ መሪው ከእነርሱ የሚጠይቀውን ለማድረግ በሚገባ ይንቀሳቀሳሉ። ነገር ግን መሪው በእነርሱ ላይ እምነት እንዳለው ካላሰቡ፣ እነርሱም በመሪው ላይ እምነት አይኖራቸውም። ብዙውን ጊዜ መሪው በአባላቱ ላይ ያለው እምነት አባላትን ያተጋቸዋል። ምክንያቱም መሪው ለእነርሱ ካለው ቦታ መውረድ አይፈልጉም። ስለዚህ የቡድኑ መሪ የአባላቱን አመኔታ ለማግኘትና ይሳቁብኛል ብለው ሳይፈሩ አሳባቸውን እንዲገልጹ መሥራት አለበት።

5) መሪዎች በአባላት ላይ እምነት ሊያሳድሩና ሁኔታዎችን ፈትሸው ለችግሩ ምላሽ የሚሆን አዲስ መፍትሔ እንዲያመጡ ወይም የተለየ ነገር እንዲሞክሩ ቢያደርጉ የቡድኑ አባላት ለእግዚአብሔር ሥራ አዲስ መንገድ ይጠቀማሉ። መሪዎች በአባላት ላይ ያላቸውን እምነት የሚያሳዩበት ዋነኛ መንገድ እነርሱን በሚመለከት ጉዳይ ላይ እንዲወስኑ በመፍቀድ ነው። መሪው ውሳኔውን ወስኖ ሌሎች አባላት ውሳኔውን እንዲያስፈጽሙ የሚጠብቅ ከሆነ፣ አባላት እንደ ታመኑ አይሰማቸውም። ስለዚህ መሪው ያለውን ብቻ ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ ይሠራሉ። በመከናወን ላይ ስላለው ነገር አይጨነቁም። የፈጠራ ችሎታቸውን አይጠቀሙም። ስለዚህ ችሎታና ተሰጥኦቸው ይባክናል። ነገር ግን ለሰዎች ችግሮችን እንዲፈቱ ኃላፊነት ሲሰጣቸው፣ ወይም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ውሳኔ እንዲወስኑ ሲፈቀድላቸው፣ ያን ጊዜ ሥራውን ለማከናወን ሲሉ የፈጠራ ችሎታቸውን ይጠቀማሉ።

15ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን ስብሳቢው እንደ ወንጌላዊ ለችግሮች መፍትሔ እንድትፈልግ ወይም የቤተ ክርስቲያኒቱን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የሚያስችሉትን የፈጠራ መንገዶች እንድትጠቀም ነጻነት በመስጠት

ፊንታ በወንጌላዊነትህ እነዚህንና እነዚያን ነገሮች ማድረግ አለብህ ቢልህ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማሃል? ለ) ወንጌላዊው ለቤተ ክርስቲያኒቱ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራም ነድፎ ተግባራዊ እንዲያደርግ ኃላፊነት ቢሰጠው ምን ዓይነት የአመለካከት ለውጥ ይኖረዋል?

16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቡድኖች በውይይት ዕቅዶችን ቢያወጡ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ የምትላቸው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች የትኞቹ ናቸው? ዘርዝራቸው። ለ) የቤተ ክርስቲያናችሁ አገልግሎቶች በዚህ ዓይነት መንገድ ቢታቀዱ፣ ምን ዓይነት ውጤቶች የሚገኙ ይመስልሃል?

መ. የቡድኑ አባላት መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን፣ ክህሎቶቻቸውንና ጥረቶቻቸውን ለራሳቸው የግል ጥቅም ሳይሆን ለቡድኑ ለማዋል መትጋት ይኖርባቸዋል። እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ለቡድኑ ስኬትና በጋራ ለመፈጸም ለሚፈልጓቸው ዓላማዎች በከፍተኛ ጥረት መሥራት ይኖርበታል። ስለ ግል ፍላጎቶቻቸው ወይም ለቤተ ክርስቲያናቸው የአገልግሎት ዘርፍ መጨነቅ የለባቸውም። የቡድኑ አባላት በግል ደረጃ ላከናወኑት ተግባር እውቅና ለማግኘት ከመጣር ይልቅ ቡድኑ እውቅና እንዲያገኝ የሚችሉትን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ለእያንዳንዱ ግለሰብ ጥቅም የሚሠሩ ቡድኖች ለጋራ ዓላማ የሚሠሩትን ያህል ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም። ከጋራ ይልቅ በግል ጥቅሞቻቸው ላይ የሚያተኩሩ የቡድኑ አባላት አብረው ለመሥራት የሚቸገሩ ሲሆን፣ ብዙም ሳይቆይ በተለያዩ የአሳብ ልዩነቶች ይከፋፈላሉ። ስብሰባዎች ባለመተማመንና በውጥረት ይሞላሉ። ውሳኔዎች የሚሰጡት ለሥራው ከሁሉም የሚሻለውን በማሰብ ሳይሆን፣ የቡድኑ አባላትን ለማስደሰት ይሆናል።

ሠ. የቡድኑ አባላት በቡድኑ ውስጥ በሚሠሩበት ጊዜ ማንን እንደሚወክሉ ማወቅ አለባቸው። ብዙውን ጊዜ በኮሚቴዎች ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች የሚወስኗቸው ውሳኔዎች በማን ላይ ተጽዕኖ እንደሚያመጡ ያውቃሉ። ሥራው ስኬታማ እንዲሆን፣ በቡድኑ ውስጥ የሌሉት ሰዎችም በውሳኔው አሳብ መስማማት አለባቸው። በመሆኑም፣ እንደ ቡድን ውሳኔ የሚሰጡ ወገኖች እነዚህን ወገኖች መዘንጋት የለባቸውም። ለምሳሌ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቀጣና መንፈሳዊ አገልግሎቶችን የሚያቅድ ቡድን አባል ከሆነ፣ ዳይሬክተሩ ውሳኔው የሚመለከታቸውን መምህራን፣ ተማሪዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማሰብ አለበት። ለእነርሱ ተቀባይነት ያለው ውሳኔ እንዲሰጥ አሳብ ማቅረብ አለበት። ይህ ካልሆነ፣ ውሳኔውን ይዞ በሚመጣበት ጊዜ ውሳኔውን ስለሚቃወሙ፣ የተወጠነው ዕቅድ ሁሉ ከንቱ ይሆናል።

ለአንድ አገልግሎት ራእይ ያላቸው ሰዎች ዕቅዶቻቸውን ለማቀድና ተግባራዊ ለማድረግ በሚጥሩበት ጊዜ እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን ያደርጋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህን ለማድረግ የሚያስችል ጊዜ የላቸውም። በቤተ ክርስቲያን ሁሉንም ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ጊዜም ሆነ እውቀት የለንም። ነገር ግን፣ የቡድን አባላትን በጥንቃቄ ከመረጥን፣ እና የቤተ ክርስቲያኒቱን ግብ እያሰቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ክትትል የምናደርግ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ራእዩ ባላቸው ሰዎች አማካኝነት ታላቅን ነገር ሲያደርግ እንመለከታለን። ስለሆነም፣ ሁሉንም ነገር እኛው ማድረግ አለብን ከሚል አሳብ መውጣት አለብን! መንፈስ ቅዱስ በሌሎች ሰዎች በኩል ሊሠራ እንደሚችል ማመን አለብን። እንደ እግር ኳስ አሠልጣኝ፣ የቡድኑን አባላት ክህሎቶች ለማሻሻልና በጥሩ ሁኔታ አብረው እንዲሠሩ ለማስቻል መጣር አለብን። ከዚያ በኋላ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሠሩ ዕድሉን መስጠት ያስፈልጋል።

17ኛ ጥያቄ፡- ከዚህ በፊት ስለ መራኸው ወይም አሁን በመምራት ላይ ስላለኸው አንድ ኮሚቴ አስብ። ከላይ የቀረቡት አሳቦች ኮሚቴውን ለመምራትና ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ እንዴት እንደሚጠቅሙህ ግለጽ።

## የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ ቡድን አብረው ለመሥራት መማር አለባቸው።

የመምራት ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ በአንድ ሰው ላይ በሚያርፍበት ጊዜ፣ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይሠቃያል። በክርስቶስ አካል ውስጥ ሁሉንም ውሳኔ ብቻውን የሚወስን አምባገነናዊ መሪ ቦታ የለውም። ይሁን እንጂ፣ ብዙውን

ጊዜ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ውሳኔዎች ሁሉ በአንድ ሰው ብቻ የሚወሰኑበት ሁኔታ ይታያል:: የሽማግሌዎች ቦርድ ሲኖር ቢችልም፣ አንዱ ግለሰብ ውሳኔዎችን ሁሉ መስጠቱን ሊቀጥል ይችላል:: ይህ በሁለት ምክንያቶች ለቤተ ክርስቲያን በጣም አደገኛ ነው::

<u>አንደኛ</u>፣ ሰይጣን ብዙውን ጊዜ ብቻውን በሚወስነው መሪ ላይ ኃይልን ይቀዳጃል:: ሁሉንም ሥራ ብቻውን እንደሚያከናውን በማሰብ፣ በቀላሉ በኩራት ሊወጠር ይችላል:: ሁሉንም ውሳኔዎች እርሱ ብቻ ሊወስን እንደሚችልም ያስባል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በአመራር ውስጥ የሚሠሩ ብዙ መሪዎችን እንዳስቀመጠ እንመለከታለን:: በአንድ ሽማግሌ ብቻ ቤተ ክርስቲያን መመራቷን የሚያሳይ መረጃ የለም::

<u>ሁለተኛ</u>፣ አንድ ግለሰብ ብቻውን ለመምራት በሚፈልግበት ጊዜ፣ የሚጠቀመው የራሱን መንፈሳዊ ስጦታዎች፣ የትምህርት ደረጃና አመለካከቶች ብቻ ነው:: አንድ ሰው እንዳለው፣ ውሳኔዎችን ሁሉ ብቻውን የሚሰጥ መሪ ሞኝ አማካሪ ያለው ነው:: እርሱ ሁሉንም ነገር የሚያደርግ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከእርሱ ችሎታ በላይ ልታድግ አትችልም:: በመሆኑም፣ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያንና እያንዳንዱ አገልግሎት በአገልጋዮች «ቡድን» መመራት አለበት:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ የተለያዩ ተሞክሮዎችና መንፈሳዊ ስጦታዎች የቤተ ክርስቲያን መሪውን ድክመቶች በመሙላት ለእግዚአብሔር ሥራ የተሻለ ሥራ እንዲሠራ ያስችላሉ:: በመሆኑም፣ በቅርብ አብረው በመሥራት የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመሩ ሽማግሌዎች መኖር አለባቸው:: በዚህ ዓይነት፣ የእግዚአብሔር ሥራ በተሟላ መንገድ ይከናወናል::

እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አብረው በመሥራት የቤተ ክርስቲያኒቱን ግቦች የሚፈጽሙበትን አስተዳደራዊ መዋቅር ማዘጋጀት አለባት:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉት፣ ጥራት ያላቸውን ውሳኔዎች ሊሰጡ የሚችሉት፣ በቅርብ አብረው ሲሠሩና ልዩነቶቻቸውን ሲቻቻሉ ብቻ ነው:: **ውጤታማ የቤተ**



**ክርስቲያን አመራር ሊኖር የሚችለው የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሏቸው በሳል ግለሰቦች ሲኖሩ ነው:: እነዚህ ሰዎች ደግሞ በፍቅርና በግልጽነት መንፈስ የሚሠሩ መሆን አለባቸው::** በአመራር ላይ ያሉ ወገኖች (የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ የቀጣና ሽማግሌዎች፣ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት፣ ወዘተ. . . ) የአመራርና የአገልግሎት ቡድኖቻቸውን በሚያዋቅሩበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስታወስ አለባቸው::

1. ከመሪው ጋር የሚሠሩ ትክክለኛ ሰዎች መመረጥ አለባቸው::

ብዙውን ጊዜ መሪው አብረውት በሚሠሩት ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ባያሳድርም፣ ምእመናን በሚከተሉት መስፈርቶች ላይ ተመሥርተው መሪዎችን እንዲመርጡ ማበረታታት አለበት፦

ሀ. ሰዎቹ መንፈሳዊ ብስለት ያላቸው መሆን አለባቸው:: አንድ መንፈሳዊ ብስለት የጎደለው ራስ ወዳድ መሪ አንኳን ቡድኑን ሊከፋፍል ይችላል:: እግዚአብሔርን የመስማትና እስቲጋሪ ቢሆንም እንኳን እርሱ ያላቸውን ብቻ የማድረግ ፍላጎት የሚኖራቸው መንፈሳዊ ብስለት ያላቸው ብቻ ናቸው:: የማይቻሉ በሚመስሉ ሁኔታዎች ውስጥ ወደ እግዚአብሔር በእምነት ማየት የሚችሉት እርሱን መተማመንን የተማሩ ሰዎች ብቻ ናቸው:: እርስ በርሳቸው ለመደማመጥና የግል ፍላጎታቸውን ለእግዚአብሔር መንግሥት ለመሠዋት የሚችሉት መንፈሳዊ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው:: በመሆኑም፣ መሪዎችን በምንመርጥበት ጊዜ መንፈሳዊ ብስለታቸው ትልቁ ነጥብ ሊሆን ይገባል::

ለ. የቦርድ አባላት የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ሊኖሯቸው ይገባል:: ቀደም ሲል መንፈስ ቅዱስ ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን እንደሚሰጥ ተመልክተናል:: ውሳኔዎችን በመስጠቱ በኩል ሚዛናዊነትን የሚጠብቀው ይህ የመንፈሳዊ ስጦታዎች ውህደት ነው:: የቤተ ክርስቲያን አመራር ሚዛናዊ እንዲሆን ከተፈለገ፣ የወንጌላዊነት፣ የማስተማር፣ የመርዳት፣ የማስተዳደር፣ ወዘተ. . . ስጦታዎች ያሏቸው ሰዎች መወከል አለባቸው:: መሪዎች እንዲህ ዓይነት መንፈሳዊ ስጦታዎች

ካሏቸው፣ እያንዳንዳቸው ቤተ ክርስቲያን እንዴት መመስክር፣ የደቀ መዝሙርነት ትምህርት መስጠት፣ እንዲሁም በችግር ላይ ያሉትን ወገኖች እንዴት መርዳት እንዳለባት የሚያመለክቱ አሳቦችን ሊያቀርቡ ይችሳሉ:: ይህ ደግሞ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ፅ ቅዶች እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኒቱ እንድታከናውን የሚፈልገውን ዓላማ እንዲያንጸባርቁ ያስችላቸዋል:: መሪዎች በሚመረጡበት ጊዜ ይህ የመንፈሳዊ ስጦታዎች እንዲጠበቅ ማድ ረጉ ጠቃሚ ይሆናል::

(ማስታወሻ:- የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ከዓለማዊ ትምህርት ወይም የሥራ ልምድ በላይ አስፈላጊዎች ናቸው:: መሪዎች ለመሪነት አገልግሎት ከመመረጣቸው በፊት መንፈሳዊ ስጦታዎቻ ቸውን አውቀው ከሥራ ላይ ማዋል አለባቸው:: ምእመናንም ቢሆኑ መምረጥ ያለባቸው መደበኛ ባልሆነ መንገድ ማገልገል የጀመሩትን ሰዎች ሊሆን ይገባል:: የሽማግሌዎች ምርጫ ምእመናን እግዚአብሔር አንድን ሰው ለአመራር መጥራቱን የሚያ ረጋግጡበት አጋጣሚ መሆን አለበት:: ይህም የሚሆነው ግለሰቡ ክራሱ ወዳድነት በጸዳ መንገድ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ሲያገለግል በማየታቸው ምክንያት ሊሆን ይገባል:: በሙያ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን አሠራርና በአነርሱ መሥሪያ ቤት በሚከናወኑ ሥራዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለይተው ማወቅ አለባቸው::)

ሐ. ሽማግሌዎች የተለያዩ ተሞክሮዎች ሊኖሯቸው ይገባል:: ሁሉም መምህራን፣ ወይም ወንጌላውያን፣ ወይም ደግሞ መጋቢያን ብቻ ቢሆኑ ጥሩ ውሳኔዎችን ለመስጠት መቸገራቸው የማይቀር ነው:: ብዙውን ጊዜ የቡድኑ ውሳኔ ሚዛናዊ የሚሆነው የቡድኑ አባላት የተለያዩ ተሞክሮዎች ያሏቸው እንደ ሆነ ነው::

መ. ሽማግሌዎች ክመሪው የተለዩ አመለካከቶች ሊኖሯቸው ይገባል:: ሁሉም አባላት አንድ ዓይነት አቋም የሚይዙበት ቡድን ጤናማ አይደለም:: ጥሩ ውሳኔዎችን መስጠት የሚቻለው ሰዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አመለካከቶች ሲኖራቸው ነው:: የቡድኑ አባላት ሁሉ የመሪው የገደል ማሚቶዎች ክሆኑ፣



መኖራቸው አስፈላጊ አይሆንም:: የመሪውን ውሳኔዎች የሚያጠናክሩት የተለያዩ አሳቦችን ስለሚጨምሩ ነው:: ስለሆነም፣ መሪው በሽማግሌዎች ቦርድ ውስጥ ልክ እንደ እርሱ የሚያስቡ ሰ ዎች እንዲኖሩ መሻት የለበትም:: ነገር ግን፣ በጉዳዮች ላይ የተ ለያዩ አመለካከቶች ያሏቸው ሰዎች እንዲኖሩ ማበረታታት አለበት::

> 18ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ የሽማግሌዎች ስብሳቢ ሆነህ ብትመ ረጥ፣ የቦርዱ አባላት ሆነው እንዲመረጡ የምትፈልጋቸውን ሰዎች ወይም የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዓይነቶች ዘርዝር:: ለ) እያንዳንዱን መንፈሳዊ ስጦታ ወይም ልምድ ያለው ሰው ለምን እንደ መረጥክ ግለጽ:: ይህ ለአንተና ለምትሰጣቸው ውሳኔዎች ሚዛናዊነትን የሚሰጠው እንዴት ነው? ሐ) ሰዎችን የሚመርጡት ምእመናን ስለሆኑ፣ መሪዎች ለምርጥ ውሳኔ አሰጣጥ የሚጠቅሙ ሚዛናዊ የሆኑ ሰዎች እንዲመረጡ ምን ማድ ረግ ይኖርባቸዋል?

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሚዛናዊ መንፈሳዊ ስጦታ ያላቸው ሰዎች እንዲመረጡ ለማድረግ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የተወሰነ ነው:: (ማስታወሻ:- በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ተመራጭ ዕ ጩዎችን ለምእመናን የሚያቀርብ አስመራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል:: በዚህ ጊዜ አስመራጭ ኮሚቴው ሚዛናዊነታቸውን የጠበቁ ሰዎች እንዲመረጡ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል::) ምእመናን የፈለጉትን ሰው እንዲመርጡ ነጻነት የሚሰጡ አብያተ ክርስቲያናት፣ የቦርድ አባላትን በሚመርጡበት ጊዜ የሚከተሉትን ነገሮች እንዲያደርጉ ይመከራሉ:-

1) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለያዩ መንገዶች አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ መንፈሳዊና በሳል ሰዎች መመረጥ እንዳለባቸው ለምእመናኑ ተናገሩ:: ምርጥ ውሳኔ ለመስጠት ለምን የተለያዩ ስጦታዎችና ሥረ-መሠረቶች ያሏቸው ሰዎች መመረጥ እንዳለባቸው አብራሩላቸው:: የሽማግሌዎች ስጦታዎችና ተሞክሮ ዎች እርስ በርሱ ይደጋገፍ ዘንድ አንዱን ሰው ክመረጡ በኋላ ቀጣዩ ተመራጭ ምን ዓይነት ስጦታ ሊኖረው እንደሚገባ እንዲያስቡ አበረታቷቸው::

2) መጀመሪያ የሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ መመረጥ አለበት:: ይህ ሲሆን ሁሉም የእርሱን መንፈሳዊ ስጦታዎችና ሥረ-መሠረት ያውቃል::

3) ሌሎች የቦርዱ አባላት በሚመረጡበት ጊዜ ሚዛናዊ የአመራር ቡድን እንዲኖር ለመራጮቹ ማብራሪያ መስጠቱ አስፈላጊ ነው:: መሪዎችን ከተለያዩ ጎሳዎች ወይም መልክዓ ምድራዊ አካባቢዎች መምረጡ ጠቃሚ ነው:: በምርጫው ጊዜ የመሪውን ደካማ ጎኖች ለመሸፈን እንዲቻል የተለያዩ ስጦታዎች ያሏቸውን ሰዎች መምረጡ አስፈላጊ ይሆናል:: ለምሳሌ፣ መሪው የገንዘብ ጉዳይ ብዙም የማያውቅ ከሆነ፣ ጥሩ የገንዘብ አያያዝ ችሎታ ያለው ሰው እንዲመረጥ ማድረጉ ተገቢ ነው:: መሪው ለወንጌል ስርጭት ራእይ ከሌለው፣ ለወንጌል ስርጭት ከፍተኛ ራእይ ያለው ሰው መምረጥ መልካም ነው::

2. ሰዎች አሳባቸውን ለማካፈል እንዲችሉ በአመራር ስብሰባዎች ላይ ትክክለኛ ግንኙነቶችን መፍጠር::

የቤተ ክርስቲያን መሪው ሰዎች «እውነትን በፍቅር የሚናገሩበትን» ድባብ መፍጠር አለበት (ኤፌ. 4:15):: ጥሩ ውሳኔዎችን መስጠት የሚቻለው ሁሉም ሰው አሳቡን በነጻነት መናገር ሲችል ነው:: መሪው ሰዎች ከእርሱ ጋር ወይም እርስ በርሳቸው በአሳብ በመለያየታቸው ምክንያት የሰውን ስሜት እጎዳለሁ የሚል ፍርሃት እንዳያድርባቸው መከላከል አለበት:: ይህም ማለት መጀመሪያ መሪው አብረውት በሚሠሩት ሰዎች መካከል መተማመን እንዲኖር ማድረግ አለበት:: የቡድኑ አባላት መከበራቸውን፣ መታመናቸውንና መወደዳቸውን ማወቅ አለባቸው:: ሰዎች የሌላውን ሰው ስሜት በማይጎዳ መንገድ በፍቅር እንዴት አሳባቸውን መግለጽ እንዳለባቸው ማስተማር የመሪው ተግባር ነው:: እንዲሁም ደግሞ ሰዎች አሳባቸውን በእውነቱ መንገድ መግለጽ እንዲችሉ፣ የመሪውን ወይም የሌላውን አባል አሳብ እንዲቃወሙ ማበረታታት አለበት:: ቡድኑ ጥሩ ውሳኔዎችን መስጠት የሚችለው ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲተማመኑና በግልጽ አሳባቸውን ሲናገሩ ብቻ ነው::



> 19ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች «እውነትን በፍቅር ለመናገር» የሚያስችል የመተማመንና የመከባበር ደረጃ ላይ የደረሱ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ:: ለ) የቤተ ክርስቲያናችሁ የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ሆነህ ብትመረጥ፣ ሰዎች መሪውን ሳይፈሩ ወይም እርስ በርሳቸው ሳይፈራሩ አሳባቸውን በግልጽ እንዲናገሩ ለማስቻል ምን ምን ነገሮችን ታደርጋለህ?

3. መሪው «ግቡን» በሁሉም መሪዎች አእምሮ ውስጥ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት:: ግለሰቦች ቡድን ሲሆኑ የሚችሉት ለአንድ ዓላማ ሲሠሩ ብቻ ነው:: ብዙውን ጊዜ ሽማግሌዎች ወይም የቀጣና መሪዎች ወደ ስብሰባው የሚሄዱት ለአገልግሎታቸው ወይም ለቀጣናቸው አንዳች ነገር ለማግኘት በመፈለግ ነው:: ውሳኔዎች በሚሰጡበት ጊዜ፣ ተወካዩ ብዙውን ጊዜ «ከዚህ ውሳኔ አካባቢዬ ምን ጥቅም ያገኛል?» የሚል ጥያቄ ያነሣል:: ምንም እንኳን መሪዎች ውሳኔው በአገልግሎታቸው አካባቢ ወይም ቀጣና ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ማወቃቸው አስፈላጊ ቢሆንም፣ መሪዎች በራስ ወዳድነት መንፈስ ለአካባቢያቸው ብቻ የሚያስቡ ከሆነ፣ ጥሩ ውሳኔዎችን መስጠት አይቻልም:: መሪው አብሮ የመሥራቱ ዓላማ እያንዳንዱ አካባቢ ፍትሐዊ የገንዘብ ወይም የህብት ድርሻ እንዲያገኝ ለማስቻል አለመሆኑን መግለጽ አለበት:: ከዚህ ይልቅ፣ ወሳኙ ጥያቄ፣ «ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚልቀው ነገር ምንድን ነው?» የሚለው ነው:: እያንዳንዱ መሪ መንፈስ ቅዱስ የሚፈልገውንና ለእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚኖረውን ውሳኔ ለመስጠት ተዘጋጅቶ መምጣት አለበት:: ይህ ማለት ብዙውን ጊዜ ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ቀጣናዎች የሚፈልጉትን ሳያገኙ ይችላሉ ማለት ነው:: መሪዎች እንደ አንድ ቡድን ለእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሥራ ሲያከናውኑ የሚችሉት ለአካባቢያቸው አንዳንድ ነገሮችን ለማስፈጸም ሲፈልጉ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ሲሹ ብቻ ነው::

**የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎቶች ለማከናወንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ ለመፈጸም የሽማግሌዎቹ ለብሳቢና ሌሎችም ሠራተኞች በጥንቃቄ መመረጥ አለባቸው።**

ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሥራቸው የሚሠሩትን ሌሎች ሰዎች ለማሰብና ለማቀድ እንደማይችሉ «የቀን ሠራተኞች» አድርገው ይቆጥሯቸዋል። መሪዎቹ ዝርዝር መመሪያዎችን በመስጠት የሆነ ነገር እንዲያደርጉ ይነግሯቸዋል። «ወደ ገበያ ሄደህ ቅቤ ግዛ። የማስታወሻ ደብተሬን አምጣልኝ፣» ሊሉ ያዟቸዋል። መሪው ውሳኔዎችን ሁሉ ያደርግና ከሥሩ የሚሠሩ ወንጌላውያን፣ ሰባኪዎች ወይም የመዘምራን ቡድን አባላት የሚፈልገውን ነገር እንዲያደርጉለት ይጠይቃል። የሚያሳዝነው፣ መሪዎች የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን በዚህ መንገድ የሚያስተናግዱ ከሆነ፣ መሪዎቹ እግዚአብሔር ለእነዚህ ሰዎች የሰጣቸውን ስጦታዎች እንዲጠቀሙ ሊያደርጉ አለመቻላቸው ነው።

ከቤተ ክርስቲያን መሪው ሥር የሚሠሩ ሠራተኞች ወይም ሰዎች እግዚአብሔር የሰጣቸው መንፈሳዊ ስጦታዎችና ችሎታዎች አሏቸው። መሪው ችሎታዎቻቸውን እንዲጠቀሙ የሚያበረታታቸው ከሆነ፣ አገልግሎቱን ሊያሳድጉለት ይችላሉ። በመሆኑም፣ መሪው በመሪዎች መካከል ቡድን መፍጠር ብቻ ሳይሆን፣ መሪው አገልግሎቶች በቡድን የሚሠሩበትን ሁኔታ መፍጠር አለበት። እነዚህ ቡድኖች የመሪውን አገልግሎት ሊያሳድጉ ይችላሉ። (መሪው ከሥሩ የሚሠሩትን ሰዎች እንዴት ማሳደግ እንዳለበት ቀደም ሲል ስለ ውክልና በተነጋገርንበት ክፍል ውስጥ የተገለጹትን ሐሳቦች ተመልከት።) የቤተ ክርስቲያንን ቀጣይነት ያለው አገልግሎት የሚከታተሉ ሁለት የአመራር ደረጃዎች አሉ።

1. መሪውና የእያንዳንዱ አገልግሎት ዘርፍ ኃላፊዎች እንደ አንድ ቡድን መሥራት አለባቸው።



አብዛኛውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚያካሂዱት ወንጌላውያን፣ መጋቢያን፣ የሰንበት ትምህርት ቤት መምህራንና የልማት ሠራተኞች ናቸው። የእነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ ስጦታዎችና የሥራ ልምዶች ሚዛናዊነትን እንዲፈጥሩ መሪዎች በእነዚህ አገልግሎቶች ላይ የሚሰማሩትን ሰዎች በጥንቃቄ መምረጥ አለባቸው። ሁሉም አገልግሎቶች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጠውን ግብ ለመፈጸም እንዲችሉ ሁሉም እንደ ቡድን እንዲሠሩ ማድረግ አሰበት። እያንዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ ለየብቻው የሚሠራ ከሆነ፣ በኅብረት የሚሠሩትን ያህል ውጤታማ መሆን አይቻልም። ልማት ለወንጌል አገልግሎት፣ የወንጌል አገልግሎት ደግሞ በመዘምራንና በሰንበት ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ማበርከት አለበት። እያንዳንዱ ፕሮግራም ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያበረክተው ነገር ሊኖር ይገባል። ስለሆነም፣ አንድ መሪ እያንዳንዱ ሠራተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ እውን ለማድረግ እንዲችል አስተዋጽኦ የሚያደርግ መዋቅር ማዘጋጀት አለበት።

2. እያንዳንዳቸው የአገልግሎት ዘርፍ ኃላፊዎች የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግሎት ለመምራት የሚችሉትን የቡድን አባላት ማዘጋጀት አለባቸው።

ለምሳሌ፣ ወንጌላዊው አዋቂዎችን፣ ሴቶችንና ወጣቶችን በወንጌል ለመድረስ አብረውት የሚሠሩትን ሰዎች እንደ አንድ ቡድን ማዘጋጀት አለበት። በስፖርት አገልግሎቶች ላይ የሚሠራ ሰው የወንጌል ስርጭት አገልግሎቱን ውጤታማ ለማድረግ በቡድኑ ውስጥ ሊካተት ይችላል። የሰንበት ትምህርት ላይ የሚሠራ ሰው ደግሞ የአዋቂዎች፣ የልጆችና የወጣቶች ትምህርት የሚመለከታቸውን ሰዎች በማሰባሰብ ቡድን ሊመሠርት ይችላል።

በቡድኑ ውስጥ ያሉት ሰዎች ይበልጥ ተቀራርበው የሚሠሩ ከሆነ፣ ሥራቸው የተሳካ ይሆናል። ዋንኞቹ የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት አስተባባሪዎች አዘውትረው የማይሰባሰቡ ከሆነ፣ በጥሩ ሁኔታ የሚሠራ ቡድን መመሥረት ይቸግራቸዋል። ይህ ደግሞ አገልግሎቶችን ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዳያስተባብሩ

ያደርጋቸዋል:: የአገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ አብረውት የሚሠሩ ሰዎች የሚገኙበት ቡድን ከሌለው፣ ለአገልግሎት ዘርፉ ብቃት ያለው ዕቅድ የማውጣት አቅሙ የተገደበ ይሆናል፣ በአገልግሎቱ ውስጥ የሚሠሩትን ሰዎች ማግኘትም ይቸግረዋል:: ብዙውን ጊዜ ሰዎች በደስታ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉት የአንድ ቡድን አካል ሲሆኑ ነው:: ስለሚያከናውኑት ተግባርም ሆነ ፕሮግራሙ ስለሚካሄድበት መንገድ ድምጽ ሊሰጡ የማይችሉ ከሆነ፣ በአብዛኛው ልባቸውን ለአገልግሎቱ አይሰጡም::

> 20ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ የሚከናወኑትን አገልግሎቶች ዘርዝር:: ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪው አገልግሎቶቹን የሚያከናውኑ ሰዎች የራሳቸውን አገልግሎት እንዲያዘጋጁ፣ የአገልግሎት ግቦቻቸውን እንዲወጥኑና ግቦቻቸውን ለመፈጸም የሚችሉባቸውን መንገዶች እንዲቀይሱ ያስችሏቸዋልን? ካልሆነ፣ ለምን? ሐ) በእነዚህ አገልግሎቶች ላይ ለመሥራት ቡድኖችን መመሥረት ጠቃሚ የሚሆን ይመስልሃል? ከሆነ፣ ለምን? ካልሆነስ፣ ለምን? መ) ለአንድ አገልግሎት ራእይ ያላቸው ሰዎች አብረው መሥራታቸው ምን ዓይነት ለውጥ የሚያመጣ ይመስልሃል?

**የቤተ ክርስቲያን መሪው ጊዜያቸውንና መንፈሳዊ ስጦታቸውን በፈቃደኝነት ለእግዚአብሔር የሚያውሉ ሰዎች የሚገኙበትን የበጎ ፈቃደኞች ቡድን ማደራጀት አለበት::**

> 21ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያለ ደመወዝ በትጋት የሚያገለግሉትን ሰዎች ስም ዘርዝር:: ለ) እነዚህ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ለምን እንደሚያስፈልጉ ግለጽ::

የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን ለምታከናውናቸው ሥራዎች በሙሉ ሰዎችን ቀጥሮ ለማሰማራት የሚያስችል የገንዘብ አቅም የላትም:: የቤተ ክርስቲያኒቱ ሠራተኞች ብቻቸውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከናወን ያለባቸውን ተግባራት በሙሉ ለማከናወን አይችሉም:: ስለዚህ፣ ከፍቅር የተነሣ ያለ ደመወዝ የሚሠሩ በጎ ፈቃደኞች መኖራቸው አስፈላጊ ነገር ነው:: ውጤታማ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔር መንግሥት በታማኝነት የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎቶች በሚያከናውኑ በጎ ፈቃደኞች ላይ የሚደገፍ መሆኑን



መረዳት አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን ሁሉ ክርስቶስን እንዲያገለግሉ ማደፋፈር አለባቸው:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉ ይሄዳሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በበጎ ፈቃደኝነት የሚያገለግሉ ምእመናን መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን በመጠቀም እግዚአብሔርን የሚያገለግሉባቸውን መንገዶች እንዲያገኙ ማገዝ ይኖርባቸዋል::

ይሁንና፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጎ ፈቃደኞችን በውጤታማ መንገድ እንዲጠቀሙ ለማስቻል፣ በጎ ፈቃደኞቹን በቡድን ማደራጀትና ክርስቶስን እንዲያገለግሉ ማበረታታት አለባቸው:: መሪዎች ከበጎ ፈቃደኞች ጋር በሚሠሩበት ጊዜ ሊገነዘቧቸው የሚገቡ ሁለት ነገሮች አሉ፤ እነዚህም ከሠራተኞች ጋር ከመሥራት የተለዩ ናቸው::

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ደመወዝ የማይከፈላቸው በጎ ፈቃደኞች ተበረታትተው በዋና ዋና አገልግሎቶች ላይ መሥራታቸውን እንዲቀጥሉ ማድረጉ ከባድ ነው:: መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት በምእመናን የሚመረጡ ሰዎች ናቸው:: ለአገልግሎቱ ስለ ተመረጡ የኃላፊነት ስሜት ስለሚሰማቸው በታማኝነት መሥራታቸውን ይቀጥላሉ:: «ሽማግሌዎች» በመሆናቸው ምክንያት ክብር እንደ ተሰጣቸውም ይሰማቸዋል:: ደመወዝ የሚከፈላቸው ሠራተኞች ደግሞ ገንዘብ ስለሚያገኙ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሥራታቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ:: በጎ ፈቃደኞች ግን ደመወዝም ሆነ የሽማግሌነት ክብር አያገኙም:: የሚያገለግሉት መንፈሳዊ ስጦታቸውን ለጌታ ሥራ ለማዋል በማሰብ ብቻ ነው:: ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእነዚህ ሰዎች አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን በጣም ጠቃሚ መሆኑን በመግለጽ ካላበረታቷቸው፣ አገልግሎታቸውን አቋርጠው ለአምልኮ ብቻ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል::

<u>ሁለተኛ</u>፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በበጎ ፈቃደኞች ላይ እምብዛም ሥልጣን የላቸውም:: አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አመራር ከመንግሥት ወይም ከንግዱ ዓለም አመራር በላይ አስቸጋሪ መሆኑን አይገነዘቡም:: በመንግሥት

መሥሪያ ቤቶችም ሆነ በንግዱ ዓለም፣ መሪዎች ሠራተኞችን በገንዘብ ቀጥረው ያሠራሉ። ደመወዝ ስለሚከፈላቸው፣ ሰዎቹ መሪ ዎች ያዘዟቸውን ነገሮች የማከናወን ኃላፊነት አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን ግን በቀዳሚነት «የበጎ ፈቃደኞች ድርጅት» ነች። ደመወዝ የሚከፈላቸው ጥቂት ሠራተኞች ሊኖሩ ቢችሉም፣ አብዛኛ ው ሥራ የሚሠራው ግን በበጎ ፈቃደኞች ነው። ለምሳሌ ያህል፣ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምሩ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን የሚመሩ፣ ለጎረቤቶቻቸው የሚመሰክሩ፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያጸዱ፣ ወዘተ. . . በጎ ፈቃደኞች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብዛኞቹ ሰዎች የሚሠሩት በበጎ ፈቃደኝነት ስለሆነ፣ ብዙዎቹ የአስተዳደር መርሖዎች ለእነርሱ የሚሠሩ አይሆኑም። ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጎ ፈቃደኞችን እንዴት እንደሚያስተናግዱ ማወቅ አለባቸው። በጎ ፈቃደኞችን ልክ እንደ ቅጥር ሠራተኞች ልናስተናግድ አንችልም። ነገሮችን እንዲያከናውኑ የማዘዝ ሥልጣን የለንም። ፈቃደኛ ከሆኑ ብቻ እንዲሠሩልን ልንጠይቃቸው ብቻ ነው የምንችለው።

በጎ ፈቃደኞች ነፃ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት ጠቃሚ የቤተ ክርስቲያን አካል መሆናቸውን ካረጋገጥንላቸው ነው። ሁሉም የእግዚአብሔርን ሥራ ለማከናወን ስጦታዎቻቸውንና ችሎታዎቻ ቸውን ለመጠቀም እንዲችሉ በበጎ ፈቃደኞችና ደመወዝ በሚከፈላቸው ሠራተኞች መካከል ጥሩ ግንኙነት መኖር አለበት። መሪዎች በጎ ፈቃደኞችን ለማበረታታት ሊያደርጉ ከሚችሏቸው ነገሮች ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተገልጸዋል፦

1. እንደ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ለእግዚአብሔር ታላላቅ ተግባር ልናከናውን የምንችለው እኛና ደመወዝ የሚከፈላቸው ሠራተኞች ብቻ ነን የሚለውን አሳብ መለወጥ አለብን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር ስጦታዎችን የሰጣቸውና ለእግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን ሊያከናውኑ የሚችሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ይህንን እውነታ በመገንዘብ በጎ ፈቃደኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትርጉም ያለው አገልግሎት ሊሰጡ



የሚችሉባቸውን መንገዶች መቀየስ አለባቸው። በጎ ፈቃደኞች የሚፈለጉት ቤተ ክርስቲያንን ለማጽዳት ብቻ መሆን የለበትም። እያንዳንዱ አባል ለቤተ ክርስቲያን እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። አማኞች በአምልኮ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን በመጠቀም ጭምር ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ ትርጉም ያላቸው የኃላፊነት በሮች ሊከፈቱላቸው ይገባል።

2. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለአገልግሎቱ ኃላፊነት በተሰጠው ሰው ሥር በጎ ፈቃደኞች «በቡድን» ተደራጅተው የሚያገለግሉበትን ሁኔታ ሊያመቻቹላቸው ይችላሉ። ይህ ቅንጅትን በመፍጠር የተሻለ ሥራ እንዲሠራ ያደርጋል።

3. በጎ ፈቃደኞች የበለጠ ብቃት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአገልግሎት መስካቸው ሥልጠና ሊሰጧቸው ይገባል። በጎ ፈቃደኞች የአገልግሎት ክህሎት እያገኙ በሚመጡበት ጊዜ ተጨማሪ ኃላፊነት ሊሰጣቸው ይገባል።

4. ብዙውን ጊዜ ሰማኒያ በመቶውን የቤተ ክርስቲያን ሥራ የሚሠሩት ፈቃደኞች ሆነው የሚገኙ ሃያ በመቶ ምእመናን ናቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህ በጎ ፈቃደኞች በሥራቸው እንዲቀጥሉ ለማስቻል ሊያበረታቷቸው ይገባል። በአመዛኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት እግዚአብሔርን በብቃት ከሚያገለግሉ ሰዎች ጋር ሳይሆን፣ ችግር ከሚፈጥሩ ሰዎች ጋር ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጉጉት ከሚያገለግሉ ሰዎች ጋር ባለመቀራረባቸው ምክንያት፣ በጎ ፈቃደኞች ተስፋ ቆርጠው ውጤታማ ሳይሆኑ ይቀራሉ። ስለሆነም፣ አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከበጎ ፈቃደኞች ጋር በቂ ጊዜ በማሳለፍ፣ በማበረታታትና በማሠልጠን፣ እንዲሁም ጠቃሚ አገልግሎቶችን በመስጠት ውጤታማ ተግባር እንዲያከናውኑ ያስችሏቸዋል።

5. በጎ ፈቃደኞች በቀዳሚነት የሚሠሩት ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ለመግለጽ ስለሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተደጋጋሚ በግልም ሆነ በቤተ ክርስቲያን መድረክ

አድናቆታቸውን ሊገልጹላቸው ይገባል:: ይህ በጎ ፈቃደኞችን ስለሚያበረታታ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ:: ሰ ዎች ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ሊመሰገኑ ይገባል:: በእመዞች በጎ ፈቃደኞች የሚያከናውኗቸውን አገልግሎቶች ሰዎች ማወቃቸውና ጠቃሚ ነው ብለው ማሰባቸው ከደመወዝ የበለጠ ማበረታቻ ሊሆናቸው ይችላል::

6. የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች በጎ ፈቃደኞችን ለመሪዎች አነስተኛ ሥራዎችን እንደሚሠሩ የቀን ሠራተኞች ሊመለከቷቸው አይገባም:: ይልቁንም፣ ለቤተ ክርስቲያን ሥራ በጣም አስፈላጊ እንደ ሆኑ ሰዎች መታየት አለባቸው:: መሪዎች በአክብሮትና በፍቅር ሊመለከቷቸው ይገባል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለበጎ ፈቃደኞች የግል ሕይወት፣ ለቤተሰባቸው፣ ወዘተ. . . በሚያስቡበት ጊዜ፣ በጎ ፈቃደኞች በበለጠ ራሳቸውን ለሥራው ይሰጣሉ:: ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ችል ሲሏቸው ወይም ለተራ ሥራ እንደሚፈለጉ አድርገው ሲመለከቷቸው፣ ተ ስፋ ቆርጠው በአገልግሎታቸው ከመቀጠል ይቆጠባሉ::

7. በጎ ፈቃደኞች በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ከፍተኛ እስተ ዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ:: እንድ ሰው ጠቃሚ ነኝ ብሎ ሊያስብ የሚችለው፣ ተራ ነገሮችን እያከናወንኩ ነኝ ብሎ ሲያስብ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር ከፍተኛ ሥራዎችን እያደረግኩ ነው የሚል እምነት ሲኖረው ነው:: በጎ ፈቃደኞች በአገልግሎት አካባቢያቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ሊሰጣቸው ይገባል:: በጎ ፈቃደኞች እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደሚተማመንባቸው ማወቅ አለባቸው:: መሪዎች አሳባቸውን ጠይቀው ሊረዱ ይገባል:: ሽማግሌዎች በጎ ፈቃደኞች በሚያከናውኗቸው አገልግሎቶች ላይ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ፣ በጎ ፈቃደኞቹ አሳባቸውን ለሽማግሌዎች እንዲያካፍሉ መጋበዝ አለባቸው::

8. በጎ ፈቃደኞች ብዙውን ጊዜ ሥራ ስለሚበዛባቸው፣ ደመወዝ የሚከፈላቸውን ሰዎች ያህል በቂ ጊዜ የላቸውም:: በጎ ፈቃደኞቹ ትምህርታቸውን በማጥናቱ ሥራ ላይ የተጠመዱ ተማሪዎች፣ ልጆች ያሏቸው የቤት እመቤቶች፣ ሥራ ያላቸው ባለሙያዎች፣



ወይም በቤት ውስጥ ኃላፊነት ያለባቸው የቤተሰብ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ነገሮችን ከእነርሱ በመጠበቅ በጎ ፈቃደኞችን መበደል የለባቸውም:: በጎ ፈቃደኞች ብዙ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ከተጠየቁና ሌሎች ሥራ ዎቻቸው ከተናጉባቸው፣ የበጎ አድራጊነት ተግባራቸውን ሊያቋርጡ እንደሚችሉ መረዳቱ ጠቃሚ ነው:: ይህ እንዳይሆን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: በተጨማሪም በጎ ፈቃደኞች መደበኛ የሆነ የዕረፍት ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል:: ለምሳሌ፣ የልጆች የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ሆነው የሚያገለግሉ ከሆነ፣ ሁልጊዜም ከልጆች ጋር እንዲሆኑ ከማድረግ ይልቅ፣ አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ እንዲካፈሉ ማድ ረጉ ተገቢ ይሆናል:: በጎ ፈቃደኞች በሚሰጡት አገልግሎት ደስተኛ ካልሆኑ፣ አገልግሎቶችን በማቋረጥ እንደ ብዙዎቹ ምእመናን መኖራቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ:: ይህም በአገልግሎት ሳይሳተፉ ለአምልኮ ብቻ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ነው::

በጎ ፈቃደኞች ሌሎች ብዙ ኃላፊነቶች ስላሉባቸው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎቱን በሚመቻቸው ጊዜ የሚያከናውኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለባቸው:: ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ሁሉ የሚካሄዱት ከ2 ሰዓት እስከ 11 ሰዓት ብቻ ከሆነ፣ ሥራ ያላቸው ሰዎች ሊያገለግሉ አይችሉም ማለት ነው:: ነገር ግን አገልግሎቶቹ የበጎ ፈቃደኞቹን የጊዜ ችግር የሚያገናዝቡ ከሆኑና ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ ወይም ቅዳሜና እሑድ ቀን የሚከናወኑ አገልግሎቶች ካሉ፣ በጎ ፈቃደኞች በእነዚህ አገልግሎቶች ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ::

በተለይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከበፊት የተሻለ ጊዜ ያላቸውን ሰዎች ለአገልግሎት ሊያበረታቷቸው ይገባል:: ወጣት ጎልማሶች ሥራና የሚንከባከቧቸው ልጆች አሏቸው:: ነገር ግን ልጆች ትምህርት ቤት ከገቡ በኋላ፣ ወይም ሥራ የነበራቸው ሰዎች ጡረታ ሲወጡ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል የሚያስችል በቂ ጊዜ ይኖራቸዋል:: አረጋውያንን ለማገልገል እንደማይችሉ ከመመልከት፣ ወይም የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በወጣቶችና

በተማሩ ሰዎች ብቻ እንደሚካሄድ አድርጎ ከመመልከት ይልቅ፣ አረጋውያን በተቻለ መጠን አገልግሎት እንዲሰጡ ማበረታታት አለብን:: እነዚህ አባላት አሁን በጸሎት፣ ወይም ድሆችን በመርዳት፣ ወዘተ . . . ላይ ለማተኮር የሚያስችል በቂ ጊዜ አላቸው:: ብዙውን ጊዜ ለአገልግሎት ፈቃደኞች ሆነው የሚገኙት እነዚሁ አረጋውያን ናቸው:: እንዲሁም ደግሞ እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሔር መንግሥት ሊጠቀሙ የሚችሉት ብዙ ጥበብና የተከማቸ እውቀት አላቸው::

9. በጎ ፈቃደኞች አገልግሎታቸውን በሚጀምሩበት ጊዜ ግልጽ መመሪያዎችና ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል:: በጎ ፈቃደኞች አዲስ ኃላፊነት በሚሰጣቸው ጊዜ፣ ስለ አገልግሎቱ ብዙ ነገር ላያውቁና ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው እርግጠኞች ላይሆኑ ይችላሉ:: ስለሆነም፣ በአገልግሎቱ ክህሎትና ልምድ እስኪያገኙ ድረስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግልጽ መመሪዎችን ሊሰጧቸውና ሥራውን እስኪያውቁት ድረስ በቅርብ አብረዋቸው ሊሠሩ ይገባል::

10. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጎ ፈቃደኞች ነገሮችን በመሞከር የተሻለ ውጤት ለማምጣት በሚጥሩበት ጊዜ ነጻነት ሊሰጧቸው ይገባል:: በጎ ፈቃደኞች መሪዎች ተስፋ ባደረጉበት መንገድ የማይሠራ አንድ ነገር ቢያደርጉ እንኳን፣ አዳዲስ ነገሮችን መሞከራቸውን እንዲቀጥሉ ማበረታቻ መስጠቱ ተገቢ ነው:: በጎ ፈቃደኞች እንሳሳታለን በሚል ፍርሃት ከተጠመዱ፣ አገልግሎቱን በበለጠ ውጤታማ የሚያደርጉትን ነገሮች ከማድረግ ይልቅ መሪዎቹ የሚናገሩትን ብቻ ያከናውናሉ:: ስለ አገልግሎቶች የራሳቸውን አሳቦች እንዲያካፍሉ ማበረታታቱ ጠቃሚ ነው:: ብዙውን ጊዜ በጎ ፈቃደኞች ከቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ከቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች የተለዩ ሁኔታዎችን በመመልከት ጠቃሚ ምክር ሊሰጡ ይችላሉ::

11. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው የሰጠውን ራእይ እውን ለማድረግ በሚጥሩበት ጊዜ፣ ሌሎች ምእመናን የሥራው ተካፋይ እንዲሆኑ ማበረታታት ያስፈልጋቸዋል:: በሆነ መንገድ የአገልግሎት ተካፋይ የማይሆን አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊያድግ አይችልም::



12. በጎ ፈቃደኞች ለአገልግሎታቸው ደመወዝ ስለማይከፈላቸው፣ መሪዎች በሌሎች መንገዶች እነዚህን ወገች «መሸለም» አለባቸው:: ይህም በሕዝብ ፊት በሚሰጥ እውቅና፣ ወይም ሥራቸው ምን ያህል ጠቃሚ እንደ ሆነ ለመግለጽ የተዘጋጀ የምሳ (ወይም እራት) ግብዣ በማድረግ ሊገለጽ ይችላል:: በታማኝነት ላገለገሉት ሰዎች ስጦታ በማበርከትም ምስጋናችንን ልንገልጽላቸው እንችላለን::

| |
|---|
| 22ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን ደመወዝ ከሚከፈላቸው ሠራተኞች ይልቅ በቤተ ክርስቲያናችሁ በበጎ ፈቃደኞች ሊሠሩ የሚችሉትን ሥራዎች ዘርዝር:: ለ) መሪዎች ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እንዲሳተፉ ለማበረታታት ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ በበጎ ፈቃደኝነት በማገልገል ላይ ያሉትን ሰዎች ስም ዘርዝር:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህ ሰዎች በበለጠ እንዲሠሩ ለማበረታታት ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? |

## ሦስተኛ ቀን

ዘሪሁን ታዋቂ የቀጣና ኃላፊ ነበር:: ዋናው ጽ/ቤት እንዴት ዕቅዶችን ማውጣትና ራእይን መወሰን እንደሚችል ካሠለጠነው በኋላ፣ ዘሪሁን የተማረውን ትምህርት በሥራ ላይ ለማዋል ፈለገ:: ዘሪሁን ታዋቂ በመሆኑ፣ ብዙውን ጊዜ ጓደኞቹና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አባላት ወደ ቢሮው ጎራ ብለው ያነጋግሩት ነበር:: የሚመጡትም ለሁነኛ ጉዳይ ሳይሆን፣ እንዲሁ አብረውት ለመሆን ነበር:: ዘሪሁን ሥራ የሌላቸው ወዳጆቹን ለማስደሰት ስለሚፈልግ፣ በሚመጡበት ጊዜ ሥራውን ትቶ ያነጋግራቸውና ችግራቸውን ለመፍታት ይሞክር ነበር:: ሁልጊዜም ዘሪሁን «ለአካባቢዬ ራእይ ማዘጋጀት መጀመር አለብኝ» ይላል:: በየማታው ግን «ዛሬ በጣም ሥራ በዝቶብኝ ስለ ነበረ ያንን ራእይ አላዘጋጀሁትም:: ምናልባትም ነገ አሠራው ይሆናል» ይላል:: ብዙ ወራት አለፉ:: በዚህ ጊዜ ዘሪሁን ለቀጣናው ራእይና ዕቅድ ማውጣት ምን ጥቅም እንዳለው የተማረውን ዘንግቷል:: ስለዚህ ወደ ቢሮው ይመጣና የሚችለውን ነገር ያደርጋል:: በመጨረሻም፣ በቀጣናው የሚገኙ ሰዎች በዘሪሁን ሁኔታ እየተናደዱ መጡ:: «አሠራስሁ ይላል ግን ቃሉን አይጠብቅም:: በቀጣናችን ውስጥ ምንም ዓይነት እድገት

አይታይም:: ከቀን ቀን ለውጥ አይታይም» ሲሉ አማረሩ:: በቀጣዩ የምርጫ ጊዜ በዘሪሁን ቦታ ሌላ ሰው ተመረጠ::

23ኛ ጥያቄ:- መዝ. 90:1-12 አንብብ:: ሀ) ይህ ምንባብ ሕይወት አጭር ስለ መሆኗ ምን ያስተምራል? ለ) ጊዜያችንን በጥበብ ስለ መጠቀም ምን ያስተምረናል? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጠቃሚ ሥራ ሳይሠሩ ጊዜያቸውን ሊያባክኑ የሚችሉት እንዴት ነው?

መሪ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኒቱ እንዴት ማደግ እንዳለባት የሚያሳይ ግልጽ ራእይ ሊቀበል ይችላል:: ዝርዝር ዕቅዶችን ሊወጥን ይችላል:: ነገር ግን አንድ መሪ ጊዜውን ሊቆጣጠር ካልቻለ፣ እምብዛም ዘላቂ ውጤት ያለው ተግባር ሊያከናውን አይችልም:: ልክ እንደ ዘሪሁን፣ ጊዜውን የሚያባክነው ቤተ ክርስቲያኑን ሊያሳድጉ በማይችሉ ነገሮች ነው::

ሙሴ መዝሙር 90ን በሚጽፍበት ጊዜ፣ ስለ ሕይወቱ በማሰብ ምን ያህል አጭር እንደ ሆነ ተናግሯል:: ከዘላለም ጋር ሲነጻጸር፣ የምንረው 70 ወይም 80 ዓመት በጣም አጭር ነው:: ነገር ግን በመንግሥተ ሰማይ የሚሆነው ነገር የሚወሰነው በዚህች አጭር የምድር ላይ ቆይታችን ነው:: ስለሆነም፣ ሙሴ እግዚአብሔር የዘመኑን ቁጥር እንዲያስታውቀውና በጥበብ ለመኖር እንዲችል ጸልዮአል:: ሙሴ ለማለት የፈለገው እድሜያችን አጭር መሆኑን በመረዳት እንዳች ጠቃሚ ነገር ለማከናወን በምንፈልግበት ጊዜ አስፈላጊ የሆነውንና ያልሆነውን ነገር ለይተን ማወቅ እንዳለብን ነው:: ጊዜያችንን መጠቀም ያለብን አስፈላጊ በሆነው ነገር ላይ ነው:: የሕይወት ዓላማ ዝም ብሎ መኖር ብቻ ሳይሆን፣ ፍሬያማ ሕይወት መምራትና እግዚአብሔር የሚፈልግብንን ተግባር መፈጸም ነው:: ጥያቄው እንግዲህ «እግዚአብሔር የሰጠንን ሥራ እንጨርሳለን ወይስ የሰጠንን ጊዜ በአግባቡ ባለመጠቀም ሕይወታችንን እናባክናለን?» የሚል ነው:: ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ዕድሉ እያላቸው ጊዜያቸውን እንዲጠቀሙ አስጠንቅቋቸዋል:: ምክንያቱም ምንም ነገር መሥራት የማይቻልበት የጨለማ ጊዜ ይመጣልና (ዮሐ. 9:4):: በሕይወታችን መጨረሻ ላይ ጊዜያችንን መለስ ብለን በመመልከት «እግዚአብሔር



እንዳደርግ የፈለገውን ሁሉ አድርጌአለሁ» እንል ይሆን? ይህንን ለማለት ከፈለግን፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ጊዜ በአግባቡ የመጠቀምን ክህሎት ማወቅ አለብን::

## ክህሎት አሥር:- ጊዜያችንን በአግባቡ መጠቀም

**ብዙ መሪዎች ሥራ-ብዙ በመሆን በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት አስፈላጊ የሆኑትን በርካታ ሥራዎች የማያከናውኑት በሁለት ምክንያቶች ነው::**

በርካታ ሥራዎች እያሉ ትንሽ ጊዜ ብቻ በሚኖረን ጊዜ «በቂ ጊዜ የለኝም» ብለን እናማርራለን:: ይህ ግን ትክክለኛ አነጋገር አይደለም:: ለማከናወን የምንፈልገውን ለማከናወን የሚበቃ ጊዜ፣ በማይረን ጊዜ፣ በአብዛኛው ሁለት ችግሮች አሉ::

1. እግዚአብሔር ከሚፈልገው በላይ ስንሠራ::

እግዚአብሔር ሁልጊዜም እርሱ የሰጠንን ተግባር እንድናከናውን በቂ ጊዜ ይሰጠናል:: ይህ ሊሆን የሚችለው ጊዜያችንን በአግባቡ ከተጠቀምን ነው:: አንደኛው ችግር መሪዎች እግዚአብሔር ያልጠየቃቸውን ነገሮች ማድረጋቸው ነው:: እንደ መሪ ሌሎች ሰዎች የሚጠይቁንን ወይም እኛ ራሳችን የምንፈልገውን ሳይሆን፣ እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር ማድረጋችንን ማረጋገጥ አለብን::

ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት እግዚአብሔር የሰጠውን ሥራ ሁሉ እንዳከናወነ ተናግሯል (ዮሐ. 17:4 አንብብ):: አሁንም ገና ብዙ የሚሠራ ሥራ ነበር:: ፈውስ የሚያስፈልጋቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ:: ወንጌል ያልደረሳቸው ብዙ አገሮች ነበሩ:: ነገር ግን ኢየሱስ እግዚአብሔር እንዲያከናውን የፈለገውን አንድ ተግባር ማከናወኑን ተረድቷል:: በአጭር የምድር ላይ ቆይታው የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እንደ ተወጣ ለመመስከር ችሏል:: ሥራውን ሁሉ እንዳጠናቀቀ ለመናገር የቻለው ለዚህ ነው:: መጨረስ ያለባቸውን ሥራዎች በሙሉ ለመሥራት ባይችልም፣ እግዚአብሔር እንዲያከናውን የሚፈልገውን ሥራ ሠርቷል::

እግዚአብሔር እንድናከናውን የሰጠን ውስን «ሥራ» አለን:: ሁልጊዜ እግዚአብሔር የሰጠንን ሥራ ለማከናወን የሚበቃ ጊዜ አለን:: ሰዎች ይመጡና በኮንፍረንስ ወይም በቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ እንድንሰብክ ይጠይቁናል:: ቅር ልናሰኛቸው ስለማንፈልግ፣ «እሺ» እንሳለን:: ሌሎች ደግሞ የኮሚቴ ወይም የሆነ የአስተዳደር አካል እንድንሆን ይጠይቁናል:: እነርሱንም ለማሳዘን ስለማንፈልግ፣ እሺ እንላለን:: ብዙውን ጊዜ ሥራዎችን የምንሠራው እግዚአብሔር ስላዘዘን ሳይሆን፣ ሰዎችን ለማስደሰት ስለምንፈልግ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እዚያም እዚህም መሆንና በብዙ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለመሳተፍ ስለምንፈልግ በርካታ ኃላፊነቶችን እንወስዳለን:: ከሰይጣን ውሸቶች አንዱ ሥራ በዝቶብን የሚጠበቅብንን ሥራ ባናከናውን ወይም አጅግ ብንደክም፣ በጣም መንፈሳዊ ሆንናል የሚል ስሜት እንዲያድርብን ማድረጉ ነው:: ውጤታማነታችንን በጥድፊያ ብዛት እንለካለን:: ብዙውን ጊዜ ምን ያህል መሥዋዕትነት እየከፈልን መሆናችንን ሰዎች ይረዱልን ዘንድ ጥድፊያ እንደ በዛብን ለሰዎች እናወራለን:: ይህንን በምናደርግበት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወሳኝ የሆኑትን ነገሮች ለማከናወን ሳንችል እንቀራለን:: ሰዎች የሚፈልጉትን እያደረግን፣ እግዚአብሔ ር የሚጠይቀንን ሳናከናውን እንቀራለን:: ይህ ደግሞ ጊዜያችንንና መንፈሳዊ ስጦታዎቻችንን እንድናባክን ያደርገናል::

ለዚህ ችግር የእግዚአብሔር መፍትሔ «አይሆንም» ማለትን መማር ነው:: ብዙውን ጊዜ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉንም ነገር እንዲያደርጉ ስለሚጠብቁ፣ አይሆንም ማለቱ ከባድ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ምሩቃን በሁሉም የቀብር ሥነ-ሥርዓቶችና ሠርጎች ላይ እንዲገኙ፣ ሁልጊዜም እንዲሰብኩ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ እንዲያስተምሩ፣ ወዘተ. . . ይጠበቅባቸዋል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያኖቻችን ለመሥራት ለሚቀጠሩ ወገኖች ማሰብ አለባቸው:: ሁሉንም ነገር እንዲያከናውኑ በመጠየቅ አስፈላጊ ሥራዎችን ለመሥራት ወይም ቤተሰባቸውን ለመንከባከብ ጊዜ እንዳያገኙ ካደረግን፣ ሰይጣን እግዚአብሔር ያልጠየቃቸውን ሥራ እንዲያከናውኑ



እንድንጠይቃቸው እየፈተነን ነው ማለት ነው:: ይህ ደግሞ አገልጋዮችንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን ይጎዳል:: የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሏቸው ሰዎች እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውንና የማይፈልግባቸውን ሥራ ለይተው እንዲያውቁ በማገዝ ሊጠብቋቸው ይገባል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን ከሚፈሰግባቸው የበለጠ እንዲያከናውኑ ከሚጠይቁና «አይሆንም» የሚሰውን ቃል ሰመስማት ከማይፈልጉ ወገኖች መጠበቅ አለባቸው:: መሪዎቹ ራሳቸው በአገልጋዮቹ ፈንታ «አይሆንም» ማለት አለባቸው:: አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከሚገባው በላይ ከመሥራቱ የተነሣ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ተ ስፋ ቆርጦ ከሥራው ቢሰናበት፣ ይህ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ሰዎች ብዙ ነገሮችን ስለሚጠይቋቸውና «አይሆንም» ለማለት ስለሚቸገሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ከመጠን በላይ ኃላፊነቶችን ሲቀበሉ የተመለከትከበት ሁኔታ ካለ ግለጽ:: ለ) አገልጋዮች የተመጠነ የሥራ ጫና እንዲኖራቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሁሉንም ነገር ለማከናወን ከመጣር ይልቅ አስፈላጊ በሆኑ ሥራዎች ላይ እንዲያተ ኩሩ ለማገዝ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ዓይነት ሚና መጫወት አለባቸው? |

2. ብዙውን ጊዜ ጊዜያችንን በአግባቡ ስለማንጠቀም፣ በቂ ጊዜ የለንም ብለን እናስባለን:: ጊዜያችንን እምብዛም አስፈላጊ ባልሆኑ ነገሮች ላይ እናጠፋና ጌታ የሰጠንን አስፈላጊ ነገሮች ሳናከናውን እንቀራለን:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያን ያህል አስፈላጊ ያልሆኑትን ነገሮች በማከናወን ጊዜያቸውን ሊያባክኑ ይችላሉ:: ሠንጠረዦችንና ሪፖርቶችን እየሞሉ ሳይጸልዩ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ሳያጠኑ፣ ወይም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእይ እውን ለማድረግ የሚያስችሉትን ነገሮች ሳያከናውኑ ይቀራሉ: እንዲሁም ደግሞ ወደ ቢሮአችን ከሚመጡ ወዳጆቻችን ጋር በመጫወት፣ ሥራችንን ልክ በሰዓቱ ባለመጀመር፣ ለምሳ ረዘም ያለ ሰዓት በመውሰድ፣ ወዘተ. . . ጊዜያችንን ልናባክን እንችላለን:: ሰይጣን

የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ለእግዚአብሔር መንግሥት ወሳኝ የሆኑትን ነገሮች ሳያደርጉ ወዲያ ወዲህ እያሉ በጥድፊያ ጊዜያቸውን እንዲያባክኑ ለማድረግ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል።

> 25ኛ ጥያቄ:- ሀ) ትናንት ጊዜህን እንዴት እንዳሳለፍክ አስብ። ያከናወንካቸውን ነገሮች ዘርዝርና እያንዳንዱ ጉዳይ ምን ያህል ጊዜ እንደ ፈጀብህ ግለጽ። ለ) ካደረግካቸው ነገሮች ውስጥ ለእግዚአብሔር መንግሥት ይጠቅማል ብለህ በምታስባቸው ነገሮች ጎን «ጠቃሚ» ብለህ ጻፍ። ለእግዚአብሔር መንግሥት በማይጠቅሙ ነገሮች አጠገብ «የማይጠቅም» ብለህ ጻፍ። ሐ) አሁንም የዘረዘርካቸውን ነገሮች በመመልከት የወሰዱትን ጊዜ አጢን። የጊዜ ብክነት ባላስከተሉት ነገሮች ላይ «በጥሩ ሁኔታ ያለፈ ጊዜ» የሚል ጻፍ። የጊዜ አጠቃቀምህን ባለመቆጣጠርህ ምክንያት በባከኑት ጊዜያት አጠገብ «የባከነ ጊዜ» የሚል ጻፍ። መ) ጊዜህን ይበልጥ በማስተዋል ልትጠቀም ትችል የነበረው እንዴት ነበር?

## ጊዜ በኋላ አቆይተን ልንጠቀምበት የማንችለው ከእግዚአብሔ ር የተሰጠን ሀብት ነው

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው እኩል ጊዜ ይሰጣል። ድሆች ወይም ሀብታሞች፣ የተማርን ወይም ያልተ ማርን፣ ትልቅ ሥራ ያለን ወይም ትንሽ ሥራ ያለን፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ወይም አባላት ብንሆን፣ እግዚአቁሔር ለሁላችንም በየቀኑ የሚሰጠን እኩል ጊዜ ነው። ይህ በሕይወት ውስጥ ለሁሉም ሰው እኩል ከሚደርሱ ጥቂት ነገሮች አንዱ ነው። ሰዎች የተለያዩ ስጦታዎችና ችሎታዎች ቢኖራቸውም፣ እግዚአብሔ ር ለሁሉም የሚሰጠው ጊዜ እኩል ነው።

በቤተ ክርስቲያን አመራራችንና አገልግሎታችን ውጤታማ ለመሆን ከፈለግንና በሕይወታችን መጨረሻ ላይ «እግዚአብሔር እንዳደርገው የሰጠኝን ሥራ አጠናቅቄአለሁ» ለማለት ከፈለግን፣ ጊዜያችንን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደምንችል ማወቅ አለብን። ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠን ልክ እንደ ገንዘብ ያለ ሀብት መሆኑን ማወቅ አለብን። ሰዎችም ለእግዚአብሔር መንግሥት



በማስተዋል ልንጠቀም የሚገቡን ሀብት ናቸው። ከገንዘብና ሰዎች በተለየ መንገድ ጊዜ ተጠቀምንበትም አልተጠቀምንበትም ማለቁን ይቀጥላል። ገንዘባችንን ባንክ ቤት አስቀምጠን በኋላ ልንጠቀምበት እንችላለን። የተለያዩ ስጦታዎች ያሏቸው ሰዎችም ነገ እግዚአብሔ ርን ሊያገለግሉ ይችላሉ። ጊዜ ግን ተጠቀምንበትም አልተ ጠቀምንበትም ያልፋል። እግዚአብሔር ለኢያሱ ካደረገው በተለየ መንገድ ጊዜ አስፈላጊ ነገሮችን አከናውነን እስክንጨርስ ድረስ ቆሞ አይጠብቀንም (ኢያሱ 10)። እኛ ብንተኛ፣ ብንመገብ፣ ብንነጋገር፣ ወይም ብንሠራ ደቂቃዎችና ሰዓታት ወደፊት ከመግፋት አይቦዝኑም።

አንተ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነህ እንበል። አንድ ሀብታም ሰው ወደ አንተ መጥቶ፣ «በየቀኑ ለቤተ ክርስቲያን ሥራ 240 ብር እሰጥሃለሁ። ነገር ግን ገንዘቡን በሙሉ በየቀኑ የማትጠቀም ከሆነ፣ ለእኔ መመለስ አለብህ» ይልሃል። በየቀኑ ሀብታሙ ሰውዬ ገንዘቡን ይሰጥሃል። አንተም የሠራተኛ ደመወዝ በመክፈል፣ መጋረጃዎችን በመግዛት፣ ለሰንበት ትምህርት ቤት መጻሕፍትን በመግዛት፣ ወዘተ. . . ትጠቀምበታለህ። ነገር ግን አንዳንድ ቀን በሌሎች ሥራ ዎች ተጠምደህ ትውልና 40 ብር ብቻ ትጠቀማለህ። ማታ ሀብታሙ ሰውዬ ሊመጣ 200 ብር መመለስ አለብህ። 200 ብር ለቤተ ክርስቲያን የመጠቀም ዕድልህን አጥተሃል ማለት ነው። በተ መሳሳይ መንገድ፣ እግዚእብሔር 24 ሰዓታትን በየቀኑ ይሰጥሃል። እነዚህን ሰዓታት በማስተዋል መጠቀም ይጠበቅብናል። ነገር ግን ማንም ሰው ለሚቀጥለው ቀን ቆጥቦ ሊያሳድር አይችልም። ለዘላለም ለውጥ የሚያመጣ ተግባር በማከናወን ጊዜን በአግባቡ መጠቀም አለመጠቀምህ ዛሬ በአግባቡ በመጠቀምህ ላይ ይወሰናል።

እያንዳንዳችን በየቀኑ 24 ሰዓታት አሉን። ጥያቄው እንግዲህ ይህንን ጊዜ እንዴት እየተጠቀምን ነው? የሚል ነው። እንበልና በቀን ስምንት ሰዓት ብንተኛና ሦስት ሰዓታት በምግብ ላይ ብናጠፋ፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ልንጠቀም የምንችለው 13 ሰዓታትን ብቻ ነው ማለት ነው። የመንግሥት ሥራ የምንሠራ ከሆነ፣ በቀን ስምንት ሰዓት ያህል ለዚህ ሥራ እንጠቀማለን ማለት

ነው:: ከዚህ በኋላ ለእግዚአብሔር መንግሥትና ለቤተ ሰባችን የቀ ረን አምስት ሰዓት ይሆናል:: በእነዚህ ሰዓታት ምን እያደረግን ነው?

በቀን 13 ሰዓታት ለእግዚአብሔር መንግሥት ማዋል የሚጠበቅብህ አገልጋይ ነህ እንበል:: ለ8 ሰዓታት ደመወዝ ይከፈልሃል:: የቀሩት 5 ሰዓታትም ለእግዚአብሔር ሥራ የሚውሉ ናቸው:: ነገር ግን በየቀኑ ጠዋት ሁለት ሰዓት ላይ ሥራ መግባት ሲኖርብህ፣ አንተ ሦስት ሰዓት ላይ ትመጣለህ:: ከሰዓት ደግሞ 11 ሰዓት ላይ ትወጣለህ:: ይህ ማለት በቀን ለ7 ሰዓታት ብቻ ሠርተ ሃል ማለት ነው:: ይህ ደግሞ በቀን 1 ሰዓት፣ በሳምንት 6 ሰዓታት፣ በዓመት 312 ሰዓታት እንድታባክን ያደርግሃል:: ይህ ጊዜ የባከነው እንግዲህ ለእግዚአብሔር መንግሥት እምብዛም ጠቀሜታ በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ነው ማለት ነው:: (ማስታወሻ:- በቀን ስምንት ሰዓት እንድትሠራና በሳምንት ስድስት ቀናት እንድትሠራ የ600 ብር ደመወዝ የሚከፈልህ ከሆነ፣ በቀን የምታገኘው ብር 3.15 ያህል ነው ማለት ነው:: በመሆኑም በዓመት ውስጥ 982.80 ብር የሚያወጣ ጊዜ አባክነሃል ማለት ነው:: ይህ ደመወዝ የሚከፈልህን ስምንት ሰዓት የሚመለከት እንጂ ተጨማሪ አምስት ሰዓቱን ሳያጨምር ነው::)

ጊዜን ማባከን ወይም አላግባብ መጠቀም እግዚአብሔር የሰጠንን ዋጋ ያለው ሀብት እንደ ማባከን ነው:: **የቤተ ክርስቲያን ቅጥር ሠራተኞች ሆነን ሳለን፣ ባለን ችሎታ ሁሉ የማንሠራ ከሆነ፣ ከቤተ ክርስቲያንና ከእግዚአብሔር «እየሰረቅን» ነው ማለት ነው::**

26ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች የሚያደርጓቸውና ጊዜ የሚያባክኑ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ጊዜ ማባከን የሚመስሉና ዘላለማዊ ጠቀሜታ ያላቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

የሕይወታችን እያንዳንዱ ቅጽበት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው:: ጥያቄው እንግዲህ «ጊዜያችንን እናባክናለን ወይስ ጥሩ የጊዜ ባለ አደራዎች በመሆን ለዘለቄታዊ ነገር እንጠቀምበታለን?» የሚለው ነው:: ጊዜን መቆጣጠር አንችልም:: ልንቆጣጠር የምንችለው የጊዜ አጠቃቀማችንን ብቻ ነው:: በጊዜያችን ተጠቅመን አንድ ጠቃሚ



ነገር ካልሠራን፣ አያባክንነው ነው ማለት ነው:: ይህ ለእግዚአብሔ ር የሚጠቅም ሥራ የምንሠራበትን ዕድል ያሳጣናል:: ይህ ማለት ግን በፍጥነት ከአንዱ ሥራ ወደ ሌላው መሄድ አለብን ማለት አይደለም:: ከክርስቶስ ሕይወት እንደምንመለከተው እርሱ በጥድፊያ የሚባክን ሰው አልነበረም:: ቀኑን ሁሉ በዝግታ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ተግባር ነበር የሚያከናውነው:: በሕይወቱ መጨረሻም ላይ እግዚአብሔር እንዲያከናውን የሰጠውን ተግባር በሙሉ እንዳከናወነ ተናግሯል:: እኛም የምንሞትበት ጊዜ ሲደርስ እንደዚህ እንድንል ጌታ ይርዳን!

## ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ራእዮችንና ዕቅዶችን ወደ እውነታነት ይቀይራል::

ለአንደ መሪ የሚያስፈልጉ ሁለቱ የመጀመሪያ ክህሎቶች ለቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ዘንድ ራእይን መቀበልና ራእዩ እውን የሚሆንባቸውን ዕቅዶች ማውጣት እንደ ሆነ ተምረናል:: እስካሁን ድረስ ግን ዕቅዱ ከወረቀት አላለፈም ወይም ገና እውን አልሆነም:: ማንኛውም ዕቅድ እውን ለመሆን ካልቻለ፣ ዋጋ የለውም:: ይህ ለእግዚአብሔር ተግባራዊ የማናደርገውን ቃል እንደ መግባት ነው:: አንድ ዕቅድ እውን የሚሆነው ደግሞ መሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ ሲጠቀሙ ነው::

አንድ ሰው እንዳለው፣ *«የስኬታማ ሰዎች ትልቁ ቁም ነገር ተ ግቶ መሥራት፣ ጥሩ ዕድል፣ ጥሩ የሰዎች ግንኙነት መኖር ሳይሆን፣ ወሳኝ የሆኑትን ነገሮች የማስቀደም ችሎታ ነው::»* ስለ ሆነም፣ አንድ መሪ እግዚአብሔር እንዲከናወን ይፈልጋል ብሎ ስሚያምነው ነገር ዕቅድ ማውጣቱ አስፈላጊ ቢሆንም፣ ይህ ግን የግድ ውጤታማ (ጥሩ) መሪ አያደርገውም:: ከሰዎች ጋር የመሥራትና ውክልና የመስጠት ብቃት ሊኖረው ይችላል:: ይህም ሆኖ አሁንም ጥሩ መሪ ላይሆን ይችላል:: በዋናነት ጥሩ መሪ እግዚአብሔር የሰጠውን ሥራ ለማከናወን ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም መቻል አለበት:: ተግቶ መሥራቱ ብቻ ሳይሆን፣ ትጋቱን የሚያሳየው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ወደሚፈልግበት ስፍራ እንድትደርስ በሚያግዙ ሥራዎች ላይ ጊዜውን በማዋል ነው::

**ጊዜን በአግባቡ መጠቀም የጊዜ አጠቃቀማችንን መቆጣጠርን ይጨምራል።**

ጳውሎስ በገላትያ 1:10 ላይ እንዳለው፣ እኛ ወይ የስዎች አለያም የክርስቶስ ባሪያዎች ነን፣ በአንድ ጊዜ የሁለቱም ባሪያዎች ልንሆን አንችልም። ይህም ማለት እኛ እንዴት እንደምንኖር እና ምን እንደምናምን ሰዎች እንዲወስኑልን ከፈቀድንላቸው፣ ያኔ ባሪያ ዎቻቸው ነን ማለት ነው። ወይም ደግሞ ጊዜያችንን እንዴት እንደምንጠቀም የሚወስኑልን ሰዎች ከሆኑ፣ ጌቶቻችን ናቸው ማለት ነው። ነገር ግን የምናምነውን የምንወስነው እኛ ከሆንን እና ክርስቶስ የሚፈልገውን የምናደርግ ከሆነ፣ የክርስቶስ ባሪያዎች ነን። ወደ ጊዜ አጠቃቀማችን ስንመጣ፣ ከጊዜ ጋር ሦስት ዓይነት ግንኙነቶች ሊኖሩን ይችላሉ።

1. *ጊዜ ሊቆጣጠረን ይችላል።* ይህ ማለት የሚያጋጥመን ነገር ሁሉ የምናደርገውን ነገር እንዲቆጣጠር መፍቀድ ማለት ነው። ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወደ ቢሮአቸው ይመጡና ጠቃሚ ነገሮችን ለማከናወን ቀኑን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ዕቅድ ሳያወጡ ያጋጠማቸውን ነገር ያከናውናሉ። አንድ ሰው መጥቶ ስለ ገንዘብ ችግር ካናገራቸው፣ ስለ ገንዘብ ችግር መናገራቸውን ይቀጥላሉ። ወንጌላዊ ከመጣ፣ ስለ ወንጌል ስርጭት ያወራሉ። ዝም ብሎ ለመጫወት የመጣ ሰው ካለም፣ ቁጭ ብለው ያወራሉ። ደብዳቤ ከመጣላቸው ያነብቡታል። አንድ ሰው መጥቶ ስለ አንድ ጉዳይ ካልጠየቃቸው ቀደም ብለው አስፈላጊውን ጉዳይ አያከናውኑም። እንዲህ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጊዜ ያቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙ ሳያስቡ ከአንድ ጉዳይ ወደ ሌላው ጉዳይ ማለፍን ያዘወትራሉ። ትኩረት የሚሰጡት አስቸኳይ በሆኑ ወይም ከፊታቸው ባጋጠሟቸው ነገሮች ላይ ነው። ለነገሮች ቅድሚያ ሰጥተው አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማከናወን አይሞክሩም።

2. *ሰዎች የጊዜ አጠቃቀማችንን ሊቆጣጠሩ ይችላሉ።* አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም አገልጋይ ጠንቃቃ ካልሆነ፣ ሌሎች ሰዎች የጊዜ አጠቃቀሙን እንዲቆጣጠሩ ሊያደርግ ይችላል። አንድ



የቤተ ክርስቲያን መሪ ሥራ የሌለው ጎደኛው ቢሮው ቁጭ ብሎ እንዲያዋራው ከፈቀደ፣ ጎደኛው የጊዜ አጠቃቀሙን እንዲወስን አደ ረገ ማለት ነው። አንድ አገልጋይ «ይህን ሳደርግ አልችልም» ለማለት የሚፈራና ሰዎች እንዲያከናውን የሚጠይቁትን ሁሉ በእሺታ የሚያከናውን ከሆነ፣ ሰዎች የጊዜ አጠቃቀሙን እንዲወስኑ አደረገ ማለት ነው። መሪዎች ሰዎች የሚያከናውኗቸውን ተ ግባራትና የጊዜ አጠቃቀማቸውን እንዲወስኑ በሚፈቅዱበት ጊዜ በጊዜ አጠቃቀማቸው ረገድ የሕዝቡ ባሮች ሆኑ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ መሪ፣ «እግዚአብሔር እንዳከናውን የሰጠኝን ሥራ እንዳጠናቅቅ የሚያግዙኝ አስፈላጊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?» የሚል ጥያቄ አያነሣም።

3. *በምናከናውናቸው ተግባራት ላይ ውሳኔዎችን በመስጠት የጊዜ አጠቃቀማችንን እንቆጣጠራለን።* በዋናነት፣ ጥያቄው «ጊዜ ያችንን በጥሩ ሁኔታ እንጠቀማለን ወይ?» የሚለው ሳይሆን፣ «እኛ ና የምናከናውናቸው ነገሮች አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ላይ ይመሠረቱ ዘንድ ሕይወታችንን እየተቆጣጠርን ነው ወይ?» የሚለው ነው። ለእግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን የሚያከናውን መሪ ጊዜውን እንደ እግዚአብሔር ባሪያ የሚጠቀምና ሕዝቡን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው መንገድ የሚመራ መሪ ነው። መሪው የጊዜን ሀብት እንዴት እንደሚጠቀም ይወስናል። በአስፈላጊነት ቅደም-ተከተላቸው ለእግዚአብሔር ክብር ማከናወን ያለባቸውን ነገሮች ለመፈጸም ጊዜ ውን ይጠቀማል። የጊዜ አጠቃቀም የተመሠረተው ለእርሱ ቀላል፣ አስደሳች ወይም ሌሎች ሰዎች በሚፈልጉት ነገር ላይ አይደለም።

**27ኛ ጥያቄ፡-** ባለፈው ሳምንት የጊዜ አጠቃቀምህ ምን ይመስል እንደ ነበ ረ ገምግም። ሀ) ጊዜ አንተን የተቆጣጠረባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) ሰ ዎች የጊዜ አጠቃቀምህን የተቆጣጠሩባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ሐ) የጊዜ አጠቃቀምህን ራስህ የተቆጣጠርክባቸውን መንገዶች ዘርዝር። መ) ካከናወንካቸው ተግባራት አብዛኞቹ በሰዎች አሳብ ሳይሆን በአንተ ውሳኔ ይሆን ዘንድ ምን የተለየ ነገር ልታደርግ ትችል ነበር?

የጊዜ አጠቃቀሙን የማይቆጣጠር ሰው ብዙውን ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አንዱ የሆነውን «ራስን መግዛት» ያልተማረ ነው (ገላ.

5:22-23)። ጊዜያችንን ለእግዚአብሔር ክብር መጠቀም አለመጠቀማችንን የምናውቀው ጊዜያችንን እንዴት እየተጠቀምን እንደ ሆነ ስንገመግም ብቻ ነው። በምን መንገዶች ጊዜያችንን እያባከንን እንደ ሆነ በመረዳት እግዚአብሔር የሰጠንን ጊዜ ለእርሱ ክብር እንዴት ማዋል እንዳለብን መማር አለብን።

## ውጤታማ አመራር የሚወሰነው አስቸኳይ ከሆኑ ነገሮች ይልቅ አስፈላጊ ነገሮችን በማድረግ ላይ ነው።

1. በአስቸኳይና አስፈላጊ ነገሮች መካከል ያሉትን ልዩነቶች መረዳት።

በየቀኑ የጊዜ አጠቃቀማችንን ለመወሰን የሚፈልጉ ሁለት ዓይነት ጉዳዮች ይገጥሙናል።

አንደኛ፣ ሁኔታዎች አስቸኳይ ወይም አስቸኳይ ያልሆኑ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። አንዳንድ ነገሮች በፍጥነት መከናወን ያለባቸው ናቸው። ሌሎች ደግሞ ፈጣን ምላሽ የማይጠይቁ ናቸው። ቢሯችን ቁጭ ብለን እየሠራን ሳለ ስልክ ጮኸ እንበል። እንሡሻ እያለ ስለሚጮህ ወዲያውኑ ለማንሣት እንፈልጋለን። የሚጮህ ስልክ እንድናነሣው የሚጠይቅ አስቸኳይ ጥሪ ነው። ሌላው ደግሞ አንድ ሰው ወደ ቢሮአችን ቢመጣና ለእርዳታ ከአገሌ ጋር ተነጋገሩ ለማለት የምንችለው ሰው በቢሮው አካባቢ ከሌለ፣ ከግለሰቡ ጋር መነጋገር ስላለብን አስቸኳይ ጉዳይ ሆነብን ማለት ነው። ባናነጋግረው፣ ስሜቱ ሊጎዳ ይችላል። ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን እድገት በተወጠነው ራእያችንና ዕቅዳችን ላይ መሥራት ቢኖርብን፣ ይህ አስቸኳይ ጉዳይ አይሆንም። በቤተሰብ መካከል መልካም ግንኙነትን ለመመሥረትና ልጆቻችንን በጌታ መንገድ ለማሳደግ በማሰብ ከቤተሰባችን ጋር የምናሳልፈውም ጊዜ አስቸኳይ አይደለም። ሌላ እመቴ ጊዜ እናደርገዋለን በማለት አስቸኳይ ያልሆኑትን ነገሮች ልናስተላልፍ እንችላለን።

> 28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) መሪዎችን የሚያጋጥሙ አስቸኳይ ነገሮች ምን ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ዘርዝር። ለ) የመሪዎችን ጊዜ የሚወስዱና ዳሩ ግን አስቸኳይ ያልሆኑ ነገሮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?



ሁለተኛ፣ ሁኔታዎችን አስፈላጊ ወይም አላስፈላጊ ብለን ልንመድብ እንችላለን። ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች ተጠቅመን እንወያይ። የሚጮኸውን ስልክ የደወለው ስልክ ቁጥሩን የተሳሳተ ሰው ወይም ትናንትና ያገኘኸውና ሥራ ስለሌለው ሰላም ለማለት የፈለገው ጓደኛህ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ አንተን ለማነጋገር የፈለገው ሰው ነገ ወደ ሌላ ከተማ ለመሄድ ሲዘጋጅ የሚሠራው ስለሌለው እግረ መንገዱን ከአንተ ጋር እየተጫወተ ጊዜውን ለማሳለፍ ፈልጎ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ነገሮች ጊዜያችንን ይወስዳሉ። ነገር ግን ዘለቄታዊ ጥቅም ያለው ተግባር የማከናወን አቅም የላቸውም። አስፈላጊ ነገሮች አይደሉም። በቤተ ክርስቲያን ራእዮችና ዕቅዶች ላይ መሥራት ግን አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያንን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ደረጃ ለማድረስ የሚያስችሉን እነዚህ ነገሮች ናቸውና። የአመራር ውጤታማነት የሚለካው ቤተ ክርስቲያንን ወደ መንፈሳዊ እድገት ለመምራት በመቻላችን ነው። ከቤተሰባችን ጋር ጊዜ ካልወሰድን፣ ልጆቻችን ከእምነት ሊያፈነግጡ ይችላሉ። ከሚስታችን ጋር ያለን ግንኙነትም ሊበላሽ ይችላል። ይህ አስፈላጊ ነገር መሆኑ ግልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ልጆቻችንን በትክክል ካላሳደግንና ከሚስታችን ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ከሌለን፣ ለአመራር ብቁ አለመሆናችንን ይናገራል (1ኛ ጢሞ. 3:4-5)።

> 29ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አስፈላጊ ያልሆኑና የመሪዎችን ጊዜ የሚወስዱ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ለ) እግዚአብሔር ለአንድ መሪ የሰጠውን ሥራ ለማጠናቀቅ አስፈላጊ የሆኑና ዳሩ ግን ብዙውን ጊዜ መሪዎች ወደ ዳር የሚገፏቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

ከእነዚህ ምሳሌዎች አንድ አስፈላጊ እውነት እንመለከታለን። አስቸኳይ የሆኑ ነገሮች ያን ያህል አስፈላጊዎች አይደሉም። ብዙውን ጊዜ ለአስቸኳይ ነገሮች እንዴት ምላሽ እንደምንሰጥ ከማሰብ ይልቅ፣ በእነዚህ ጉዳዮች ጊዜያችንን እናባክናለን። የበለጠ አስፈላጊ የሚሆኑት አስቸኳይ ያልሆኑ ነገሮች ናቸው። አስቸኳይ ነገሮች ላይ ለመሥራት የአኛን ቁርጥ ውሳኔ ይጠይቃል። ውጤታማ መሪዎች መሆን አለመሆናችንን የሚወስነው አስቸኳይ ነገሮችን ማድረግ አለማድረጋችን ነው። ጊዜያችንን ሁሉ አስቸኳይ

ለሚመስሉና አስፈላጊ ላልሆኑ ነገሮች ከሰጠን፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ውድ የጊዜ ሀብት እናባክናለን:: ውጤታማ መሪነት አስፈላጊውን ነገር ለማከናወን እንችል ዘንድ የጊዜ አጠቃቀማችንን የመቆጣጠር ውጤት ነው:: አንድ ደራሲ እንደ ተናገረው፣ ከጊዜያችን 80 በመቶውን በመጠቀም ወሳኝ ናቸው ከምንላቸው ነገሮች መካከል 20 በመቶዎቹን ብናከናውን፣ ውጤታማ መሪዎች ልንሆን እንችላለን:: ካለን ጊዜ በላይ ጥሩዎች የሚመስሉ ነገሮች ሁልጊዜም ይገጥሙናል:: ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ትንሽ ትንሽ ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ፣ ወሳኝ በሆኑ ነገሮች ላይ ብናተኩርና እነዚህኑ ነገሮች ብናከናውን ውጤታማ እንሆናለን:: ውጤታማ አመራር ማለት ጊዜያችንን አስፈላጊ በሆኑ ወይም ቅድሚያ በሰጠናቸው ጉዳዮች ላይ ማዋል ማለት ነው:

> 30ኛ ጥያቄ:- ሉቃስ 10:38-42 አንብብ:: ሀ) ክርስቶስ ማርያም ያደረገችው ከማርታ ይልቅ እንደሚሻል የተናገረው ለምንድን ነው? ለ) ከዚህ ለኢየሱስ አንድ ነገር አደርጋለሁ ብሎ ጠደፍ ጠደፍ ከማለት ይልቅ፣ አስፈላጊና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ስለ ማከናወን ምን እንማራለን?

2. አንድ ነገር አስፈላጊ መሆን አለመሆኑን እንዴት እንደምንወስን::

አስፈላጊ የሆነውንና ያልሆነውን ነገር የምናውቀው እንዴት ነው? ብዙውን ጊዜ አላስፈላጊ የሚመስለው ነገር አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን:: አንድ ቀን ኢየሱስ ማርያምና ማርታ የሚባሉ ወዳጆቹን ሊጎበኝ ሄደ:: ማርታ ለወዳጇ ለኢየሱስና ለደቀ መዛሙርቱ ምግብ ለመሥራት ስትል ጊዜዋን ማእድ ቤት ውስጥ ደፋ ቀና ስትል አሳለፈች:: እኅቷ ማርያም ግን ሳሎን ተቀምጣ የኢየሱስን ትምህርት ትሰማ ነበር:: ማርታ ሥራውን በሙሉ ብቻዋን በመሥራቷ ተናድዳ ወደ ኢየሱስ በመምጣት ማርያም ሥራ ታግዛት ዘንድ እንዲነግራት ጠየቀችው:: በዚያን ዕለት ኢየሱስ ለማርታ አንድ ጠቃሚ ትምህርት አስተማራት:: ጠቃሚ ነገሮችን ሳያደርጉ ለኢየሱስ ወዲያ ወዲህ እያሉ መጣደፍ ይቻላል:: ምግብ ጥሩ ነገር ነው:: ነገር ግን ከኢየሱስ እየተማሩ ማሳለፉ የበለጠ ጠቃሚ ነው:: እንደ ማርታ እኛም በሥራ መጠመድ ብቻ በቂ



እንዳልሆነና አስፈላጊውን ነገር ማከናወን ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት አለብን:: ስለሆነም፣ ኢየሱስ አስፈላጊ ነው የሚላቸውን ነገሮች ማከናወናችንን ማረጋገጥ አለብን:: አስፈላጊ የሆነውን ነገር ለማወቅ «አንድን ነገር ማድረግ ወይም አለማድረግ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? ይህ እግዚአብሔር እንዳደርገው የሰጠኝ ሥራ ነው?» የሚል ጥያቄ ማንሣት አለብን::

አስፈላጊ የሆነው ነገር ብዙውን ጊዜ የሚሽከረከረው በሁለት ነገሮች ላይ ነው::

*ሀ.* **ግንኙነቶችን መጠበቅና ማጎልበት::** ክርስቶስ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሁለት ግንኙነቶች እንደሚታወቅ ተናግሯል:: በሁለንተናችን እግዚአብሔርን እንድንወድ ታዝዘናል:: እንዲሁም ደግሞ ራሳችንን የምንወደውን ያህል ሰዎችን እንድንወድ ታዝዘናል (ማቴ. 22:34-40):: በግንኙነቶች ስኬታማ መሆን ማለት ግንኙነቶችን በሚከተለው ቅደም ተከተል መጠበቅ አለብን ማለት ነው::

1) ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት:- እንደ መሪዎችን ነገሮችን ምንም ያህል የማከናወን ብቃት ቢኖረን፣ ከእግዚአብሔር ጋር እያደገ የሚሄድ ግንኙነት ከሌለን፣ መውደቃችን የማይቀር ነው:: በሕይወት ውስጥ የጳውሎስ ዓላማ ክርስቶስን፣ የክርስቶስን ፍቅር፣ ኃይሉንና የመከራውን ኅብረት ማወቅ ነበር (ፊልጵ. 3:7-14):: ይህ ለሁሉም አማኝ በተለይም ለመሪዎች ከሁሉም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ነው:: በብዙ ነገሮች እየተጠመዱ ከሰማያዊ አባታችን ጋር እያደገ የሚሄድ ግንኙነት አለመመሥረት በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ስኬታማ እንዳንሆን ያደርገናል:: እንደ መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያንና በሁኔታዎች ውስጥ ያለው ፈቃዱን መሻት አለብን:: አስፈላጊ ውሳኔዎችን ያለ ጸሎት የምንወስን ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን ምሪት ሳይጠብቅ በሩጫ ሄዶ መሥዋዕት እንዳቀረበው ንጉሥ ሳኦል መሆናችን ነው (1ኛ ሳሙ. 13:5-14):: የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ፣ በመጸለይ ወይም እግዚአብሔርን በማዳመጥ ጊዜ የማናሳልፍ ከሆነ፣ ሥራ ሊበዛብን

ቢችልም፣ ወሳኝ የሆነውን ነገር እያደረግን አይደለንም ማለት ነው።

2) <u>ከቤተሰቦቻችን ጋር ያለን ግንኙነት</u>፡- የሚያሳዝነው፣ ብዙ መሪዎች ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ያለውን ግንኙነት ቸል ይላሉ። የቤተሰቦቻችን ፍላጎት ብዙውን ጊዜ እንደ አስቸኳይ ነገር የሚታይ አይሆንም። እንዲያውም፣ አንዳንድ ጥሩ አስተሳሰብ ያላቸው መሪዎችና አገልጋዮች መሪዎችን፣ «ስለ ቤተሰባችሁ አትጨነቁ። እግዚአብሔር ይንከባከባቸዋል» ይላሉ። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታችን ቤተሰቦቻችንን የሚያጠፋ ከሆነና ልጆቻችን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ የሚያደርግ ከሆነ፣ ዋጋ የለውም። የአንዳንድ መጋቢዎች ሚስቶች በባሎቻቸው ቸል ስለሚባሉ የወሲብ ኃጢአት የሚፈጽሙበት ጊዜ አለ። ባሎቻቸውን የሚፈቱም አሉ። አገልጋዩ አስፈላጊውን ቤተሰባዊ ግንኙነት ቸል ስላለ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግልበት ሁኔታ ያበቃል።

3) <u>አብረውን ከሚሠሩ ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት</u>፡- መሪዎችና አገልጋዮች እርስ በርሳቸው ከሌሎች ሽማግሌዎች፣ ከወንጌላውያን፣ ከሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች፣ ከመዘምራን፣ ከመጋቢዎች፣ ወዘተ. . . ጋር አብረው ይሠራሉ። አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በእነዚህ ግንኙነቶች የማያድግ ከሆነ፣ ሰዎች በራሳቸው ፍላጎት ላይ በማተኮር የእግዚአብሔርን መንግሥት ጉዳይ ችላ ስለሚሉ፣ የእግዚአብሔር ሥራ ይጎዳል፣ ክፍፍልም ይፈጠራል።

4) <u>ከምእመናን ጋር ያለን ግንኙነት</u>፡- የቤተ ክርስቲያን መሪነት የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእረኝነት የማገልገል ጉዳይ ነው። አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዕቅዶችን በማውጣቱ በኩል ስኬታማ ከሆነና ከምእመናን ጋር የቅርብ ግንኙነት ከሌለው፣ ሊከተሉት አይችሉም፤ እርሱም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ሊረዳቸው አይችልም።

5. <u>ከማኅበረሰባችን አባላት ጋር ያለን ግንኙነት</u>፡- ኢየሱስ በአካባቢያችን ላለው ዓለም ጨውና ብርሃን እንድንሆን አዝዞናል



(ማቴ. 5፡13-16)። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከማኅበረሰቡ አባላት ጋር አዎንታዊ ግንኙነት ከሌላቸው፣ ሰዎች ወደ እምነት እንዳይመጡ ይገፋሉ። ይህም ሰዎች የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሊሆኑ የሚችሉበትን ትልቅ አገልግሎት ማደናቀፍ ነው።

የአመራር ውጤታማነት በግንኙነቶች ላይ የተመሠረተ ነው። ውጤታማነት ደግሞ እነዚህ ሁሉ ግንኙነቶች ጤናማ በመሆናቸው ላይ የሚመሠረት ነው። አንድ መሪ ወይም አገልጋይ ከላይ በተዘረዘሩት ግንኙነቶች ሁሉ ጤናማ ካልሆነ፣ ለውድቀት መዳረጉ የማይቀር ነው። በመሆኑም፤ አንድ አገልጋይ ጥሩ መጋቢ ሆኖ ሳለ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ጥሩ ግንኙነት ከሌለው በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ስኬታማ ሊሆን አይችልም። ብዙውን ጊዜ ለአገልጋይ አስፈላጊ የሆነው ነገር በእነዚህ በአምስት የሕይወት ክፍሎች ግንኙነቶቹን ለማሳደግ የሚረዳው ነገር ነው።

**ለ. እግዚአብሔር የሰጠንን አስፈላጊ ነገሮች ማከናወን፡፡**
ጥሩ ግንኙነቶችን መመሥረት ብቻ በቂ አይደለም። እግዚአብሔር የምናከናውነውን ተግባር ሰጥቶናል። እኛም ይህንን ተግባር መፈጸም አለብን። ከሰዎች ጋር ሆነን ጤናማ ግንኙነት በመመሥረት ብቻ ልንወሰን አይገባም። የእግዚአብሔርን ሕዝብ እርሱ ወደ ሰጣቸው ራእይ መምራትም ይጠበቅብናል። ሰዎች ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ መርዳት አለብን። ቤተ ክርስቲያን በበለጠ ትጋት ወንጌልን እንድትመሰክር፣ ክርስቲያኖች በማኅበረሰባችን ውስጥ በተጨባጭ መንገዶች ክርስቲያናዊ ፍቅርን እንዲያሳዩ ማስቻል አለብን። ሰይጣን አስፈላጊ ያልሆኑ ነገሮችን በማድረጉ ሥራ ላይ እንድንጠመድ የሚችለውን ሁሉ ማድረጉ የማይቀር ነው። እግዚአብሔር አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያስበውን ነገር እናደርግ ዘንድ የጊዜ አጠቃቀማችንን መወሰን አለብን።

| |
|---|
| 31ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በእነዚህ አምስት ግንኙነቶች ላይ ትኩረት አለማድረግ የአንድን የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም አገልጋይ አመራር ሲያበላሽ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) በግንኙነቶች ላይ ከመጠን በላይ ጊዜ ማጥፋት በበኩሉ አገልጋዩ ሥራውን እንዳያከናውን በማድረግ ከውጤታማ አመራር እንዴት እንደሚያርቀውም ግለጽ። |